# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪ መፅሐፍ

# 5ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የግብረ-ገብ ትምህርት የተማሪ መፅሐፍ አምስተኛ ክፍል

የግብረ ገብ ትምህርት

የተማሪ መፅሐፍ

5ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# ይህ መጽሐፍ በጥንቃቄ ይያዝ!

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው። ስለዚህም እንዳይጎዳ ወይም እንዳይጠፋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጉ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ይረዷችሁ ዘንድ የሚከተሉትን 10 ነጥቦች አስተውሉ።

1. መጽሐፉን እንደ ፕላስቲክ፣ ጋዜጣ እና በመሳሰሉ ቁሶች መሸፈን፣
2. መጽሐፉን ንጹህ እና ደረቅ ቦታ ማስቀመጥ፣
3. መጽሐፉን በሚጠቀሙበትጊዜ እጅዎት ንጹህ መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በመጽሐፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገጾች ላይ አለመጻፍ፣
5. ገጾችን ከማጠፍ ይልቅ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድለምልክት መጠቀም፣
6. ማናቸውንም ምስሎች ወይም ገጾችን ፈጽሞ አለመቅደድ፣
7. ማናቸውንም የተቀደዱ ገጾች መጠገን፣
8. መጽሐፉን በቦርሳ ውስጥ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፣
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ሲያውሱ በጥንቃቄ ማቀበል፣
10. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቀሙ፤ መጽሐፉን በጀርባ ሽፋኑ በኩል ማስቀመጥ ከዚያም በአንድ ጊዜ ውስን ገጾችን መግለጽ፤ እንዲሁም የመጽሐፉን ጠርዞች በትንሹ ጫንጫን ማድረግ። ይህም የመጽሐፉ ሽፋን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ይረዳል።

# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪ መፅሐፍ

## የአምስተኛ ክፍል


አዘጋጆች ገብረጻድቅ አውግቸው (MA)

ከበዴ ይማም (PHD)

አርታዒዎች አብዮት ታከለ (MA) የይዘት አርታኢ

ግርማ ገብሬ (MA) የቋንቋ አርታኢ

መሰረት አሰፋ (PHD) የስርዓተ ትምህርት አርታኢ

ሰዓሊ ኤሊያስ ወ/አገኘ (M.sc)

ዲዛይነር መስፍን አብርሃም (B.sc) (አመሳክሮ የሰራው)

ዮሐንስ ቢያድግለኝ (M.sc)

ተርጓሚዎች ጌቱ ታምሬ (M.A)

ኃብታሙ የኃላጌጥ (M.A)

አርታኢና ገምጋሚ ገበየሁ አስፋው (M.A)

አስተባባሪ ጌታቸው ታለማ (M.A)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው xxxxx 2022 (እ.ኤ.አ) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ለፍትሃዊነት (GEQIP-E) በተባለ በዓለም ባንክ፣የእንግሊዝ አለም አቀፍ ልማት ክፍል (DFID) የጋራ ሀብትና ልማት ቢሮ (FCDO)፣ የፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ንጉሣዊ የኖርዌይ ኤምባሲ፣ በተባበሩት መንግስታት የህጻናት አድን የገንዘብ ተራድኦ፣ የአለም አቀፍ የትምህርት አጋርነት (GPE)፣ እና የዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣በተለያዩ ለጋሽ ትረስት ፈንድ እገዛ በኩል ነው፡፡

©2022 (እ.ኤ.አ) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ በትምህርት ሚኒስቴር መብቱ በህግ የተጠበቀ ሆኖ የደራሲው የሞራል መብቶች የተረጋገጡ ናቸው። የዚህን መማሪያ መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል በተለያየ መንገድ ወይም በማንኛውም መልኩ በቅጂ ለምሳሌ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በሜካኒካል፣ በማግኔቲክ፣ በፎቶኮፒ ወዘተ በመሳሰሉት በፌዴራል የትምህርት ሚኒስቴር የጽሑፍ ፈቃድ ከተሰጠው አካል ውጪ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ አዋጅ ቁጥር 410/2004 - እንደተገለጸው የቅጂ መብቶች ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ ለተሳተፉ በርካታ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ሌሎች አካላትን ማመስገን ይፈልጋል፡፡ በተለይ ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲእና ትብብር ላደረጉ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናውን ያቀርባል።

የቅጂ መብት ያላቸው ቁሳቁሶች በባለቤቶቻቸው ፈቃድ ተገቢ እውቅና ተሰጥቶት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን የቅጂ መብት ባለቤት ከሆኑና በአግባቡ ያልተጠቀሰ ነገር ካለ እባክዎን ኢ.አ አራት ኪሎ በሚገኘው የትምህርት ሚኒስቴር፣ ዋና መሥሪያ ቤትን ያነጋግሩ(ፖ.ሣ.ቁ 1367) አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።

የታተመውበ፡ -------------

xxxxxxxxማተም

ፖ.ሣ.ቁxxxxxx

xxxxxxx, ኢትዮጵያ

በትምህርት ሚኒስቴር ውል ቁጥር. xxxxxxxxxxx

ISBN፡________

# መቅድም

ትምህርት የኢትዮጵያ ልማት ቁልፍ መሳሪያ ነው ሲባል ትምህርት እና ልማት በቅርበት የተያያዙ በመሆናቸው ነው፡፡አሁን የምንኖርበት ፈጣን የሉላዊነት ዓለም በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ አዲስ  እውቀት፣ችሎታ እና አመለካከት ይፈልጋል፡፡ የሀገራችን አዲሱ የስርዓተ ትምህርት ትግበራ ይህንን አላማው ያደረገና ለውጡን ለማፋጠን ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስርዓተ ትምህርቱ ንድፍ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ የትምህርት ስርዓት ነፀብራቅ ሆኖ ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

ኢትዮጵያ አዲሱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መተግበር ከጀመረች ከ 1994 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ሶስት አስርት አመታት ውስጠ በርካታ ውጤቶችን አስመዝግባለች፡፡ በሀገሪቱ በተለይም በትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና አግባብነት ረገድ ከፍተኛ እድገት ተመዝግቧል፡፡ ጥራቱንም ለማሻሻል ጠንካራ ጥረቶች ተደርገዋል፤እየተደረጉም ይገኛሉ፡፡

ይህንን እድገት ለማስቀጠል የትምህርት ሚኒስቴር አዲስ የአጠቃላይ ስርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ በ2021 እ.ኤ.አ አዘጋጅቷል፡፡ የትምህርት ስርዓት ማዕቀፉ ሁሉንም ቅድመ-መደበኛ፣የመጀመሪያ ደረጃ፣መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች እና የትምህርት ዓይነቶች ያካተተ ነው፡፡

የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ ዓላማውም መሰረታዊ መርሆችን በመከተል ከዚያም በተከታታይ ለሚዘጋጁት የመምህሩ መመሪያ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ እና ሁሉንም ቀጣይ የስርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲሁም ችግር ፈቺ የማስተማር ስነ-ዘዴንና ተማሪ ተኮር የማስተማር አቀራረብን መሰረት በማድረግ ብቃት ያለው ዜጋ ማፍራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በዚህአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ላይ አዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናት (2018እ.ኤ.አ) እንደ አንድ የጀርባ አጥንት ተደርጎ ተወስዷል፡፡አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በይዘት ደረጃ የተማሪዎችን ዕድሜ ከግንዛቤ ያስገባ ፣ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ያካተተ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመማር ማስተማር ዘዴን ያስተሳሰረ እንዲሁም የቀለምና የሞያ ትምህርትን ያጣመረ ሆኖ የግብረገብ ትምህርቱ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ሙያዊና የክህሎት ትምህርትን በማዛመድ ተማሪዎች እንደ የፍላጎታቸው እንዲጠቀሙበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ለዚህ ሥርዓተ ትምህርት መሻሻልእና ትግበራ በቀጣይነት የትምህርት ሚኒስቴር አስተያየቶችን፣ ሀሳቦችንና ጥያቄዎችን ለመቀበል እንዲሁም የበለጠ ማሻሻያ ለማድረግ ሁልጊዜም ዝግጁ ነው፡፡

አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ — የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ሰኔ 2022 — የትምህርትሚኒስቴር

## መግቢያ

የሰውን ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ባህሪነው። የሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ ባህሪያትንና ሌሎች ተሰጥኦዎችን በተፈጥሮ ሳይሆን በትምህርት ማዳበር ይችላል።

ሰዎች ያላቸው የትምህርት አቅም በጣም አስፈላጊ ነው።ይህ አቅማቸው በሥነ-ምግባር የታነፁና ወደፊት የሚያስቡትን  እንዲሆኑ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

በሌላ መልኩ የሰው ልጅ ምንም ያህል ስልጣኔ ቢኖረው በቂ ሥነ-ምግባር ከሌለው ማህበራዊ ግንኙነቶቹ ጤናማ አይሆኑም። ሥነ-ምግባር በውስብስብ ዓለም ውስጥ እንዴት ከሌሎች ጋር በሰላም አብሮ መኖር እንደሚቻል እውቀትን የሚጠይቅበት ጥበብ ነው። ማንኛውም ሥልጣኔ የተሟላ ትርጉም የሚኖረዉ አንድን የሚታይ ነገር ተቀባይነት ያለው፣ ትክክለኛ ወይም የሚጠበቅ ባህሪን ሲላበስ ነው።

ስለዚህ እነዚህ የሚጠበቁ ማህበራዊ ደንቦች በህብረተሰቡ ውስጥ ሥርዓት ያለው ባህሪን ለማራመድ እንደየባህሪ ደረጃዎች የሚሰሩ ይሆናሉ። እያንዳንዱ ማህበረሰ ብመኖር ካለበት ማህበራዊ ህጎቹን እና ልማዶቹን ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ማስተላለፍ አለበት። ያለ ትምህርት ሰዎች ማህበራዊ ህጎችን መከተል እንደማይችሉ ግልጽ ነው። በዚህ ምክንያት ማህበራዊነት ቀጣዩን ትውልድ ለማስተማርና ዕሴቶቹን ጠብቀው ለመኖር ያስችላል።

ሰዎች ማኅበራዊ ሕጎችን ለመቀበልና ለመተግበር በሥነ-ምግባር መታነፅ ይኖርባቸዋል። በሌላ አነጋገር ዜጎች በማህበረሰባቸው ውስጥ ያሉ ማህበራዊ ደንቦችን ሲገነዘቡ የበለጠ ወደ ውስጣቸው በማስረፅ በአኗኗር ዘይቤያችው ውስጥ የዕለትተ ዕለት ተግባር ይሆናል።

“ግብረገብ” የሚለው ቃል የሚገልፀው የሰውን የሥነ-ምግባር ደንቦችን ሲሆን ሰዎች እንዴት ተባብረው በማህበራዊ ህይወት ውስጥ በትስስር መኖር እንዳለባቸው ያሳያል።

በአሁኑ ጊዜ የትምህርት ቤቶች ዓላማ የተማሪዎችን ስነ-ምግባር፣ ዕሴቶችንና የዕውቀት አቅማቸውን ማሳደግ ነው። የግብረገብ ትምህርት የሚያተኩረው የተማሪዎችን የስነ-ምግባር ዕሴቶችን ማሳደግ ሲሆን ይህም ሀቀኝኝነትን ፣ታማኝነትን፣ ኃላፊነትን መወጣት፣ ሌሎችን ማክበርን ወዘተ ያጠቃልላል። በመሆኑም የግብረገብ ትምህርት ማለት ወጣት ተማሪዎችን በስነ-ምግባራቸው የተሻሉ እንዲሆኑ ከማገዙም በላይ በህብረተሰቡ ውስጥ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ እንዲሁም ተቀባይነትና ተወዳጅነትን እንዲያተርፉ ማስቻል ነው።

በአጠቃላይ የግብረገብ ትምህርት ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ እድገትና ማህበራዊ መስተጋብር  አስፈላጊ በመሆኑ እንደማህበረሰብ ነፃ ሆነንና ጠቃሚ የስነ-ምግባር ዕሴቶቻችንን ጠብቀን ለመኖር ሲባል ለትምህርቱ የሚሰጠው ትኩረት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

የግብረገብ ትምህርት ግቦች

(ሀ) መልካም ባህሪያትንና ችሎታን በማዳበር ኃላፊነት መውሰድን፣ የውሳኔ ሰው መሆንን፣ስራ ወዳድና በምክንያት የሚያምን ዜጋን ማፍራት።

(ለ) ተማሪዎች በግብረገብ ትምህርት አማካይነት የአንድን ህብረተሰብ እምነትን፣ ባህልን ፣መቻቻልን፣ እውነተኛነትን፣ መከባበርንና ትህትናን እንዲያዳብሩ ማድረግ።

(ሐ) ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ ንቁ ሚና እንዲጫወቱ ማበረታታት እና መደገፍ።

(መ) ተማሪዎች የሀገራቸውን እንዲሁም በአለቀም-አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ባህሎችን እንዲያውቁና የባህል ልዩነቶችን ተረድተው አንዲያደንቁ ማድረግ።

(ሠ)የተማሩ፣ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ የበለጠ ዓለም አቀፋዊ ሁነቶችን የተረዱ ንቁዜጎችን መፍጠር ናቸው።

የ5ኛ ክፍል የግብረ ገብ ትምህርት ዓላማው ለተማሪዎች መልካምነትን ፣ታማኝነትን፣ኃላፊነትን መወጣትንና ርህራሄን ማዳበር ሲሆን በአካልም በአእምሮም ጤነኛ የሆነና ውጤታማ ዜጋ ማፍራት ነው፡፡
ይህንን ዓላማ ለማሳካት ትምህርቱ በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን ኃላፊነት መወጣት፣ጠንካራ የስራ ባህል፣የግብረገባዊ ውሳኔ ክህሎት፣አካባቢን መንከባከብ፣ማህበራዊ ድረ- ገፆች የመጠቀም ስነ-ምግባር እና የባህል ትስስር ተካትተዋል።

ማውጫ ገፅ

1 ኃላፊነትን መወጣት ........ 1
1.1 የኃላፊነትምንነት ........ 2
1.1.1 የኃላፊነት ትርጉም ........ 2
1.1.2 ኃላፊነትን የመወጣት ምንነት ........ 3
1.2 ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት ........ 5
1.2.1 ኃላፊነት ለተግባራችን አስፈላጊ ነዉ ........ 5
1.2.2 ለስሜቶቻችን ኃላፊነትን መዉሰድ አስፈላጊ ነዉ ........ 5
1.3 የኃላፊነት ዓይነቶች ........ 7
1.3.1 የግለሰብ ኃላፊነት ........ 7
1.3.2 የቤተሰብ እና የህብረተሰብ ኃላፊነት ........ 7
1.3.3 ሀገራዊ ኃላፊነት ........ 8
1.4 የግብረገባዊ ኃላፊነት ዓይነቶች ........ 8
1.4.1 ቃልን መጠበቅ ........ 9
1.4.2 ሌሎችን መርዳት ........ 9
1.4.3 የሀብት አጠቃቀም ........ 11
1.4.4 ንቁ የማህበረሰብ ተሳትፎ ........ 12
1.4.5 ግብር መክፈል ........ 13
1.4.6 የትራፊክ ደንቦችን ማክበር ........ 13
1.4.7 አካባቢን መንከባከብ ........ 15
1.5 የምዕራፉ ማጠቃለያ ........ 17
2 ጠንካራ የስራ ባህል ........ 20
2.1 ጠንካራ የስራ ባህል ........ 21

2.2 የጠንካራ ስራ ባህል አስፈላጊነት ........ 22
2.3 የታታሪ ሰራተኛ ባህሪያት ........ 24
2.4 የንባብ ባህል ........ 26
2.5 የንባብ ክህሎትን ለማዳበር የሚጠቅሙ ስልቶች ........ 29
2.5.1 ዓላማ ያለው ንባብ ........ 29
2.5.2 መቃኘት/የዳሰሳንባብ ........ 29
2.5.3 የአሰሳ ንባብ ........ 29
2.5.4 የመረጃ ሰጭ ቃላት ........ 30
2.5.5 የሀረግ ንባብ ........ 30
2.5.6 ጽሑፍ ላይ ምልክት ማድረግ ........ 32
2.5.7 ማስታወሻ መያዝ ........ 32
2.5.8 በጋራ ማንበብ ........ 32
2.6 የምዕራፉ ማጠቃለያ ........ 33
3 የግብረገባዊ ውሳኔ ክህሎት ........ 35
3.1 የውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ-ሀሳብ ........ 37
3.2 የግብረገባዊ ውሳኔክህሎትመገለጫዎች ........ 38
3.2.1 አስተሳሰብ ........ 38
3.2.2 ምክንያታዊነት ........ 38
3.2.3 ምክንያታዊ ውሳኔ ........ 39
3.3 የግብረ ገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ቅደም ተከተል ........ 40
3.4 የግብረ ገባዊውሳኔ አሰጣጥ ቅደም ተከተል ........ 44
3.5 የግብረገባዊ ውሳኔ ተግዳሮቶች ........ 45
3.6 የምዕራፉ ማጠቃለያ ........ 47



የግብረ ገብ ትምህርት

4 የአካባቢ እንክብካቤ ........ 50
4.1 መግቢያ ........ 51
4.1.1 ‘አካባቢ’ ምንድን ነው? ........ 51
4.2 የአካባቢ እንክብካቤ ጽንሰ-ሀሳብ ........ 51
4.3 የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት ........ 52
4.3.1 አካባቢያችን እንደ ቤታችን ........ 53
4.3.2 ንፁህ አካባቢ ማለት ጤናማ ህይወት ማለት ነው ........ 53
4.3.3 የሙቀት መጨመርን መቆጣጠር ........ 53
4.3.4 ስነ-ምህዳርንና ሰብአዊነትን መንከባከብ ........ 54
4.3.5 የብዝሃ ሕይወት አስፈላጊነት ........ 54
4.3.6 አካባቢያችንመኖሪያችን ብቻ ሳይሆን የሀብት ምንጫችንም ነው. .. . . 54
4.3.7 የግብረገባዊ ግዴታችን ........ 55
4.3.8 አካባቢን መጠበቅ የተሻለ ህይወት መኖር ነው ........ 55
4.4 አካባቢንየመንከባከቢያ መንገዶች ........ 55
4.4.1 ተረፈ ምርቶችን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ብክነትንና ቆሻሻን መቀነስ ........ 56
4.4.2 የውሃ ሀብትን ባግባቡ መጠቀም ........ 56
4.4.3 ንጹህ የኃይል ምንጮችን መጠቀም ........ 56
4.4.4 ግብይትን በአግባቡ መጠቀም ........ 57
4.4.5 የኬሚካል አጠቃቀምን መቀነስ ........ 57
4.5 የአካባቢ እንክብካቤ ጉድለት የሚያስከትለው መዘዝ ........ 58
4.5.1 የውሃ እጥረት ........ 59
4.5.2 የአየር ብክለት ........ 59

4.5.3 አደገኛ ደረቅ ቆሻሻዎች ......59
4.5.4 የምግብ እጥረት ......59
4.5.5 የብዝሃ ህይወት መጥፋት ......60
4.6 የምዕራፉ ማጠቃለያ ......61
5 የማህበራዊ ድረ ገፆችአጠቃቀም ሥነ-ምግባር ......64
5.1 የማህበራዊድረገፆችትርጉም ......65
5.2 የማህበራዊ ድረገፆች አስፈላጊነት ......66
5.3 የማህበራዊ ድረገፆችአጠቃቀም ስነ-ምግባር ......67
5.4 ስነምግባር የጎደለው የማህበራዊ ድረገፆችአጠቃቀም ስጋት ...... 69
5.5 የምዕራፉ ማጠቃለያ ......75
6 የባህልትስስር ...... 77
6.1 መግቢያ ......78
6.2 የባህል ትስስርምንነት ......79
6.3 የባህል ትስስርአስፈላጊነት ......81
6.4 የባህል ትስስር አመላካቾች ......84
6.4.1 ውጤታማ ተግባቦት ......84
6.4.2 ባህልዊ ሽምግልና ......86
6.4.3 በትኩረት የሚደረግ የተግባቦት ባህሪያት ......87
6.5 የምዕራፉ ማጠቃለያ ......89





# ምዕራፍ አንድ

# ኃላፊነትን መወጣት

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ኃላፊንትን ስለመወጣትና ስለአስፈላጊነቱ ይዳስሳል። በአራት ዋናዋና ርዕሶች የተከፈለ ሲሆን እነዚህም የኃላፊነት ትርጉም፣ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት፣የኃላፊነት ዓይነቶች እንዲሁም የግብረገብ ኃላፊነት አይነቶች ናቸዉ።ስለሆነም ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረው ኃላፊነትን ወይም ተጠያቂነትን በአግባቡ መወጣት ላይ ነዉ። ተማሪዎች ለሚያደርጓቸዉ ሁሉ እንዴት ሃላፊነት ወይም ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸዉና ይህንንም በማድረጋቸዉ ሲወደሱ ባለማድረጋቸዉ ደግሞ ሊወቀሱ ይችላሉ። ምክንያቱም የእናንተ ድርጊት አዎንታዊ ዉጤቶች ስላሉት ነዉ።

የምዕራፉ የመማር ዉጤቶች፡ ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- የኃላፊነት ምንነትን ትረዳላችሁ።
- ኃላፊነት የመወጣትን ጠቃሚነት ዋጋ ትሰጣላችሁ።
- የኃላፊነት ዓይነቶችን ታብራራላችሁ።
- የሚጠበቅባችሁን ግብረገባዊ ኃላፊነትን ታሳያላችሁ።

## 1.1 የኃላፊነት ምንነት

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ተግባር 1.1

- በቤትህ/ሽ ውስጥ ኃላፊነት እንዳለብህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?
- አንዳንዶቹን ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ልትጠቅስ/ሽ ትችላለህ/ሽ?

### 1.1.1. የኃላፊነት ትርጉም

ኃላፊነት ማለት ታማኝ መሆን፣ ጥሩ ምርጫ ማድረግ እና ለድርጊቶቻችን ተጠያቂነትን መውሰድ ማለት ነው፡፡ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ የሌሎች ደህንነት ይመለከተዋል፡፡ዓለምን የተሻለች የመኖሪያ ቦታ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰው ድርሻ እንዳለበት ይገነዘባል፡፡

ውስን ጥናት1.1፡ የሚከተለውን ምልልስ አንብቡና ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

1) ናሆም በቤቱ ውስጥ ኃላፊነት አለበትን?

2) ናሆም በቤቱ ውስጥ ያለው ኃላፊነት ምንድን ነው?

ልጅ፡ “አባዬ ከጫላ ጋር ልጫወት ነው፡፡”

አባት፡ “የትምህርት ቤት የደንብ ልብስህን አጥበሃል?”

ልጅ፡ “አይ ስመለስ አጥባለሁ”

አባት፡ “ናሆም፣ የትምህርት ቤት የደንብ ልብስህን ማጠብ የአንተ ኃላፊነት ነው፡፡ በዚህ ቤት ውስጥ ኃላፊነታችንን መወጣት ይቀድማል፡፡ መጀመሪያ የደንብ ልብስህን አጥበህ ከዚያም ወደ ጫላ ቤት መሄድ ትችላለህ፡፡”

በት/ቤት ደረጃም ሆነ ከዛም ባለፈ ኃላፊነትን መወጣት ለስኬት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሰዎች በአንተ ላይ እንዲተማመኑብህ ማደረግ የሚገባህ ነገሮች፣

- የገባኸውን ቃል መጠበቅ፣
- ግዴታዎችን ማሟላት፣
- አንድን ነገር በአቅም ልክ መስራት፣
- ለራስህ ባህሪ ተጠያቂ መሆን፣





- መልካም ነገሮችን በማድረግ ምስጋና መቀበል፣
- ስህተቶችን መቀበል፣
- ለቤተሰብና ለህብረተሰብ አስተዋጽዖ ማድረግ፡፡

ኃላፊነት ሁሉም ልጆች መማር ያለባቸው ነገር ነው፡፡ ስለኃላፊነት ለማወቅና ለመማር ከምንችልባቸዉ መንገዶች መካከል በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ በንቃት መሳተፍ ነው፡-

- ለክፍል ጓደኞቻችሁ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
- ለቤተሰቦቻችሁ አገልግሎት መስጠት፡፡
- ጓደኞችን እና ጎረቤቶችን ማገዝ፡፡

ለማህበረሰቡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት፡፡

- ስህተቶችን ለማረምና ለይቅርታ መዘጋጀት እና የመሳሰሉት.....

ተግባር 1.3

1) ከዚህ በፊት ከላይ ከተጠቀሱት ዉስጥ በአንዱ ወይም በሌሎች ተግባራት ላይ ተሳትፋችኋል?

2) ልምዳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### 1.1.2 ኃላፊነትን የመወጣት ትርጉም

ኃላፊነትን መወጣት ማለት አንድ ሰዉ ከእርሱ የሚጠበቀዉን ተግባር ወይም ግዴታ በአግባቡ ማሟላት ማለትነው፡፡

ኃላፊነት ማለት ከእናንተ የሚጠበቅ ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ:

- ወላጆችህ እጅህን እንድትታጠብ ይጠብቃሉ፡፡ እጅን መታጠብ ያንተ "ኃላፊነት ነው"

ስለሆነም ከምግብ በፊትም ሆነ በኋላ ሁልጊዜ እጅን መታጠብ አንደኛው ኃላፊነታችሁ ነው፡፡

- ሌላው ደግሞ አንድ መምህር ለተማሪዎቹ የሰጠዉን የቤት ስራ ሰርተዉ እንዲመጡ ይጠብቃል፡፡ ስለሆነም ወደ ትምህርት ቤት ከመምጣታችሁ በፊት መስራትና ማጠናቀቅ ኃላፊነታችሁ ነው፡፡

ኃላፊነት ማለት ከእናንተ የሚጠበቅ ድርጊት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ:-

• ወላጆቻችሁ በመንገድ ላይ ለመጫወት ከሄዳችሁ የመኪና አደጋ ሊያጋጥማችሁ እንደሚችል ይሰጋሉ፤ እናም እራሳችሁን ወይም ሌላ ሰው እንዳይጎዳ መጠንቀቅ ኃላፊነታችሁ ነዉ።

ስለ ኃላፊነት ስንናገር በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ፤ለምሳሌ የሚከተለውን ስዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ።




## ተግባር 1.4

ጥንድ ጥንድ በመሆን ተቀመጡና  መስራት የሚጠበቅባችሁን ተግባራት እና የምታከናዉኑበትን መንገዶች ጥቀሱ።

እንዲሰሩ የሚጠበቁ ተግባራት:-

1) ............................................2) ........................................

3) ..........................................4) ..........................................

5) ......................................... 6) .......................................

የሚጠበቁ የመተግበሪያ መንገዶች:-

1)...................................... 2)..........................................

3)..............................................4)..........................................

5)..........................................6)...........................................





ኃላፊነት የመወጣትን አስፈላጊነት ለመረዳት ሰዎች ተጠያቂ ካልሆኑ ምን ሊፈጠር እንደሚችል  ማሰብ በቂ ነዉ።

• ከሌሎች ጋር እንዴት ትጫወታላችሁ ወይም ትሰራላችሁ?
• ሰውነታችሁን እንዴት ትጠብቃላችሁ?
• የቤት ስራችሁን እንዴት ትሰራላችሁ?
• ንብረቶቻችሁንእንዴትትንከባከባላችሁ?

### 1.2.1 ኃላፊነት ለተግባራችን አስፈላጊ ነው

ተጠያቂ መሆን ማለት ድርጊቶችን ከውጤታቸው ጋር ማገናኘት ነው። ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣትን ለመረዳት አንዱ መንገድ ሰዎች ተጠያቂ ካልሆኑ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ግምት ውስጥ ማስገባት ነው።

ለምሳሌ:-

• **ከሌሎች ጋር መጫወት ወይም መስራት:-** ተማሪዎች ኃይል በተቀላቀለበት መልኩ ቢጫወቱ፣ የቤት ስራቸዉን ባይሰሩ ፣ስለታማ ነገሮችን መጫወቻ በታቸው ላይ ይዘው ቢመጡና መኪኖች ሲመጡ ማየት በማይችሉበት መንገድ  ላይ ቢጫወቱ ምን ሊፈጠር ይችላል?

• **ራሳቸዉን መጠበቅ:** ተማሪዎች መኪኖች ሲመጡ ማየት የማይችሉበት መንገድ ላይ ቢጫወቱ ምን ሊፈጠር ይችላል?

• **ነገሮችን በንጽህና መጠበቅ:** ተማሪዎች ክፍላቸዉን ባያጸዱ፣ ቤታቸዉን በአግባቡ ባይዙ ወይም ቤት ዉስጥ እቃዎችን ቢያዝረከርኩ ምንሊፈጠርይችላል?

• **ተጠያቂነት የጋራ ጥረትን የሚጠይቅ ነው:** ሌሎች ለእኛ ሲሉ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ሁሉ እያንዳንዳችን ለሌሎች ኃላፊነት ልንወስድ ይገባናል።

### 1.2.2 ኃላፊነት በስሜታችን ወይም በፍላጎታችን ውስጥ አስፈላጊ ነው

ኃላፊነትን መዉሰድ ግድ የለሽ ከመሆን ውሎ አድሮ የጸጸት ስሜትን አይፈጥርም።

አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛውን ወይም ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ እርምጃ በወቅቱ መዉሰድ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ተጠያቂ መሆን የምትፈልገውን ውጤት ያስገኛል። ኃላፊነት የጎደላቸው ውሳኔዎች አሉታዊ ውጤቶችን በማስከተል የራስንና የሌሎችን ስሜትና ፍላጎት የሚረብሹ ይሆናሉ።

የሚከተለውን የፋሪስ ታሪክና ድርጊት አንብባችሁ ጥያቄውን ስሰሩት የበለጠ ግልፅ ይሆናል። ልጅ እያለን ያን ያህል ትልቅ ጉዳይ ላይመስለን ይችላል። ነገር ግን በዕድሜ ከፍ እያልን ስንሄድ ምርጫዎቻችንና ውጤቶቻቸው የበለጠ ግልጽና ጉልህ ይሆናሉ።

**ውስን-ጥናት 1.2:-** የፋሪስ የእግርኳስ ጨዋታ

ፋሪስ ከጓደኛው አሊ ጋር ከቤቱ ውጭ እግርኳስ ይጫወት ነበር።

እርስ በርስ ኳሱን ለመቆጣጠርና ለመምታት ጥረት ያደርጉ ነበር።. በእያንዳንዱ ጨዋታ ፋሪስ ራሱን የሰፈሩ ቁጥር አንድ ተጨዋች እንደሆነ አድርጎ ያስብ ነበር። የስፖርት ተንታኙም በበኩሉ እንዲህ ይል ነበር "በዚህ የመጨረሻ ግጥሚያ ላይ ፋሪስ በዓለም ላይ ካሉ ምርጥ የእግር ኳስ ተጫዋቾች አንዱ ነው በሚል ሀገርተስፋጥሎበታል" ።

ፋሪስ በሙሉ ኃይሉ ኳሷን በብርቱ ሲመታት ኳሷ አጥሩን መትታ በመዉጣት የጎረቤት መስኮት ተሰባበረ!

"በፍፁም!"ወይኔ!" ፋሪስ እና አሊ በአንድነት ጮሁ አለቀሱ። "አምልጥ!" አለ፡- አሊእየሮጠ።

አሊ ጥግ አካባቢ ሲደበቅ ፋሪስ ተመለከተ።ለማምለጥ ቢያስብም እሱግን ይህን ማድረግ አልፈለገም ነበር። " ምንድንዉ የተፈጠረዉ ?" የሚልድምፅሰማ።ፋሪስ

ዘወር ሲል ጎረቤቱን አየ። "አዝናለሁ ጋሼ ሻፊ" አለፋሪስ። “ጥፋቱ የኔ ነበር።አላስተዋልኩም ነበር“።

**ተግባር 1.5**

አቅጣጫ፡-ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመቀመጥ ከላይ በውስን-ጥናት1.2.1 ባነበባችሁት ታሪክ መሰረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1) አሊለምንሸሸ? የእሱ ኃላፊነት ምንድን ነበር?

2) ፋሪስ ትክክለኛውን ነገር እያደረገ ነበር? አናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?





## 1.3 የኃላፊነት ዓይነቶች

የሰው ልጅ እውቀትና ጥበብ አለው። ይህንን የማሰብ ችሎታ በተገቢው መንገድ መጠቀም ከቻለ ራሱን ከሌሎች ሁሉ የተሻለ ፍጡር አድርጎ ማሰብ ይችላል።ከዚህ ቀደም እንደ ተማርነዉ ለድርጊታችን ተጠያቂዎች መሆናችንን እናስታዉሳለን።ከብዙ ምልከታዎች በመነሳት የተለያዩ የኃላፊነት ዓይነቶች አሉ።

### 1.3.1 የግለሰብ ኃላፊነት

የግለሰብ ኃላፊነት ከግል ባህሪያት እና ከመሳሰሉት ልማዶች ጋር የተያያዘ ነው። በግለሰብ ኃላፊነት ውስጥ የሚካተቱት የሚከተሉት ናቸው።

- በትህትና መናገር፣
- የሌሎችን ስሜት ማክበር፣
- የግል ጤንነትን መገንዝብ፣
- የትምህርት ቤት ሰዓት፣ህግና መመሪያዎች ማክበር፣
- መምህር የሰጠዉን  ተግባር በጊዜዉ መከወን፣
- ምግብ አለማባከን፣
- እውነትን መናገር፣
- አለመዋሸት፣
- በጓደኛ አለመቅናት፣
- ስግብግብነትን ማስወገድና ለተቸገሩ ማካፈል፣
- ጎጂ ነገሮችን አለመጠቀም፣
- የታላላቆችን፣የወላጆችንና የመምህራንን ምክር መቀበል እንዲሁም መታዘዝ፣
- የቤትእና የትምህርት ቤት ንጽሕናን መጠበቅ።

### 1.3.2 የቤተሰብ እና የማህብረሰብ ሃላፊነት

በቤተሰብ እና ማህብረሰብ ውስጥ ያለን ሁላችንም በሰላም አብሮ ለመኖር ሁላችንም የጋራ ኃላፊነትን መወጣት አለብን።

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በተለያዩ የዕድሜ ደረጃ ላይያሉ አባላት ይገኛሉ።በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ ዉስጥ በስምምነት ለመኖር እያንዳንዱ አባል የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል።ሁሉም የቤተሰብ አባላት እና ቤተሰብን እና ማህበረሰቡን ለማስቀጠል ህብረተሰቡ በተገቢው መንገድ ግዴታውን መወጣት አለበት።ስለዚህ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እና የህብረተሰብ ክፍል ደንቦች እና እሴቶችን ማክበር አለበት።እነዚህንም እሴቶች እና ደንቦች ማጎልበት አለባቸው። ለምሳሌ፡

- በማንኛውም የቤተሰብ ስራ ላይ መሳተፍ፣
- እርስበርስ መከባበር፣
- ለአዛዉንቶችና ለታመሙ ሰዎች ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ፣
- ለትንንሽ ልጆች እንክብካቤ ማድረግ፣አርአያ መሆን፣
- የቤተሰብ ኃላፊነትን መወጣት፣
- የቤተሰብን ስራ ማክበር የአንድ ቤተሰብ አባል ዋና ተግባር ነው።

### 1.3.3 ሐገራዊ ኃላፊነት

ከታች ባለው ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እንደ ተገለጸው ሁላችንም ለሀገራችን ኃላፊነት አለብን።እንደ ዜጋ ወይም እንደ አንድ የማህበረሰቡ አባላ ሁሌም ሀገራችንን ማስቀደምና ኃላፊነታችንን መወጣት አለብን።ይህም ሀገራችንን እንድናሳድግ እና ጥሩ ዜጋ እንድንሆን ያግዘናል።




ምስል 1.1: ሐገራዊ ሃላፊነት

## 4 የግብረገባዊ ኃላፊነት ዓይነቶች

ማህበራዊነት ማለት የግለሰብን ግንኙነት ከሚወስኑ ዋና ዋና ፅንሰ ሀሳቦች አንዱነው።ሰዎች በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ከሌሎች ጋር አብረው የሚኖሩ ማህበራዊ ፍጡራን ናቸው።ይህም ማለት እርስበርሳቸው በቁሳዊም ሆነ በሥነ-ልቦና የተሳሰሩና የተደጋገፉ ናቸዉ።በሌላ አባባል የመደጋገፍ ግንኙነት የእያንዳንዱን ግለሰብ ኃላፊነት ከመወጣት ጋር ይያያዛል።በተመሳሳይ ከተማሪዎች የሚጠበቅ





የተወሰነ "የግብረገባዊ ኃላፊነት" እና ግዴታ እንዳለባቸው መገንዘብ ያስፈልጋል።

ከዚህ አንፃር እንደተማሪ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በንቃት መሳተፍ ይኖርባችኋል።ለምሳሌ በሚከተሉት የግብረገባዊ ኃላፊነት ላይ፡-

### 1.4.1 ቃልን መጠበቅ

> **ተግባር 1.6**
>
> - ቃል-ኪዳንን ወይም ቃልን መጠበቅ ምንድን ነው?
> - ቃል-ኪዳንን መጠበቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ/ሽ?

ቃልን መጠበቅ ማለት አንድ ሰው አንድን ነገር እንደ ሚያደርግ ወይም እንደሚሰራ የሚያረጋግጥበት መግለጫ ነው። በሌላ አገላለጽ ቃል-ኪዳን ማለት አንድ ሰዉ የተናገረዉን እንደሚፈጽም ለሌላ ሰዉ

ቃል የመግባትን ኃላፊነት ለመወጣት 5 መንገዶች አሉ።

| ቃል የመግባት ኃላፊነትን ለመለማመድ የሚረዱ መንገዶቹ፡- |
|---|
| 1) ቃሌን እጠብቃለሁ። |
| 2) ሰበብ አላበዛም። |
| 3) ስራዬን በሙሉአቅሜ እሰራለሁ። |
| 4) ስህተት ከሠራሁ ነገሮችን አስተካክላለሁ። |
| 5) ግዴታዬን አውቄ በአግባቡ እወጣለሁ። |

### 1.4.2 ሌሎችን መርዳት

> **ተግባር 1.7፡**
>
> ከቤተሰባችሁ ውጪ ስለ ሚያግዟችሁ ሰዎች አስቡ።እነማን እንደሆኑና ምን እንደሚያግዟችሁ ግለጹ።ለምንድነዉ እናንተን ለመርዳት የመረጡት?

ሌሎችን መርዳት ለሚታገዘዉ ሰዉ ብቻ ሳይሆን ለረጂዉም የበለጠ ደስተኛና ጤናማ ያደርጋል።በተጨማሪም መስጠት ከሌሎችጋር ያለንን ግንኙነት ጠንካራ በማድረግ ደስተኛ ማህበረሰብ ለመገንባትያስችላል፡ ፡መርዳት ሲባል ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ጊዜን፣ሃሳብን፣ጉልበትን እና ሌሎችንም ሊሆን ይችላል። የተቸገሩትን መርዳት የህይወት ኃላፊነት ብቻ አይደለም ለሕይወት ትርጉምም ይሰጣል።

ሌሎችን መርዳት የመኖሪያ አካባቢን የተሻለ ቦታ ያደርገዋል።

ሌሎችን መርዳት ለሌሎች ደግ መሆን ነው።ይህም በሰፊው ማህበረሰብ ዉስጥ ሲለመድና ሲተገበር የሰዎችን ደህንነት በማረጋገጥ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸዉን ከማሟላት ጋር ተዛማጅነት አለዉ።

### ተግባር 1.8

የሚረዷችሁን አስቡ! እንዴትእንደሚረዷችሁእና ለእነርሱ ምንመጀመርእንደምትችሉአብራሩ!

የእናንተንእይታበሚከተለውባዶ ቦታ ላይጻፉ።

የምትረዷቸውሰዎች፡-

•...........................................................................................................

•...........................................................................................................

እንዴትእንደምትረዷቸው

•...........................................................................................................

•...........................................................................................................

እንዴትሊረዷችሁእንደሚችሉ

•...........................................................................................................

•...........................................................................................................





1.4.3 የሀብት አጠቃቀም

የሰዉ ልጅ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ማለትም እንደውሃ፣ኃይል፣ማዕድናትና በሌሎችም ላይ ያለዉፍላጎት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ነዉ። ምክንያቱም የህዝብ ቁጥር መጨመር በርካታ ቤቶች እንዲገነቡ ስለሚያደርግና ከዚህም ጋር ተያይዞ የፍጆታ መጨመር ስለሚያጋጥም ነዉ።

በተጨማሪም እነዚህን ሀብቶች ኃላፊነት በጎደለው መልኩ መጠቀም በአካባቢ ላይ ትልቅ ጫና ይፈጥራል።ለምሳሌ ጥንቃቄ የጎደለዉ የቆሻሻአወጋገድ ስርዓት እንዲሁም የአለም ሙቀት መጠን መጨመር ዉስን በሆነዉ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል።

ሀብቶች የሚባሉት፡-

- ጊዜ
- ገንዘብ
- ቁሶች
- ቦታ (መሬት)
- ሰዎች
- የተፈጥሮሀብት

በአንፃሩ የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ መጠቀማችን ወሳኝ መፍትሄ ከመሆኑም በላይ በአካባቢው ላይ የሚፈጠረዉን ጫና ይቀንሳል።ይህም የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ይባላል።የተፈጥሮ ሃብት የሰውን ፍላጎት ለማሟላት እና ለማርካት አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም ሰዉ በዚህ ረገድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት አለበት።

### ተግባር 1.9

ጥንድ ሆናችሁ በመቀመጥ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። ምላሾቻችሁን ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

- በቤት ውስጥ የገንዘብ ወጪ ወይም አስቤዛ ላይ እቅድ በማዘጋጀት ተሳትፋችኋል?
- የክረምት ጊዜያችሁን እንዴትና በምን ታሳልፉታላችሁ?
- ቤተሰቦቻችሁ ሀብትን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ አስቀድመው የማቀድ ልምድ አላቸው?

### 1.4.4 የነቃ የማኅበረሰብ ተሳትፎ

የማህበረሰብ ተሳትፎ በማህበረሰብ ውስጥ የሰዎች ተሳትፎ ተብሎ የሚገለጽ ሲሆን በተለያዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ የራሳቸውን ማህበራዊ ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ነዉ፡፡ተማሪዎች በግለሰብና በማህበረሰብ መካከል ያለዉን ግንኙነት አስፈላጊነት መገንዘብ አለባቸዉ፡፡ምክንያቱም የሰዉ ልጅ በማህበረሰቡ ዉስጥ ይገኛል፤ ተማሪዎች ደግሞ የዚሁ አንድ አካል በመሆናቸዉ ከማህበረሰቡ ተነጥለው መኖር አይችሉም፡፡

**ንቁ ዜጋ፡-**በአካባቢው፣በማኅበረሰቡ፣በሀገር ወይም በዓለምአቀፍ ደረጃ የነቃ ተሳትፎ የሚያደርግ ሰዉ ነዉ፡፡

ተማሪዎች ማህበረሰቡን በማሻሻል እና በማጠናከር ረገድ ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡ቀላሉ እውነታ ከተባብረን እንቆማለን ከተከፋፈልን እንወድቃለን፡፡ማህበረተሰብ የዚህ አንድነት መገለጫ ነው፡፡ስለዚህ ወንዶች እና ሴቶች በሁሉም እድሜ እናሙያዎች ያሉ በሙሉ ህብረተሰቡን ለማገልገል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

ማጥናት የተማሪዎች ዋና ሥራ ቢሆንምወጣትነትና ጉልበት ያላቸው በመሆናቸው በትርፍ ጊዜያቸው በተለያዩ የማህበራዊ ስራዎች ውስጥ መሳተፍይገባቸዋል፡፡

1) ተማሪዎች የትምህርት ዘመቻ ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው፡፡

2) ማንበብና መጻፍ የማይችሉትን ማንበብና መጻፍ ማስተማር ይችላሉ፡፡

3) የደም ልገሳ ፣ በተለያዩ የስፖርት ክበባት፣ በጤና ማዕከላት፤ በቤተ-መፅሐፍት ወዘተ በመሳሰሉት ብዙ ሰዎችን በመንከባከብ ላይ ያግዛሉ፡፡

4) በዕቁብ፣ በሎተሪ እና በመንግስት እርዳታ ገንዘቦችን በማሰባሰብ የበጎ አድራጎት ትርኢቶችን በማዘጋጀት የተቸገሩትን ይረዳሉ፡፡

5) ተማሪዎች የጥቂቶችን ፀረ-ማህበራዊ ተግባራትንናሙሰኞች በመታገል ኃላፊነታቸዉን ይወጣሉ፡፡

6) አደንዛዥ እጾችን እና መጠጦችን ከአካባቢያቸው ለማጥፋት ተግተው ይሰራሉ፡፡

**ተግባር 1.10**

- በማህበረሰባችሁ ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት ማህበራዊ ስራዎች ላይከዚህ በፊትንቁ ተሳትፎ አድርጋችኋል? መልስህ/ሽ 'አዎ' ከሆነ ከክፍል ጓደኛህ/ሽ ጋር በጋራ ተወያዩበት፡፡

- ከአሁን በኋላ በማህበረሰብ ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ ፍላጎት አላችሁ?





### 1.4.5 ግብር መክፈል

**ተግባር 1.11**

- ወላጆችህ ግብር እየከፈሉ ነው? ለምን ግብር እንደሚከፍሉ ትጠይቃላችሁ?

ግብርበግለሰብ ወይም በዜጎች ለሀገራቸው የሚከፍሉት የዉዴታ ግዴታ የገንዘብ ልክ ማለት ነዉ፡፡በሁሉም የአለም ሀገራት መንግስት በዋናነት ብዙ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚሰበስበዉ ገቢ ግብር ይባላል፡፡

መንግስትም በግብር መልክ በሰበሰበዉ ገንዘብ በርካታ ስራዎችን ያከናዉናል፡፡ ለምሳሌ ለመሰረተ-ልማት ግንባታ፣ ለደህንነት ለማሕበራዊ አገልግሎቶች እና ለሌሎች የዕለት ተዕለት የመንግስት አስተዳደራዊ ወጪዎች ይዉላል፡፡ ስለዚህ አስፈላጊ ከሆኑ የዜግነት ግዴታዎች ወይም ኃላፊነቶች አንዱ ግብር መክፈል ነው፡፡

### 1.4.6 የትራፊክ ደንቦችን ማክበር

የትራፊክ ህጎችን ሁልጊዜ ማክበር አንዱ ቅድሚ የሚሰጠዉ የኃላፊነት ተግባራችንነው፡፡ከዚህ በታች ያለው መዝሙር ስለ ትራፊክ ህጎችና ደንቦች እንዴት እንደምናከብር ይገልጻል፡፡



ምስል 1.2፡ታላቅ ወንድም እና ታናሽ እህት አረንጓዴው መብራት ሲበራ በእግረኛ ማቋረጫዉ ላይ አብረው ሲሻገሩ

ኀበዝ ተማሪዎች ጠንቃቃ ናቸው፤
መንገድ ሲያቋርጡ ግራ ቀኝ አይተው፤
በዜብራ በኩል የቤተሰብ እጅ ይዘው ፤
አረንጓዴው ምልክት መብራቱን አይተው፤
መንገድ ላይ ሲጓዙም ግራቸውን ይዘው ነው፡፡

ምስል 1.3፡የትራፊክ ደንቦችን እንዴት ማክበር እንደሚቻል መዝሙሩን ዘምሩ

### ተግባር 1.12

ከላይ ያለውን መዝሙር አብራችሁ ከዘመራችሁ በኋላ መንገድ ስታቋርጡ ምን እንደም ታደርጉ በክፍል ዉስጥ ተወያዩበት፡፡

### ተግባር 1.13

በትራፊክ ደንቦች መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

- “ቀይ መብራት” ማለት ምን ማለት ነው?
- "ቢጫ መብራት" ማለት ምን ማለት ነው?
- "አረንጓዴ መብራት" ማለት ምን ማለት ነው?

**አስሩ የትራፊክ ደንቦች፡**

1. በመንገድ ላይ ደህንነታችንን ለመጠበቅ የትራፊክ ደንቦችን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡
2. መንገድ ስትሻገሩ አትቸኩሉ፡፡
3. የመንገድ ዳር ምልክቶችን አክብሩ፡፡
4. ቀይ ሲበራ ቁሙ፡፡
5. አረንጓዴ ሲበራ ሂዱ፡፡
6. የመኪና በር ሲከፈት ከአጠገባቹሁ ያለዉን ተመልከቱ፡፡
7. በሚፈጥን ተሽከርካሪ አጠገብ አትሂዱ፡፡
8. መታጠፊያ ላይ አታቋርጡ፡፡
9. በእግረኛ ማቋረጫ ላይ ብቻ ተሻገሩ፡፡
10. እጃቹሁን በመስኮት አታዉጡ፡፡








ምስል 1.4: 10ሩ የትራፊክ ደንቦች

### 1.4.7 አካባቢን መንከባከብ

አካባቢን መንከባከብ ሌላዉ የሁላችንም ግዴታ ብቻ ሳይሆን በአካባቢ ላይ የሚደርስን ከባድ ጫና የምናሽንፍበት መንገድም ጭምር ነው፡፡

**አካባቢ ማለት** ሰዎች በሚኖሩባቸው ዙሪያዎች ያሉ ማናቸውም ነገሮች የሚያጠቃልል ነገር ነው፡፡ የአካባቢ ኃላፊነት በንፁህ አካባቢ ዉስጥ መኖርን ማረጋገጥ ነዉ፡፡

### ተግባር 1.14

ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ እና የታዘባችሁትን ፃፉ፡፡

- አካባቢን መንከባከብ አስፈላጊ ነው?



ምስል 1.5: አካባቢን መንከባከብ እና አለመንከባከብ



ምስል 1.6: የተጠበቀ እና የተበከለ አካባቢ

ግሪኮች እንደሚሉት ማህበረሰብ ሰልጥኗል ወይም አድጓል የሚባለዉ አዋቂዎች ችግኞችን በመትከል ከእነሱ አልፈዉ ለልጅ ልጆቻቸዉ ማሰብ ሲጀምሩ ነዉ።




ምስል 1.7: ዛፎችን የመትከል አስፈላጊነት





## 1.5. የምዕራፉ ማጠቃለያ

ኃላፊነት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት ሰዎች ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ ባይወጡ በሕይወት ዉስጥ ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ነዉ። ማነኛዉም ሰዉ አደርገዋለሁ ያለውን ካላደረገ አንዱ ሌላውን እንዴት ያምናል?

እያንዳንዱ ሰው የራሱንና የአካባቢዉን ንጽህና ካልጠበቀ እንዴት በጤናማ አካባቢ ዉስጥ መኖር እንችላለን? ወላጆች ለልጆቻቸው ተጠያቂ ካልሆኑ እና ልጆችም በበኩላቸዉ ተጠያቂ ካልሆኑ ለምሳሌ የቤት ስራቸው ካልሰሩ ወይም በመኪና መንገድ ላይ ቢጫወቱ ምን ይመስላችኋል?

**ቁልፍ ቃላት፡**

- ኃላፊነት
- ኃላፊነትን መወጣት
- ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ
- ተጠያቂ መሆን
- ቃል-ኪዳን
- ሌሎችን መርዳት
- ሀብትን በአግባቡ መጠቀም
- ንቁ ዜጋ
- ግብር መክፈል
- የትራፊክ ህጎችና ደንቦች

## የማጠቃለያ መልመጃ 1.1

### ትዕዛዝ I:የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እዉነት ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ::

1) ህግን መጣስ በጭራሽ ትክክል አይደለም::

2) ውሸት መናገር ጥሩ ነው::

3) እስክሪብቶ መዋስ እና አለመመለስ ስህተት ነው::

4) ለተቸገሩ ገንዘብ መስጠት የለባችሁም::

5) ማጭበርበር ሁልጊዜ ስህተት ነው::

### ትዕዛዝ II: ከዚህ በታች ያሉትን እያንዳንዱን ታሪክ አንብቡና ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ::

1) ሙሉ የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነች:: ሙሉ ከትምህርት ሰዓት በኋላ ታናሽ እህቷን በትምህርት ቤቷ መውጫበር ላይ ጠብቃ ወደ ቤት ይዛት መሄድ ይጠበቅባታል::የሙሉ ጓደኞች ደግሞ ከሙሉ ጋር ለተወሰኑ ደቂቃዎች አብረዋትመጫዎት ይፈልጋሉ:: ሙሉም ሳታውቀው እህቷ ጋር ሳትሄድላት 30 ደቂቃ አለፈ::

(ሀ) የሙሉ ኃላፊነት ምን ነበር?

(ለ) ተጠያቂዋሙሉ ነበረች?

(ሐ) ድርጊቷ ሊያስከትለውየሚችለዉ አንዳንድት ውጤቶችምንድናቸው?

2) ገመዳ በትምህርት ቤት ሜዳ ከጓደኞቹ ጋር እግር ኳስ ይጫወት ነበር:: እናቱ ለምሳ 6:00 ሰዓት ቤት እንዲደርስ ነግራዋለች:: 5:00 ሰዓት ላይ የገመዳ ጓደኞች 1:00 ሰዓትያህል ብቻ መጫወት ፈለጉ:: ነገር ግን ገመዳ በሰዓቱ ወደ ቤት መሄድ ካልጀመረ በ 6:00ሰዓት ቤቱ እንደማይደርስ ያውቅ ነበርና ወደ ቤቱ አመራ::

(ሀ) የገመዳ ኃላፊነት ምን ነበር?

(ለ) ተጠያቂው እሱ ነበር?

(ሐ) ድርጊቶቹ ሊያስከትሉ የሚችሉት አንዳንድ ውጤቶች ምንድናቸው?

3) ሂሩት እሁድ አያቷን በጓሮ የአትክልት ሥራትረዳለች ተብሎ ይጠበቃል::ቀኑ ዝናባማ በመሆኑ መሄድ አትፈልግም ነገር ግን አያቷን ማገዝ እንዳለባትታውቃለች:: ሂሩት የዝናብ ካፖርትዋን እና ቦት ጫማዋን ለብሳ አያቷን ለማገዝ ወጣች::





(ሀ) የሂሩት ኃላፊነት ምን ነበር?

(ለ) ኃላፊነት ነበረባት?

(ሐ) ድርጊቷ ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጤቶችምንድናቸው?

4) ኤክራም ለልደትዋ አዲስ ብስክሌት ተሰጣት እና ወላጆቿ በአግባቡ ይዛ እንድትጠቀምበት ይፈልጋሉ ::ኤክራም ብስክሌቷን ከአባቷ መኪና ጀርባ ባለው የመኪና መዉጫ ላይ አስቀምጣቁርስ ልትበላ ወደ ቤትሮጣ ገባች:: የኤክራም አባት በፍጥነት እየወጣ ነበርና ብስክሌቱን ባለማየቱበመኪናዉ ወጥቶበት ተሰባበረ::

(ሀ) የኤክራም ኃላፊነት ምን ነበር?

(ለ) ተጠያቂው እሱ ነበር?

(ሐ) ድርጊቶቹ ሊያስከትሉ የሚችሉት አንዳንድ ውጤቶች ምንድናቸው?

### ትዕዛዝ III: ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛዉን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ::

1) በፍፁም መዋሸት የለብህም ወይም ሁልጊዜም እውነትን ተናገር ምክንያቱም-------------------

(ሀ) ሐቀኛ ሰው መሆን አስፈላጊ ነው::

(ለ) ውሸት ወደ ችግር ውስጥ ሊያስገባህ ይችላል ወይም ሐቀኛ ስትሆን ሰዎች ይወዱሃል::

(ሐ) መዋሸት ስህተት ነው እና እውነትን የመናገር ግዴታ አለብህ::

(መ) ሁሉም::

2) በፍጹም መስረቅ የለብህም ምክንያቱም……………………………………………………..……..

(ሀ) ከሰረቅክ ታማኝ አደለህም ወይም ስግብግብ ሰው ነህ::

(ለ) ከተያዝክ እንደ መታሰር ያሉ መዘዝ ሊያጋጥምህ ይችላል::

(ሐ) መስረቅ መጥፎ ነው እና ማንም የሌላውን ሰው ንብረት ለመውሰድ መብት የለውም::

(መ) ሁሉም::

3) ማካፈል ጥሩ ነው ምክንያቱም…………………………………………..………………..….

(ሀ) ካጋራህ ለጋስ ሰው ነህ እና ለጋስ መሆን ጥሩ ነው::

(ለ) ብታካፍል ሌሎችም ያካፍሉሃል::

(ሐ) ማጋራት ሲባል ለጋስ እና ደግሰው ማለት ነዉ እነዚህም መልካም ባሕርያት ናቸው::

(መ) ሁሉም::

# ምዕራፍ ሁለት

# ጠንካራ የስራ ባህል

**መግቢያ**

ከዚህ በፊት በነበረዉምዕራፍ ውስጥ ስለ ኃላፊነት ትርጉም ፣ አስፈላጊነት እና ዓይነቶች ተምራችኋል።በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለ ጠንካራየስራ ባህልአስፈላጊነት፣የንባብ ባህል ፣ የማንበብ ክህሎትን ለማዳበር የሚረዱ ስልቶች ትማራላችሁ።

**የመማር ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-**

- ጠንካራ የስራ ባህልን ጽንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ።
- ጠንካራ የስራ ባህል አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ታስገባላችሁ።
- የታታሪ ሰራተኛ ባህሪያትን ትዘረዝራላችሁ።
- የንባብ ልምድን እና ስልቶቹን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ታሳያላችሁ።
- ስራችሁንእንዴትበብቃት  ማቀድ እንደምትችሉ ታሳያላችሁ።





## 2.1 ጠንካራ የስራ ባህል

**ጠንካራ የስራ ባህል ምንድን ነው?**

ጠንካራ የስራ ባህልን ስንመለከት ሁለት ወሳኝ ሀሳቦችን በአጭሩ ማብራራት ያስፈልጋል። እነዚህም ባህል እና ታታሪነት ናቸዉ።ባህል ማለት ግለሰባዊና ማህበራዊ አሰራሮችን ለመምራት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ የማህበራዊ ቡድን መንፈሳዊናቁሳዊ አካላት ስብስብ ነዉ። ይህም ቋንቋን፣ ልምድን፣ወግን፣የአኗኗር መንገድን ፣እሴትን፣እዉቀትን የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

ባህል ሰፊ ጽንሰ-ሀሳብየያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ሰዉ የራሱ የሆነ ባህል ያለዉና በዚህም ራሱንና ሌሎችን የሚያይበት ዓለም ነዉ። ባህል ባህሪያችንና እምነታችንን ለመያዝ ትልቅ ሚና አለዉ። ባህል በመዝገበ ቃላት ትርጉም መሰረት በማህረሰብ ዉስጥ የሚተላለፍ አጠቃላይ ባህሪ፣እምነት፣ጥበብ፣ ተቋም/ስሪት፣አስተሳሰብና የመሳሰሉት እንደሚያጠቃልል ያሳያል።

ሌላው ማብራሪያ የሚያስፈልገው ቃል ታታሪነት ወይም ጠንክሮ መሥራት ነው። ጠንክሮ መሥራት ወይም ታታሪነት ማለት ጊዜና ጉልበትን ለአንድ የተወሰነ ስራ ወይም ተግባር በመደበኛነት ማዋል ማለት ነው።ሥራ የማህበራዊ እውነታና የሕይወት መሰረት ነዉ።




ምስል 2.1፡ የታታሪ ሰዎች ሥዕል

በትጋት መስራት እና በባህል መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

በዓለም ላይ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ለምንድን ነው ከሌሎች በበለጠ በፍጥነት የሚያድጉት? ለምን አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ያላደጉ እና ኋላ ቀር ሆኑ? ለምሳሌ ቻይናዉያን በፍጥነት ያደጉት በጠንካራ የስራ ባህላቸዉ ነዉ።



ምስል 2.2: ታታሪሰዎች

ስለዚህ ባህልበትጋት ወይም በታታሪነት ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

የምንፈልገው ስራ እና የሚያጠነክረን የስራ ባህል!

ስኬት በመታደል ነው ወይስ ጠንክሮ በመሥራት? አንዳንድ ታዋቂ ሰዎች እንደሚሉት ጠንክሮ መሥራት ዕድልን ያመጣል፡፡ለምሳሌ፡ቶማስ ጄፈርሰን እንዳሉት “በሰራሁ ቁጥር ብዙ ዕድል ያለኝ ይመስለኛል” (የቶማስ ጄፈርሰን ጥቅሶችን ተመልከቱ) እና ጄኔራል ኮሊንፓ ውል እንዳሉት " ለስኬት ምንም ሚስጥሮች የሉትም፡፡ስኬት የዝግጅት፣የልፋት፣ከውድቀት የመማር ውጤት ነው፡፡" ስለዚህ አንድ ሰዉ ጥገኛ መሆን ያለበት ትጋት ላይ እንጂ እድል ላይ መሆን የለበትም፡፡

**ተግባር 2.1**

1) አንዳንድ የኢትዮጵያዉያንን የስራ ባህልን ዘርዝሩ፡፡

2) በአካባቢያችሁ ለየት ያሉ የስራ ባህሎች የትኞቹ ናቸው?

3) በባህልና በታታሪነት መካከል ያለውን ትስስር እንዴት ታዩታላችሁ?

4)በየትኛዉ ነዉ የምታምኑት ጠንክሮ በመስራት ወይስ በዕድል? ለምን?

## 2.2 ጠንካራ የስራ ባህል አስፈላጊነት

ጠንክሮ መሥራት መልሶ ዋጋ ይከፍላል! ሁልጊዜምጠንክራችሁ ማንበባችሁንናማጥናታችሁንቀጥሉ እንዲሁም ራሳችሁን መንከባከባችሁን ለአፍታም ቢሆን አትዘንጉ ብዙም ሳይቆይ ድካማችሁ ሁሉ ፍሬያማ ይሆናል! የዛሬ ድካማችሁ ለነገ መልካም እረፍታችሁ ነዉ! ይህ ለተማሪዎች እና ለወጣቶች የተጠቆመ የተነሳሽነት መልዕክት ነው፡፡ሰዎች ለህልማቸው ስኬት ጠንክረው እንዲሰሩ የሚያበረታታ ነዉ፡፡

እናንተስእንደ አምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ዉጭ ምን ዓይነት ሥራ መሥራት ይጠበቅባችኋል?

በትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የሥራ ባህል እና በሥራ ዓለም ላይ ያለው የሥራ ባህል ልዩነት አለው፡፡በሥራ ዓለም እና በትምህርት ቤት መካከል ያለው ዋናዉ ልዩነት በትምህርት ቤት ውስጥ ያለው ጥረት ተማሪዉን ብቻ የሚመለከት ሲሆንለምሳሌ ተማሪዉ ጠንክሮ ባይሰራ ዋነኛዉ ተጎጂ ራሱ ሲሆን በስራው አለም ላይ ግን የአንድ ግልሰብ ጠንክሮ አለመስራት ወይም ስህተቶች በሌሎች ሰዎች ላይም ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

እኛ ኢትዮጵያዉያን በታሪካችን ዉስጥ ጠንካራ የስራ ባህል እንዳለን ይታወቃል፡፡ ይህ ጠቃሚ እሴታችን በነፃነትእንድንኖር፣ የአገር ፍቅር ስሜት እንዲኖረን፣ ብዝሃነት ተቀብለን እንድንኖር እና



የግብረ ገብ ትምህርት

የመሳሰሉትን በማሳካት ረገድ ትልቅ የጀርባ አጥንት ሆኖ ጠቅሞናል፡፡ ነገር ግን ይህ እሴታችን አሁን አሁን እየተዘነጋና ትኩረት እያጣ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ “የሰዉ-ልጅ መገኛ” ተብላ ትጠራለች፤ ይህቺ በታሪክ ቀደምት የሆነች ሀገር የአክሱምንሀውልት፣የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣የጎንደርን ግንብ፣ የኮንሶን እርከን፣የሀረር ጀጎል እና ሌሎችንም አስደናቂ ታሪካዊ ቅርሶችን መስራት የቻሉ ኢትዮጵያውያን የነበሩ ቢሆንም አሁን ላይ ያለዉ ትዉልድ ግን ይህንን ማስቀጠል አልቻለም፡፡ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቱ ያለዉ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ቢሆንም በደካማ የስራ ባህል ምክንያት ሁሉም እኩል ተጠቃሚ አልሆነም፡፡

የዛሬ ወጣቶች እና ጎልማሶች አገራቸው ዛሬ ካለችበት ኋላቀርነት እንድ ትላቀቅ ለማድረግ ጠንክራ የሥራ ባህልን ማዳበር ተቀዳሚ ተግባራቸዉ መሆን አለበት፡፡



ምስል 2.3፡ የኢትዮጵያውያን ጠንካራ የስራ ባህል

በአጠቃላይ ጠንክሮ የመስራት ባህል ድህነትን ለማጥፋት እና በፍጥነት ለማደግ ያስችለናል፡፡ ይህም የሀገሪቱን የሰው ሀብትና የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም ያስችለናል፡፡

**ተግባር 2.2**

1) ጠንካራ የሥራ ባህልለምን አስፈለገ?

2) በትጋት በመስራት ታምናላችሁ?

3) የስራባህላችንንእንዴትታዩታላችሁ?

4) በአካባቢያችሁያሉየጠንካራ ስራ ባህል መገለጫዎችምን ምንናቸው?

## 2.3 የታታሪ ሰራተኛ ባህሪያት

**ትምህርታችሁን ጠንክራችሁ ታጠናላችሁ? መልሳችሁ አዎከሆነ የዚህ መገለጫዎቹ ምንድንናቸው?**

እያንዳንዱ ተማሪ ጎበዝ ወይም ታታሪ የመሆን አቅም አለው፡፡ይህንን ለማድረግና ለመጀመር ተማሪዎች ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ በሰዓቱ ትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና መከታተል እንዲሁም መምህሩ የሚሰጠውን ስራ በተሰጠዉ ጊዜ ሰርቶ ማስረከብ፤ትኩረታቸዉንም በትምህርታቸዉ ላይ ብቻ በማድረግ እና ያልገባቸዉንም ጥያቄዎች በመጠየቅ ታታሪነታቸዉን ማሳየት ይችላሉ፡፡

ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች የተሰጣቸዉን ተጨማሪ ተግባር በጋራ በማጥናትና በመስራት ቀድመዉ በማጠናቀቅ የተሻለ ዉጤት ማስመዝገብ ይችላሉ፡፡



ምስል 2.5: የቡድን ጥናት

**ታታሪ ተማሪ ማነው? አንተ/ቺ ታታሪ ተማሪነህ/ሽ?**

ታታሪ ተማሪ ለትምህርቱ ስኬት አስተዋፅዖ ያላቸውን ባህሪያት ያንጸባርቃል፡፡እንደዚህ አይነት ተማሪ የመማር ሂደቱን የበለጠ ለማጠናከር ሌሎችን በማገዝና እሱምከሌሎች የተሻለዉን በመውሰድ፣ትምህርት ቤቱ የሚያቀርባቸው እድሎች በመጠቀም እና ጠንክሮ በመሥራት የጎበዝ ተማሪነትን ባህሪያት ያሳያል፡፡ ያለዉ የተፈጥሮ እውቀት ምንም ይሁን ምን እውነታዎችን እና ክህሎትን የመማር እና የመተግበር አቅሙን ለማሻሻል ሁለጊዜም ጥረት ያደርጋል፡፡ጎበዝ ተማሪ በባህሪው ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች በደንብ ይገነዘባል እናም እነዚህን ለማሻሻል መንገዶችን ይፈልጋል፡፡ፈጣንየሆነ ጥረት በማድረግ በመጨረሻም ለጥሩ ውጤት ይበቃል፡፡ በሌላ አባባል ትጉህ ወይም ታታሪ ተማሪ በትምህርት ህይወቱ ስኬታማ የመሆን እድል አለው፡፡

በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ያሳዩትን ትጋት ለወደፊት ህይወታቸዉጥሩ የሥራላይ ሥነ-ምግባርንናጠንካራየስራ ባህል ይሆናቸዋል፡፡



የግብረ ገብ ትምህርት

ጠንካራ የስራ ባህልን መልመድ ለምን ይጠቅማል?

ልጅን እንዴት ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት ማስተማር እንደበደል ሊወሰድ ይችላልን?

ባህላችን የልጆችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚረዱ ብዙ አስደናቂ እድገቶችን አድርጓል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ቤተሰቦች ለልጆቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ላያሟሉ ይችላሉ፡፡ስለሆነም ወላጆች ይህንን ለልጆቻቸዉ በጊዜ ሂደት ሊሳካ እንደሚችል ማስተማርና ማስገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

አንድን ልጅ እንዲሠራ ማስተማር መጉዳት አይደለም፡፡ልጆችን ስራ የምናለማምዳቸዉ ለጥቅማችን ሳይሆን እንዴት መስራት እንዳለባቸዉ እንዲማሩና ጥሩ የስራ ባህልን እንዲያዳብሩ ለመርዳት ነዉ፡፡ስለዚህ ልጆችን ስራ ማስተማርና ማለማመድ የልጆች ጉልበት ብዝበዛ ሳይሆን ለወደፊቱ አዎንታዊ የሆነ ጠንካራ የስራ ባህልንና እሴትን ይዘዉ እንዲያድጉ ለመርዳት ነዉ፡፡ ዛሬ ላይ የምትሰራዉ ስራ ጥቅሙ ለአንተ/ቺ ነው፡፡ ልጆች ከእድሜያቸዉ ጋርአብሮ የሚሄድ ስራ ቢሰጣቸዉ የሚሰሩት በደስታ ነዉ፡፡ ለስራ የምንሰጠዉ ዋጋ በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡

ልጅን በሚገባው ጊዜና መንገድ አስተምረው ወይም አስጀምረዉ እንደሚባለው!

ልጆች ጠንክሮ መሥራትን ከለጋነት ዕድሜያቸው ጀምረው ከለመዱ በቀሪው የሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ጠቃሚ ልምድ ወይም ባህል ሆኖ ውጤታማ ያደርጋቸዋል፡፡

ከዚህ በታች የተቀመጡት መገለጫዎች ታታሪ ተማሪዎች የሚያደርጓቸውና መምህራኖቻቸውም ማየት የሚፈልጓቸው ተግባራት ናቸው፡፡

ታታሪ የሆኑ ተማሪዎች፡-

1) በመደበኛነት ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፤በሰዓቱም ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ፡፡
2) በድንገት ያመለጧቸው ማስታወሻዎች ወይም ሌሎች ስራዎች ካሉ ከሌሎች ተማሪዎች ወይም ከመምህራቸው ላይ ይፅፋሉ ወይም ይወስዳሉ፡፡
3) የቤት ስራቸውን በሰዓቱ ያጠናቅቃሉ፡፡
4) በክፍል ውስጥ ለሚሰጥ ትምህርት ትኩረት ይሰጣሉ፤ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፤በክፍል ውይይቶች ይሳተፋሉ፡፡
5) ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በልዩ ልዩ ክበባት ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡
6) ከክፍል ውጭ ከመምህራቸው ጋር በመገናኘት ትርጉም ያለው ውይይት ለማድረግ ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡
7) በመማርሂደትውስጥንቁተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

8) በክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት ለማጠናከር ከመደበኛው ክፍል ውጪ ያጠናሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የታታሪ ተማሪ መገለጫዎች ዉስጥ በምን ያህሉቹ ላይ ትስማማላችሁ?

### ተግባር 2.3

1) የታታሪ ተማሪዎች ዋና ዋና ባህሪያት ምንድን ናቸው?

2) ስለ ህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምን ታውቃላችሁ?

3)በልጆች ላይ ከሚደርስ ጥቃትስ የሚለየው በምንድን ነው?

3) ከእድሜያችሁ አንፃር ለ እናንተ ተገቢ የምትሏቸው ስራዎችምን ምን ናቸው?

## 2.4 የንባብ ባህል

**ንባብ ምንድነው?**

መምህራን ተማሪዎቻቸው ቋንቋን አቀላጥፈው እንዲናገሩና እንዲፅፉ እንዲሁም የተሰጠን ፅሁፍ አንብበው እንዲረዱ ለማስቻል የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡እነዚህም የቋንቋ ክህሎቶች ይባላሉ (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ) ናቸው፡፡ንባብ ከቋንቋ ችሎታዎች መካከልአንዱ ነው፡፡

ብሬንስ (1998፣ 2) እንዲህይላል፡- "ንባብ  በአንባቢውእናበሚነበበው ፅሁፍ መካከል የሚካሄድ የተግባቦት ሂደት ሲሆን ውጤቱም መረዳት ይሆናል፡፡"

ንባብና የሚነበበው የጽሑፉ አይነት ዓላማው ልዩ እውቀትን፣ችሎታን እና የማንበብ ግንዛቤን ለማግኘት አንባቢው የተለያዩ ስልቶችን የሚጠቀም ይሆናል፡፡ምክንያቱም አንብቦ የመረዳት ግንዛቤ ትርጉም ከመስጠትም በላይ ነው፡፡ይህም አንባቢው የትኛውን የንባብ ክህሎት በየትኛው የንባብ ስልት ቢጠቀም ፅሁፉን በሚገባ ሊረዳውና የተነሳበትን ዓላማ ለማሳካት ስለሚያግዘው ነው፡፡

ማንበብ አንድ ሰው በህይወቱ ውስጥ ማዳበር ያለበት በጣም ጠቃሚ ልምድ ነው፡፡ ማንበብ ቋንቋንና የቃላት አጠቃቀም ክህሎትን ያዳብራል፡፡በተጨማሪም መጽሃፍትን ማንበብ ዘና ለማለት እና ጭንቀትን ለመቀነስ ጠቃሚ መፍትሄ ነው፡፡ጥሩ መጽሃፍትን በየቀኑ ቢያንስ ለጥቂት ደቂቃዎች ማንበብ የአዕምሮ ጡንቻዎችን ለማሳሳብና ለጤና አስፈላጊ ነው፡፡

- እስከ አሁን ድረስ ስንት መጽሃፍትን አንብበ ሀል/ሻል?
- የመማሪያ መጽሃፍህን /ሽን ዘወትር ታነባለህ/ታነቢያለሽ ?የትኛውን/የትኞቹን?







ምስል 2.6 በቤት ውስጥ የምታጠና ሴት ልጅ

ማንበብ ሰውን አዋቂ ያደርጋል ከዚህም በላይ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው የማንበብ ልምዱን እንዴት ያዳብራል?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መንገዶች የንባብ ልምድን ለማዳበር የሚያግዙ ናቸው፡፡

1) በየቀኑ ለማንበብ ጊዜ መድቡ፤ከሚኖራችሁጊዜ ከ5-10 ደቂቃዎች ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገርግን በቀን ዉስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ መፅሐፍ በመግለጥ የማንበብ ልምድን ለማዳበር ሞክሩ፡፡ለምሳሌ ሲመገቡ ወይም ሻይ ሲጠጡ ወይም ከመኝታ በፊት የማንበብ ልምድን ማዳበር ጥሩ መንገድ ነው፡፡ በየቀኑ በተመሳሳይ ጊዜ ስናነብ አእምሮአችን ያንን ጊዜ እንደ "የንባብጊዜ" በመውሰድ ልምድ ማድረግይጀምራል፡፡

በቀን 4 ጊዜለ 10 ደቂቃዎች ብቻ በመቀመጥ ብታነቡ፣በየቀኑለ 40 ደቂቃ ያህል ማንበብ ቻላችሁ ማለት ነው፡፡

2) ደስ የሚላችሁን መጽሐፍት አንብቡ፤በምታነቡት መጽሐፍ ካልተደሰታችሁ ንባባችሁ እንደ ቤት ውስጥ ሥራ አሰልቺ ይሆንባችኋል ነገርግን የምትወዱትን መፅሀፍ ስታነቡ በጉዳዩ ውስጥ ትገባላችሁ፤ሀሳቡንም ስለምትወዱት መጽሐፉን ማስቀመጥ አትፈልጉም እናም ማንበብ አስደሳች ይሆንላችኋል፡፡

- የምትፈልጉትን  መጽሐፍት ዓይነት ለማግኘት የጓደኞቻችሁን፣የቤተሰባችሁን ወይም የቤተ-መጽሐፍት ባለሙያዎችን አማክሩ፡፡
- መጽሐፉ በእርግጥ የእናንተን ትኩረት የማይስብ ከሆነ የመጀመሪያው ምዕራፍ ወይም የተወሰኑ ገፆችን ብቻ አንብባችሁ መተው ችግርየለውም፡፡

3) በሁሉም ቦታ መፅሐፍትን ይዛችሁ ተንቀሳቀሱ፡፡አሁን ባለንበት ዓለም መጽሐፍት በስልክ ወይም በትንሽ ነገር ላይ ስለሚያዝ የመጽሐፍቱ መጠን እና ክብደት ችግር አይሆንም፤በጉዞላይ

ሆነንም ለማንበብ አንቸገርም።ስለዚህ ሁልጊዜ መጽሐፍት ከእጃችን ስለ ማይለይ በቀን ውስጥ ባለን በማንኛውም ነፃ ወይም ትርፍ ጊዜ ማንበብ እንችላለን።

4) የመጽሐፍት ክበብና የንባብ ቡድን አባል በመሆን የተወሰነ ኃላፊነትን በመውሰድ  በንባብ ላይ በመሳተፍ ልምድ ማዳበር ይቻላል።አለበለዚያም አንተ/ቺከጓደኞችህ/ሽ ጋር በመሆን የራስህን/ሽን ክበብ መጀመር ትችላለህ/ሽ። መጽሃፎቹን በየወሩ መጨረስና መወያየት አስፈላጊ ነው። እንደየ ፍላጎታችሁ የምትቀላቀሉትን ክበብ አስቡ። ለምሳሌ ምናባዊ መጽሐፍትን ከወደዳችሁ ምናባዊ መጽሐፍ ቡድንን ተቀላቀሉ።አንዳንድ ጊዜ በአካል ተገናኝቶ ማንበብ የማትችሉ ከሆነ ወይም ካልፈለጋችሁ ማህበራዊ ድረ ገፆች በመጠቀም መቀላቀልና ማንበብ ትችላላችሁ።

በአጠቃላይ የንባብ ልምድ በህይወት ውስጥ ትልቅ መዋዕለንዋይ ነው።

አንድ ሰው በህይወቱ ውስጥ ማዳበር ከሚገባው ምርጥ ልምድ አንዱ የንባብ ባህል ነው።ምክንያቱም

ሰው ያነበበውን ይሆናል ይባላልና!

መጽሐፍት በእያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ባለው ትውልድ ውስጥ ማንበብ ለብዙዎቻችን ተወዳጅ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ነበር።ይሁን እንጂ በሚያሳዝን ሁኔታ አሁን ላይ መጽሐፍትን የሚያነብ ሰው ቁጥር በጣም እየቀነሰ ነው።የዛሬዎቹ ልጆች አሁን ላይ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለንባብ ሳይሆን በዘመናዊ ስልኮችና ኮምፒተሮች ላይ ያሉ ጨዋታዎችን (ጌሞችን) በመጫወት ነው። ወላጆች በለጋ ዕድሜ ላይ ያሉትን ልጆቻቸውን በመርዳት መጻሕፍትን የማንበብ ልምድ እንዲያዳብሩ ማለማመድ ይኖርባቸዋል።

መጽሐፍትን በምናነብበትጊዜ በቋንቋው ውስጥያሉትን ያልተለመዱ ወይም አዳዲስ ቃላትን ለመተዋወቅ ከሁሉ የተሻለ እድል እናገኛለን።በልጅነት ጊዜ የንባብ ልምድን ማዳበር አዳዲስ ቃላትን ለመማር ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ንግግራቸው ውስጥ እነዚህን ቃላት በመጠቀም ሀሳባቸውን በተለያዩ መንገዶችለመግለፅ ይረዳቸዋል።

በአጭሩ ማንበብ የህይወት ክህሎት ነው።በሕይወታችን ላይ ሙሉ ትርፍ የምናገኝት መዋዕለ-ንዋይ ነው።ስለዚህ የማንበብ ደስታን ወደ ሕይወታችሁ በማምጣት ማንበብን አስደሳች አድርጉት።

**ተግባር 2.4**

1) የንበብ ባህልን ለማዳበር የምንጠቀማቸው ዘዴዎች ምንምን ናቸው?

2) የንበብ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

3) ገና በልጅነትህ /ሽ የንባብ ልምድ የምታሳድገው/ጊው እንዴት ነው?





## 2.5 የንበብ ክህሎቶችን ለማዳበር የሚረዱ ስልቶች

ተማሪው የተሻለ የንባብ ስልቶችን ሲለይና ሲጠቀም በጣም ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲያነብ ይረዳዋል።እነዚህን ስልቶች በመጠቀም ተማሪ ውበትንሽ ጥረት ከፍተኛውን የንባብ ጥቅም ለማግኘት ይችላል።

በርካታ ምርምሮች ስለተለያዩ የንባብ ዓይነቶችና ለመማር ስለሚያግዙ የንባብስልቶች ይገልፃሉ።

ንባብን ለመማር ከምንጠቀምባቸው ስልቶች መካከል፡-

### 2.5.1 ዓላማ ያለው ንባብ

እንደዚህ የማንበብ ዝንባሌ ካለህ/ሽ “ምዕራፍ 2ን ማንበብ እፈልጋለሁ - ይሄው! …”የንባብ ስልትህን/ሽን እንደገና ማሰብት ችላለህ/ትቺያለሽ።በተለይም የንባቡን ዓላማ ማግኘት ያስፈልጋል።

ከምንባቡ ውስጥ በትክክል ስለምትፈልጉት ነገር በጣም ግልፅ ሁኑ። ያየንባባችሁ ዓላማነው፡፡ ከምንፈልገው ዓላማ ውጪ ማንበቡ ዓላማ-ቢስ ሊያደርገን ይችላል። ምናልባት ለጥያቄዎች መልስይፈልጉ ይሆናል፣የአንድ ርዕስ ወይም ጉዳይ አጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘት ይፈልጉ ይሆናል፣ዝርዝር እውቀትን፣የተለያዩ አመለካከቶችን፣የጸሐፊውን አቋም መለየትን፣የጸሐፊውን አቋም መገምገምን፣አቋምህን የሚደግፉ ክርክሮችን፣አቋምህን የሚቃወሙ ክርክሮችን፣ምሳሌዎችን፣አሀዛዊ መረጃዎችን፣ፍቺዎችን፣ማብራሪያዎችን፣ጥቅሶችን፣ወዘተየምናነብበት ዓላማ ሊሆን ይችላል።ስለዚህ ስናነብለምን ዓላማ እንደሆነ ከለየን ትኩረታችን በዓላማችን ላይ ስለሚሆን በፍጥነት  እየመረጥን ለማንበብ ይረዳናል።

### 2.5.2 መቃኘት /የዳሰሳ ንባብ/ scanning

መቃኘት ልዩ ወይንም የተወሰነ መረጃን ብቻ ለመፈለግ ሲባል በፍጥነት ማንበብ ነው።ለምሳሌ የቴሌቪዥን መመሪያን ወይም የምንፈልገውን ሰው ስልክ ስንመርጥ የምናነበው ዓይነት ነው።በመቃኘት ስናነብ በደቂቃ እስከ 1,500 ቃላትን ማንበብ ያስችለናል።በመቃኘት የምናነብበት አንዱ ምክንያት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የምናገኘው ቁልፍ ቃላትን ትኩረት ለማድረግ ስንፈልግነው።

### 2.5.3 የአሰሳ ንባብ/Skimming

የአሰሳ ንባብ የጽሁፉን አጠቃላይ ሀሳብን ለማግኘት ሲባል በፍጥነት ማንበብ ነው።በዚህም እስከ 1000 ቃላትን ለማንበብ ያስችላል።ይህ ዓይነቱ አነባበብ የጀመርነው ንንባብ ለመቀጠል ወይም ላለመቀጠል ለመወሰን ይረዳናል።በፅሁፍ ውስጥ የቱን ቦታ በጥንቃቄ ማንበብ እንዳለብንና ከየት መጀመርም እንዳለብን አለበለዚያ መጽሐፍን ወዲያውኑ መዝለል ካለብንም ለመወሰን ይረዳናል፡፡ የአሰሳ ንባብ እንደ ዳሰሳ ንባብ እያንዳንዱን ቃል ማንበብ አያስፈልግም።በዚህ መንገድ ስናነብ ለጽሑፉ ያለንን ፍላጎት ከፍ ለማድረግ ይረዳል።በዚህም መሰረት የሚከተሉትን ልናይ እንችላለን።

- አርዕስት
- ንዑስ አርዕስት
- ምልክት የተደረገባቸው ቃላት፣በደማቅ የተፃፉ፣በሰያፍ የተፃፉ ወይም የተሰመረባቸው
- ሥዕላዊ መግለጫዎች
- የሪፖርት ማጠቃለያ፣መግቢያ ወይም መደምደሚያ
- የእያንዳንዱ አንቀጽ የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር
- የምዕራፉ ጥያቄዎች
- የምዕራፉ ዓላማዎች
- የምዕራፉ ማጠቃለያዎች

### 2.5.4 የመረጃ ቃላት

አንዳንድ ጊዜ ጽሑፍን የምናነብበት መንገድ የተለየ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ከዚህ በላይ የተገለፁትን ፅሁፎች በተመሳሳይ መንገድ አናነብም። አንዳንዶቹ የገፅታ ንባብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ነገር ግን አሁንም ቢሆን በፍጥነት ማንበብ ያስፈልጋል።በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በአማካይከ 50% የማይበልጡብቻ "መረጃ"ቃላት መሆናቸውን ማስታወስ ጠቃሚ ነው።ከዚህ ውጭ ያሉት ሌሎችቃላት እንደማያያዣ ሆነውና ዓረፍተ ነገርን አስተካክለው ወይም አሳምረው ለማቅረብ ያገለግላሉ እንጂ ለትርጉም አስፈላጊ አይደሉም።

ስናነብ በመረጃ ቃላት ላይ ማተኮር በፍጥነት ለማንበብ ከመርዳቱም በላይ ስላነበብነው ፅሁፍ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን ያስችለናል። ነገር ግንተማሪዎች "ጠቃሚ መረጃ" ቃላትን መምረጥ እንዴት ይማራሉ?

ለዚህ ጥሩ መንገድ ደራሲው ለማለት የፈለገውን ሀሳብ ወይም መልእክት ማግኘት ነው።ይህን ስናደርግ የመረጃ ቃላቶቹን ማግኘት እንችላለን።

### 2.5.5 የሀረግ ንባብ

አንድን ፅሁፍ እያነበበ ያለ የጓደኛህን ወይም የቤተሰብህን አባል አይን ተመልከት። በእያንዳንዱ መስመር ላይ ያለውን የአይን እንቅስቃሴ እንዴት እንደሆነ ስታይ የት ላይ ቆም እንደሚል ታያለህ። ይህም ማስተካከያ ይባላልዓይናችን ቃላት የሚወስዱት በዚሁ በማስተካከል ጊዜ ነው።ደካማ አንባቢዎች በእያንዳንዱ ማስተካከያ ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ቃላት ብቻ ይወስዳሉ።ይህም የንባብ ፍጥነታቸውን ይቀንሰዋል።በሌላ በኩል ጎበዝ አንባቢዎች በእያንዳንዱ ማስተካከያ ጊዜ በርካታ ቃላት ይወስዳሉ





ይህም የተሻለ አንባቢያ ደርጋቸዋል።

በዚህ የተነሳ የደካማ አንባቢ ዓይኖች ጥቂት ቃላት ላይ በአንዴ ሲያርፍ በሌላ በኩል የጥሩ አንባቢ ዓይኖች ግን በርካታ ቃላትን በአንድ ጊዜ በመመልከት የተሻለ ያነባሉ።

#### ተግባር 2.5

በተሰመረባቸው ቃላት ላይ ብቻ በማተኮር ከታች ያሉትን ሁለቱን ዓረፍተ ነገሮች አንብቡ።

<u>ዛሬ</u> ከሌላው ቀን የበለጠ ንባብን <u>አቀላጥፎ</u> <u>ለማንበብ</u> የምትችሉበት <u>አስፈላጊ</u> ጊዜ ነው። <u>ለምሳሌ</u> <u>የመኪና አሽከርካሪ</u> ከሆነክ/ሽ ብዙ <u>የመንገድ ዳር ምልክቶችን ማንበብ</u> መቻል አለብህ/ሽ።

1) ሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች በዋናነት ስለ ምንድን ናቸው?

- ማንበብ።
- መጻፍ
- መንዳት

2) የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር የሚያሟላው የትኛው ቃል ነው? ማንበብ ........

- በቀስታ
- በፍጥነት
- አቀላጥፎ

3) በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሰው የየትኛው የጽሑፍ ምሳሌ ነው?

- የማመልከቻ ቅጾች
- የመንገድ ምልክቶች
- ማስታወቂያዎች

ስሞች እና ግሦች ትኩረት ከሚደረግባቸው ቁልፍ ቃላት መካከል ናቸው።

### 2.5.6 ጽሑፍ ላይ ምልክት ማድረግ

የምታነበው ጽሑፍ የራስህ ቅጂ ከሆነ ቁልፍ ወይም ወሳኝ ቃላት ስር ማስመር፣ማድመቅ ወይም በህዳጉ ላይ ማስታወሻዎችን መፃፍ ትችላለህ/ትችያለሽ፡፡የጽሑፉ ባለቤት ካልሆንክ/ሽ ግን በቀላሉ የሚጠፉ ምልክቶችን ጽሑፍ ላይ ማድረግ የምትችል/ይ ሲሆን ይህም በንባብ ጊዜ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በማተኮር ቁልፍ ነጥቦችን ለመለየት ይረዳል፡፡ለፈተና ለመከለስና እንደገና ለመጠቀም ይጠቅማል፡፡

### 2.5.7 ማስታወሻ መውሰድ

ማስታወሻ በደንብ መውሰድ የማትችሉ ከሆነ ወይም ጨርሶ ያልሞከራችሁ ከሆነ ይህ አሁን ያላችሁበት የክፍል ደረጃ ጥሩ ማስታወሻ መውሰድን የምትለምዱበት፣ጠለቅ ያለ ግንዛቤንና ማሰላሰልን የምትማሩበት፣ የተሻለ ችሎታን የምታዳብሩበት፣ጥሩ የፈተና ዝግጅት የምታደርጉበት ጊዜነው፡፡

### 2.5.8 ከሌሎች ጋርማንበብ

“የጥናት ጓደኛ” ወይም የጥናት ቡድን አግኙ፤በምትፈልጉት ነጥብ ላይ ትኩረት በማድረግ፣ማስታወሻዎችን በጋራ በመያዝ፣ሀሳቦችን በመለዋወጥና በመጠያየቅ ማስታወሻ የመያዝ ችሎታችሁንና የንባብ ልምዳችሁን አዳብሩ፡፡

**ለውጤታማ ንባብ፡-አጠቃላይ ምክረ-ሀሳቦች**

1) የትእንደምታነቡ አስቡበት፡፡ሁልጊዜ ስናነብ በደንብ ብርሃን ያለበትና ትኩረትን የማይከፋፍል ጸጥ ያለቦታ ይሁን፡፡በአልጋ ላይ ሆኖ የማንበብ ልምድ አይኑራችሁ! (መተኛት ካልፈለጋችሁ በስተቀር)

2) በምታነቡበት ጊዜ ድምጽ አታሰሙ ይህ ፍጥነትን ይቀንሳል፤ትኩረትን ይከፋፍላል፤ ወደ መጥፎ የንባብ ልምድ ይወስዳል፡፡

3) ትኩረት ማድረግ በምትችሉበት ጊዜ አንብቡ፤ ስታነቡ እንዳይሰለቻችሁ በየ 30 ወይም 45 ደቂቃ አጭር እረፍት አድርጉ፡፡

4) ለማንበብ ያቀዳችሁትን መጠን ራሳችሁ ወስኑ፡፡ (10 ገጾች፤ 1 ምዕራፍ፤የምዕራፍ 1 ክፍል፤ወዘተ)

5) ማንበብ ብዙውን ጊዜ ከምትጠብቁት ጊዜ በላይ እንደ ሚወስድና ከተቀመጠው ጊዜ በላይ መሄድ እንዳለባችሁ በማስታወስ ለራሳችሁ በቂ ጊዜ ስጡ፡፡



የግብረ ገብ ትምህርት

## 2.6. የምዕራፉ ማጠቃለያ

ጠንካራ የስራ ባህል ሰዎች ድህነትን ለማጥፋትና በፍጥነት እንዲያድጉ ያስችላቸዋል፡፡እንዲሁም የሀገሪቱን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፡፡

ተማሪዎች ጠንካራ የስራ ባህልን በትምህርት ቤት ከዕድሜያቸው ጋር የሚመጣጠን ስራን እየተማሩና እየተለማመዱ ሲያድጉ በስራው ዓለም ውስጥ ሲገቡም ይህን የስራ ባህል በማዳበር ውጤታማ ዜጎች ይሆናሉ፡፡በመማር-ማስተር ሂደት ውስጥ እንደዚህ አይነት ተማሪዎች ንቁተሳታፊዎች በመሆናቸው ትምህርት ቤቱ የሚያቀርባቸውን እድሎች ሁሉ ይጠቀማሉ፡፡ልጅንበአቅሙና በእድሜው የሚችለውን ስራ ማስተማር የሕፃናት ጥቃት ወይም ጉልበት ብዝበዛ አይደለም፤ይልቁንም ዛሬ በጥሩ ሁኔታ መስራት ከለመዱ ለወደፊቱ ጠንክሮ የመስራትን ዋጋ ይገነዘባሉ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ባህል
- ታታሪነት
- የህፃናት ጥቃት
- የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ
- ሥራ
- የንበብ ባህል
- ስልቶች
- ችሎታ

## ማጠቃለያ መልመጃ 2.1

### ትዕዛዝ 1:የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ::

1) ባህል ባህሪያችንንና እምነታችንን በማጎልበት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል::
2) መመካት ወይንም ጥገኛ መሆን ያለብን በእድል ላይ እንጂ በትጋት ላይ አይደለም::
3) ታታሪ ተማሪ በህይወቱ ስኬታማ የመሆን እድል የለውም::
4) ጠንክሮ መስራት ጎበዝ ተማሪዎች ካሏቸው ባህሪያት ውስጥ አንዱ ነው::
5) የማንበብ ልምድ በህይወት ውስጥ ትልቅ መዋዕለ ንዋይ ነው::

### ትዕዛዝ II:ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1) ጠንካራ የስራ ባህል ሰዎችን ምን እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል?

    (ሀ) ድሆች እና ደካማ እንዲሆኑ::

    (ለ) ድህነትን በማጥፋት በፍጥነት ማደግ እንዲችሉ::

    (ሐ) ውጤታማና ስኬታማ ያልሆኑ ያደርጋቸዋል::

    (መ) ጠንካራና ጤናማ አያደርጋቸዉም::

2) ከሚከተሉት ውስጥ የታታሪ ተማሪ ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

    (ሀ) በመደበኛነት ትምህርቱን ይከታተላል::

    (ለ) የቤት ሥራውን ሁልጊዜ ይሰራል::

    (ሐ) በክፍል ውስጥ ትምህርቱን በትኩረት ይከታተላል::

    (መ) በክፍል ውስጥ በንቃት አይሳተፍም::

3) የንባብ ልምድን ስለማዳበር ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

    (ሀ) በየቀኑ ለማንበብ ጊዜ መመደብ::

    (ለ) አስደሳች መጽሐፍትን ማንበብ::

    (ሐ) መጽሐፍትን ይዞ መንቀሳቀስ::





    (መ) በምናነብበትጊዜድምፅማሰማት::

4) ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ ጠንክሮ መሥራትን ሲማሩ፡-

    (ሀ) የመሥራት ልምዳቸው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ከእነሱ ጋር ዘላቂ ይሆናል::

    (ለ) የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ሊደርስባቸውይችላል::

    (ሐ) የልጆቹ የጤና ሁኔታ ይጓደላል::

    (መ)የልጆች የሥራ ፍላጎት ይቀንሳል::

### ትዕዛዝ III: ባዶ ቦታዉን ሙሉ::

1) ጊዜንና ጉልበትን ለአንድ የተወሰነ ሥራ ወይም ተግባር የማዋል ጥረት ወይም ልምድ …………ይባላል::
2) የተለየ ወይም የተወሰነ መረጃን ለመፈለግ የምንጠቀመው የፍጥነት ንባብ ዓይነት ………..
3) አጠቃላይ ሀሳብን ለማግኘት የምንጠቀመው የፍጥነት ንባብ…………………

### ትዕዛዝ IV: አጭር መልስ ስጡ::

1) ልጅን እንዴት ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት ማስተማር እንደበደል ሊወሰድ ይችላል? ለምን?

# ምዕራፍ ሦስት

# የግብረ ገባዊ ውሳኔ ክህሎት

***መግቢያ***

ይህ ምዕራፍ የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ክህሎትን የሚመለከት ሲሆን በአምስት የትምህርት ክፍሎች የተከፋፈለ ነው፡፡ እነሱም የውሳኔ አሰጣጥ መሰረታዊ ጽንሰ-ሀሳብ፣ ባህሪያት፣ ዓይነቶች፣ አስፈላጊነት እና ተግዳሮቶችን አጠቃሎ ይዟል፡፡ የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥን ስንመለከት ተማሪዎች በየቀኑ የተለያዩ ውሳኔዎችን ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ ውሳኔዎች በጥንቃቄ ያልታዩና ያልተገመገሙ ይሆናል፡፡ የውሳኔ ሰጭነት ክህሎትን ማዳበር ችግሮችን ለመፍታት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ይህንን ክህሎት በመጠቀም በሚወስኑት ጉዳይ ላይ አስቀድመው እንዲያስቡ፣ አወንታዊና አሉታዊ ውጤቶችን እንዲያጤኑ፣ከዚያም እንዲተገብሩ ይረዳቸዋል፡፡

***የመማርውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን የትምህርት ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-***

- የውሳኔ አሰጣጥ ትርጉምን ታብራራላችሁ፡፡
- ለግብረገባዊ ውሳኔዎች የሚያገለግሉ ስልቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ለምክንያታዊ የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታዎች ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- የግብረገባዊ ውሳኔዎችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ታሳያላችሁ፡፡
- የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ክህሎትን ተግዳሮቶች ትለያላችሁ፡፡





## 3.1 የውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ-ሐሳብ



ምስል 3.1: በጉዟችን ሁሉግብረገባዊ ውሳኔን መወሰን፡፡

**ተግባር 3.1**

- ከምስል 3.1 ምን ታዘባችሁ?
- የታዘባችሁትን ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

ግብረገብ ማለት ትክክለኛና ምክንያታዊ ውሳኔ ወይም ምርጫ የማቅረብ ችሎታ ነው፡፡

ማዳበር ከሚያስፈልጉን ችሎታዎች አንዱና ቁልፍ የሆነው የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ ነው፡፡

ውሳኔ የመስጠት ተግባር አንድ ሰው ከሚያጋጥመው በርካታ አማራጮች ውስጥ ሁሉንም በመገምገም አንድ ጠቃሚ የሆነውን አማራጭ የመቀበልና መደምደሚያ ላይ የመድረስ ሂደት ነው፡፡ የምናደርጋቸው ውሳኔዎች ዉስጣዊ ሰላም ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ የእርስ በርስ ግንኙነትና ስኬት በአብዛኛው የሚተሳሰረው በጥንቃቄ በምንወስነው ግብረገባዊ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግብረገባዊ ውሳኔ የማድረግ ችሎታ ኃላፊነት የሚሰማን እንድንሆን ይረዳናል፡፡ ስለሆነም ግብረገባዊ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ያለው ተማሪ ኃላፊነት የሚሰማውና በራሱ የሚተማመን ይሆናል፡፡

ውሳኔ መስጠት በውስጡ ዓላማ ስላለው ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጭ በተማሩት ላይ በመመርኮዝ የህይወትን አካሄድ ይወስናሉ፡፡ እንደ ተማሪም ወይም ሰራተኛ ስኬትንና መልካም ዜጋን መሆንን ያተርፋሉ፡፡

አሁን ላይ ተማሪዎች የራሳቸውንም ሆነ የቤተሰባቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ለሀገራቸው ደህንነት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማድረግ በመረጃ የተደገፈና ኃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ እስከማድረግ ድረስ “የተማሩ” ናቸው ተብለው ይታሰባሉ፡፡

ተግባር 3.2

በተጨናነቀ መንገድ ላይ ከወላጆችህ ጋር እየሄድክ አንዲት አቅመ ደካማ ሴት ከህንፃዉ በር ወጥታ ደረጃውን እየወረደች ሳለ በድንገት መሬት ላይ ስትወድቅ ተመለከትክ:: በጥልቅ ህመም ውስጥ ሆና ወደ እግሯ ትጠቁማለች::

ምን ዓይነት ውሳኔ ልታደርግ ነው?

እርምጃ:.....................................................................................

ውሳኔህ ግብረ ገባዊ ነበር? ለምን?

## 3.2.የግብረገባዊ ውሳኔ ችሎታ ባህሪያት

ተግባር 3.3

- ከዚህ በፊት በቤት ውስጥ ስላደረጋችሁት የውሳኔ ታሪክ ተነጋገሩ::
- ውሳኔዉ ጠቃሚ ነበር ወይስ አልነበረም? ግብረ ገባዊ ውሳኔ ነበር?

ግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ካሉት በርካታ አማራጮች ዉስጥ ትክክለኛና የተሻለዉን የመምረጥ እና የመወሰን ሂደት ነው::

ይህም የውሳኔ ሂደት አንድ ሰው በተረጋጋ አእምሮ ውስጥ ሆኖ ሁለቱንም አወንታዊ እና አሉታዊ አማራጮችን በመገምገምና በማየት የትኛውን አማራጭ እንደሚወስድ የሚወስንበት ሁኔታ ነው::

ግብረገባዊ ውሳኔ ትክክል ወይም ተቀባይነት ያለዉ በመሆኑ ለተሳታፊዉ ሁሉ አዎንታዊ ውጤትን ያስገኛል::

**የግብረገባዊ ውሳኔ ችሎታዎች የሚከተሉት ባሕርያት አሏቸው::**

### 3.2.1 አሳቢነት

የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሊሆኑ ከሚችሉ አማራጮች መካከል የመምረጥ ክህሎት ነዉ:: በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ትክክለኛውን ዉሳኔ ለመስጠት መጀመሪያ ሁሉንም መረጃዎች በማሰባሰብ ካጠናቀቅን በኋላ ውሳኔዎችን ማድረግ ነዉ::

### 3.2.2 ምክንያታዊነት

ምክንያታዊነት ለአንድ ለተወሰነ ምክንያት የሚስማማ ነገር ነው:: ይህም ሲባል ችግሩን የመለየት ሂደት እና ተጓዳኝ የመፍትሄ ዘዴዎችን ይመለከታል::የተሻለ ውሳኔ ለመወሰን የችግሩን ትንተናና





የተለያዩ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል:: ማመዛዘን ማለት እናንተ ልትወስኑት ስለምትችሉት ውሳኔ ለማወቅ ከሚያስፈልጋችሁ ቁልፍ ክህሎት አንዱ ነው::

በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ ዉሳኔ ለመስጠት ስታስቡ የተለያዩ ጥቅሞችንና ጉዳቶችን በመገምገም ከአማራጮች መካከል የተሻለውን መንገድ በማስቀደም የአሁኑን ጊዜ ለማመዛዘንና የወደፊቱን ለማቀድ ይጠቅማል::

### 3.2.3 ምክንያታዊ ውሳኔ

ተግባር 3.4

ዉስን ጥናት 3.2.1

አንድ ቀን ከጓደኞችህ ጋር ምሳ እየበላህ እያለ ከጓደኞችህ አንዱ እየበላ አንድ ታሪክ ያወራ ነበር:: በዚህ መሃል ምግቡ ትን ይለዋል ወይም ያንቀዋል:: እናም " እርዳኝ " በማለት ድምጽ ያሰማል:: ምን ዓይነት ውሳኔ ልታደርግ ትችላለህ?

እርምጃ:--------------------------------------------------

ውሳኔህ ግብረ ገባዊ ነበር? ለምን?

ምክንያታዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥንቃቄ የተሞላበት እና ስልታዊ እርምጃዎችን ያካትታል:: ጥንቃቄ በተሞላበትና በእነዚህ እርምጃዎች ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የበለጠ ምክንያታዊ ይሆናል:: ቀጥሎ በቀረበዉ ክፍል ላይ የእያንዳንዱን ቅደም ተከተል ሂደት በዝርዝር ትማራላችሁ::

በመሠረቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ችግሮችን እንዴት መለየት፣መረጃን እንዴት መሰብሰብና ለችግሩ መፍትሄዎችን እንዴት ማምጣት እንደምንችል ያካትታል::

ትክክለኛዉን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ስትከተሉና ጥንቃቄ የተሞላበት ዉሳኔ ስትሰጡ ስለዉሳኔ አሰጣጥ ተማራችሁ ወይንም ግንዛቤ አገኛችሁ ማለት ነዉ::

**ደረጃ 1: ችግሩን መለየት**



ምስል 3.2: ጊዜ ያጠረዉ ተማሪ

ችግርን መለየት የራሱ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ የግምገማ መንገድ አለው። ለአንድ ችግር መፍትሄ ከመፈለጋችን በፊት ችግሩ ከሌሎች ተመርጦ መለየትና መተንተን አለበት።በዚህ ሂደት ውስጥ እውነተኛው ችግር ምን እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል።እናም የችግሩን ዋና መንስኤ ለማግኘት እና ችግሩን ለመፍታት ያሉትን እድሎችን ያሰፋል።. በዚህ አኳኋን በችግሩና በምክንያቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በመተንተን ግብረገባዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን ይረዳል።

**ደረጃ 1: ችግሩን መለየት**

- ለማወቅ እየሞከራችሁት ያለዉ ነገር ምንድነው?
- የተሻለዉን ምርጫ ለማድረግ ችግሩ ምን እንደሆነ በትክክል መታወቅ አለበት።
- አንዴ ችግሩ ምን እንደሆነ ከለየን ያጋጠመንን ችግር መፍታት ስለሚቻሉባቸው መንገዶች ማሰብ እንጀምራለን።

ተግባር 3.5፡

**በስዕል 3.2 ላይ የምትመለከቱትን ችግር መለየት ትችላላችሁ?**

- ጊዜ የለኝም ቁርሴን እንኳ ምን መብላት እንዳለብኝ አላውቅም!

**ደረጃ 2፡ ለማነቃቂያ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች**

ይሆናሉ ብላችሁ የምታስቧቸዉን ሁሉንም አማራጮች ዘርዝሩ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማየታችሁ ምርጫችሁን ለመገምገም ሊረዳችሁ ይችላል፡- ቅንነት የጎደለው ነው? ጎጂ ነው? ኢ-ፍትሃዊ ነው? ሐቀኝነት የጎደለው ነው? ከአላማዉ ጋር ይጣጣማል?

አንዳንድ ጊዜ የተሻሉ አማራጮችን ለማምጣት ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ሊኖርብን ይችላል።

**ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ማደረግ ትችላለህ!**

- ስለ ችግሩ የበለጠ እወቁ /ጠይቁ።
- ከቅርብ ቤተሰብ አባል ምክርንጠይቁ።
- መረጃን ከመጻሕፍት፣ ከድህረ-ገጾች ወይም ከሰዎች  አግኙ።





- ለእናንተ አስፈላጊ መሆኑን አስቡ።
- ሌሎች ሰዎች ስለ ችግሩ ምን እንደሚሰማቸው አስቡ።

መረጃውን በምትሰበስቡበት ጊዜ ምናልባት የተወሰኑ አማራጮችን ልታገኙ ትችላላችሁ ወይም የራሳችሁን የተሻለ ሀሳብ መፍጠር ትችላላሁ። ትክክለኛና ውጤታማ ውሳኔ ለመወሰን ሁሉንም አማራጮች መዘርዘር አለባችሁ።

**ደረጃ 3፡ ሊከሰቱ የሚችሉ ዉጤቶችን መለየት**

አወንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶችን ዘርዝሩ። የምታደርጉት እያንዳንዱ ውሳኔ አወንታዊና አሉታዊ ውጤቶች ሊያስከትል ስለሚችል ከሁሉም የበለጠ የተሻለዉን ዉሳኔ መወሰን የእናንተ ፋንታ ነው።

አወንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶችን መለየት አስፈላጊ ነው።ተማሪዎች በራሳቸው ሊወስኗቸው የሚችሏቸውን ውሳኔዎች እና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ውሳኔዎች መለየት አለባቸዉ።

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተመልከቱ።**

- ምርጫው ጤናማ ነው ወይስ አይደለም?
- ምርጫው ምን ያህል ተጽዕኖ አሳድሮብኛል?
- ምርጫው በሌሎች ላይ ምን ያክል ተጽእኖ አሳድሯል?
- ይህ አማራጭ ያሉኝን እሴቶች ይደግፋል?
- እነዚህ አማራጮች ዓላማዬ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራሉ?
- ውሳኔው ሕጉን የተከተለ ነው?

**ደረጃ 4፡መወሰን እና መከታተል**

ያገኛችሁትን ሁሉንም መረጃዎች ከገመገማችሁ በኋላ በእናንተ እይታ በጣም ጥሩ የሆነውን አማራጭ ለመምረጥ ዝግጁ ትሆናላችሁ። ከአንድ በላይ የሆኑ አማራጮችንም በማዋሃድ መምረጥ ትችላላችሁ። በደረጃ 4 ላይ ያለው ምርጫ በደረጃ 2 መጨረሻ ላይ ባለው ዝርዝር ውስጥ ከተቀመጡት አማራጮች ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረዉ ይችላል።

**ደረጃ 5፡ የውሳኔዉን ውጤት መገምገም**

ይህ የመጨረሻ ደረጃ የውሳኔውን ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባትና በደረጃ 1 ላይ የተለየውን ችግር እንደፈታው ወይም እንዳልፈታውትገመግሙብታላችሁ። አዲስ ውሳኔ ለምሳሌ የበለጠ ዝርዝር ወይም የተለየ መረጃ መሰብሰብ ወይም ተጨማሪ አማራጮችን ማሰስ የሚያስፈልግም

ከሆነ በውሳኔው ላይ ጊዜ ወስዳችሁበማሰላሰል የውሳኔውን ውጤት ተንትኑ።

**ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጋር በተገናኘ የተለያዩ ጥያቄዎችን መልሱ ለምሳሌ እንደ፡-**

- ያደረግኩት ውሳኔ ምን ነበር?
- ይህን ምርጫ ለምን አደረግሁ?
- የወሰንኩት ውሳኔ ውጤታማ ሆኗል? ለምን ወይም ለምን አልሆነም?
- ይህ ውሳኔ በዉስጣዊ ሰላሜ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳደረ?
- ይህን ውሳኔ እንደገና ትወስናለህ/ሽ?

ተግባር 3.6

ውስን ጥናት 3.3.1

ያያ የ14 ዓመት ልጅ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከሁለት የቅርብ ጓደኞቹ ጋር ሲወጣ ሳምቡሳ የሚገዛላቸውን ታላቅ ወንድሙን ያገኛሉ። ያያ መብላት የሚፈልገው ትንሽነው።ምክንያቱም ወላጆቹ ቢያውቁ በጣም ይቆጡታል። ከዚህም በላይ ዳግመኛ ከቅርብ ጓደኞቹ ጋር እንዲወጣ አይፈቅዱለትም። ስለዚህ በምንም መልኩ ከቤት ውጭ መብላት አይፈልግም። ነገር ግን ጓደኞቹ ብዙ እንዲበላ ይገፋፉታል። በያያ ቦታ አንተ/ቺ ብትሆን/ኚ ምን ማድረግ አለብህ/ሽ?

**የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት**

**ደረጃ 1: የሚደረገውን ውሳኔ መለየት**

- ዉሳኔዉን ለመወሰን መደረግ ያለበትን ሁኔታዎች ግለጹ፡-

---------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------

- መወሰን ያለበት ምንድን ነው?

------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------

- ይህ ውሳኔ ለእኔ ዉስጣዊ ሰላም ይሰጠኛል?

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------





- ይህ ሁኔታ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን እንድከተል አድርጎኛል? አዎ ወይም አይደለም መልሱ ይብራራ።

---------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

- ይህንን ውሳኔ ብቻዬን መወሰን እችላለሁ? ወይስ የአዋቂ ወይም የታመነ የመረጃ ምንጭ እርዳታ ያስፈልገኛል? ይብራራ።

--------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------

- ይህ ውሳኔ በቀሪው ሕይወቴ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ያሳድራል?

-------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------

**ደረጃ 2: ለማነቃቂያ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች**

**ደረጃ 3: ሊከሰቱ የሚችሉ ዉጤቶችን መለየት**

**የአማራጮች አዎንታዊ ውጤት አሉታዊ ውጤት**

1. ----------------- ---------------------- ------------------------
2. ---------------- ---------------------- -----------------------

3.---------------- --------------------- ----------------------

**ደረጃ 4:መወሰን እና መከታተል።አሁን ከታች ያሉትን መስፈርቶች ተመልከቱና**

እያንዳንዱን ጥያቄ በምርጫችሁ መሰረት መልሱ። ለጥያቄዎቻችሁ መልስ አይሆንም ብላችሁ ካመናችሁ ምርጫሁን እንደገና መገምገም ያስፈልጋል።

1. ምርጫችሁ ጤናማ ነው? (አዎን/አይደለም)
2. ይህ ውሳኔዬ የህሊና እረፍት ይሰጠኛል?(አዎን /አይደለም)
3. ይህ ውሳኔ ስለ እኔ የሚያስቡ ሰዎችን ያከብራል?(አዎን /አይደለም)
4. ይህ አማራጭ ዓላማዬን ያሳድጋል?(አዎን /አይደለም)
5. ይህ ውሳኔ ህግን የተከተለ ነዉ?(አዎን /አይደለም)

**ደረጃ 5: በተሰጠው ውሳኔ ላይ ሃሳብ መስጠት ወይም መገምገም ዉሳኔን ማንፀባረቅ**

የሰጣችሁት ውሳኔ እንዴት እንደሰራ የሚያንፀባርቅ የሚያሳይ አንድ አንቀጽ ጻፉና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ሀሳብ ተለዋወጡ።

በየፋችሁት አንቀጽ ውስጥ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አንዳንድ መልሶችን ተጠቀሙ።

- ምርጫዉን ለምን አደረግሁ?
- የወሰንኩት ውሳኔ ውጤታማ ሆኗል? ለምን ወይም ለምን አልሆነም?
- ይህ ውሳኔ በእኔ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳደረ?
- ይህን ውሳኔ እንደገና እወስናለሁ?

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

## 3.4 የግብረገባዊ ውሳኔ አስፈላጊነት

ውሳኔ መስጠት በሁሉም የእድሜ ክልል ያሉ ዜጎች ሊማሩት የሚገባ ጠቃሚ ችሎታ ነው። ምክንያቱም ወላጆች ልጆቻቸዉን ራሳቸዉን የቻሉ፣ኃላፊነት የሚሰማችዉና መልካም ዜጋ ሆነዉ እንዲያድጉ ስለሚፈልጉ ነዉ። ከዚህም በላይ ሁኔታዎችን ከግምት ዉስጥ በማስገባት ግብረገባዊ ዉሳኔዎችን የሚገመግሙና የሚወስኑ ልጆች ግብረገባዊነት ከጎደለዉ ዉሳኔ ከሚሰጡ በተሻለ የወደፊት ህይወታቸዉ የተሳካና የተቃና ይሆናል።

ስለዚህ ግብረገባዊ ዉሳኔ መስጠትን ስትማሩና ችሎታዉንም ስታዳብሩ የችግር አፈታት ሂደትን የምትከተሉ ስለምትሆኑ ችግሮችን በቀላሉና ብልሀት በተሞላበት መንገድ የመፍታት አቅም ይኖራችኋል።



ምስል 3.3: ብልሀት ችግርን ያቀላል





### ተግባር 3.7

**ከላይ ካለው ሥዕል ምን ትማራላችሁ? ጥንድ ሆናችሁ በመቀመጥ ተወያዩ። ስትወያዩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከግምት ዉስጥ አስገቡ።**

- ምን አይነት ውሳኔ ነዉ በጣም አጭር ሂደትን የሚከተለዉ?
- የበለጠ ጥልቅና ሰፊ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚያስፈልጋቸዉ ምን አይነት ውሳኔዎች ናቸዉ?
- አንዳንድ ውሳኔዎችን ከሌሎቹ የበለጠ አስፈላጊ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

ግብረ ገባዊ ውሳኔ መስጠትን መማር ተገቢ ሂደት ነው። ሂደቱ በጣም ከባድ ነው በተለይም እንደናንተ ላሉ ልጆች፣ይሁንና ቀላል የሆኑ ስልቶች በመጠቀም ለወደፊቱ ጥሩ ውሳኔዎችንና የተሻሉ ምርጫዎችን ከክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጭ ማድረግ እንድትችሉ ይረዳችኋል።

ከዚህ ቀደም ብሎ እንደተማራችሁት ግብረገባዊ ውሳኔ በህይወታችሁ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይህ ደግሞ በወጥመድ/ችግር/ ውስጥ ከመውደቅ የሚያድናችሁ ሲሆን የወደፊት ስራችሁም ያማረ እንዲሆን ያደርጋል። በተመሳሳይም ህይወታችሁንና በዙሪያችሁ ያሉትን ሰዎች ከሚጎዱ የተሳሳቱ ውሳኔዎችን ከማድረግ ይጠብቃችኋል።

በአጠቃላይ ሥነ-ምግባራዊ (ወይም ሥነ-ምግባር የጎደለው) ውሳኔ አሰጣጥ ብዙ ሰዎችን ይጎዳል። ስለዚህ ያለ ጥርጥር በልጅነት እድሜያችሁ የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ክህሎትን መማር በጣም አስፈላጊ ነው። እውነቱን ለመናገር ብዙ ልጆች በስሜት ወይም በጊዜያዊ ተነሳሽነት ላይ ሆነዉ ይወስናሉ። የታሰቡባቸዉ ምርጫዎችን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል መማር የህይወት አንዱ ክህሎት ነው። ስለሆነም መማርና መለማመድ ያስፈልጋል።

## 3.5 የግብረገባዊ ውሳኔ ተግዳሮቶች

ባለው ችግር ላይ በመመስረት ትክክለኛውን ምርጫ የመምረጥ ችሎታ የውሳኔ አሰጣጥ ጉዳይ ነው። የግለሰብንውሳኔሂደት መረዳት አስፈላጊ ነው።

ውሳኔ ማድረግ አማራጭ መንገድ የሆነበት ሁኔታ ሲፈጠር ግለሰቡ ከማወላወል ይልቅ ጥሩ ውሳኔ ማድረግ መቻል አለበት። እውነታው ግን በጣም ስሜታዊ የሆኑ ሰዎች የግብረገባዊ ውሳኔዎችን በፍጥነት እንዲወስኑ ያደርጋቸዋል።

ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት በግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች ናቸው።

**ለራስ የሚሰጥ ግምት፡-** ማለት ለራሳችን የምንሰጠዉ ስዕል ወይም ግንዛቤ ማለት ነዉ፡፡

**ተጨማሪ ቁርጠኝነት፡-** ይህ የሚያመለክተዉ እንደ ሰው ምክንያት ላለው ነገር ራስን ማዘገጀትን ያካትታል፡፡ ቁርጠኛ ከመሆናችን በፊት በጉዳዩ ላይ በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ቁርጠኝነት አንድ ነገር እንድታደርግ ያስገድድሃል፡፡

**የአቻ-ግፊት፡-**አንድ ሰው በጓደኞቹ ዘንድ ለመወደድ ወይም ለመከበር እንደ ሌሎቹ የእድሜ እና የማህበራዊ ቡድን ሰዎች ተመሳሳይ ነገሮችን የማድረግ ስሜት ነው፡፡

**በወላጆች የሚሰጥ ግምት፡-** ይህ የሚያመለክተው የወላጆች ስለልጆቻቸዉ የወደፊት ስኬቶች፣ በትምህረታቸዉ ላይ ስለሚያሳዩት ትጋት፣ እዉቀትና ሌሎችም ያላቸው እምነትና ግምት ነው፡፡

**በማሕብረሰቡ የሚሰጥ ግምት፡-** ይህ ተቀባይነት ያለዉ ወግና ልማድን የተከተለ ግለሰብ ወይም ተቋም መሆንን ይመለከታል፡፡ ስለዚህ የህብረተሰቡን አጠቃላይ ውስጣዊ ማህበራዊ ደንብን መከተል እንዳለበት ያሳያል፡፡

**የተገደበ ምክንያታዊነት፡-** ዉሳኔዎችን በምንሰጥበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ምክንያታዊ መሆን አንችልም ምክንያቱም የተሟላ መረጃን ማግኘት ስለሚያስቸግር፡፡

**የማረጋገጫ ወገንተኝነት፡-**ያለንን እምነት ለሚያረጋግጡ መረጃዎች ትኩረት የመስጠትና ካለን እምነት ጋር የሚጋጩ መረጃዎችን ችላ የማለት ወይም የመቀነስ ዝንባሌ ነዉ፡፡

**የበዛ ቁርጠኝነት** ፡-ይህ ዓይነት የውሳኔ ሰጪነት ዝንባሌ ለደካማ ውሳኔ ቁርጠኛ የመሆን ዝንባሌ ነዉ፡፡ እንዲህ አይነት ዉሳኔ ሲደረግ ከጊዜ ወደ ጊዜ አሉታዊ ውጤቶችን ያስከትላል፡፡

**የግንኙነት ግጭት፡-** በግለሰብ(በግለሰቦች) ስብዕና እና በመካከላቸዉ ባለ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ግጭት ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ገንቢ ሳይሆን አጥፊ ነው፡፡

ተግባር 3.8

ከላይ ከተጠቀሱት የግብረ ገባዊ ውሳኔ ተግዳሮቶች መካከል እናንተ ውሳኔ ስትሰጡ ያጋጠሟችሁ ፈታኝ ሁኔታዎች አሉን? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማካፈል ትችላላችሁ፡፡





## 3.6 የምዕራፉ ማጠቃለያ




ምስል 3.4፡ መልካም ተማሪዎች በግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ውስጥ ያልፋሉ

**ቁልፍ ቃላት**

- ግብረገብ
- ውሳኔ መስጠት
- ትክክለኛነት
- መገምገም
- አማራጮች
- አሉታዊ
- አዎንታዊ
- የተሻለ ምርጫ
- ውጤት
- ችግር

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ 3.1

### የሚከተሉትን የተለያዩ አጫጭር ታሪኮች አንብቡና ግብረገባዊ ውሳኔ ወስኑ።በአምስት ቡድን ተከፋፍላችሁ ተወያዩና የውይይታችሁን ውጤት ለሁሉም የክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዉቁ።

መልሶቻችሁን በተማራችሁት የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ላይ ተመስርታችሁ አስረዱ።

•ከጓደኞችህ ጋር እግር ኳስ እየተጫወትክ እያለ በድንገት አንደኛው ተጫዋች በሜዳው ላይ ራሱን ስቶ ወደቀ። ነገር ግን ትንፋሹ አልተቋረጠም።

1) ምን ዓይነት ውሳኔ ልታደርግ ነው?

እርምጃ:----------------------------------------------------------

ውሳኔህ ግብረገባዊ ነበር? ለምን?---------------------------------

•መምህራችሁ የቤት ስራ ሰጥተዋል። የቤት ስራውን ያልሰራ ጓደኛችሁ ከእናንተ ደብተር ላይ መቅዳት ይፈልጋል።ች

2) ምን ዓይነት ውሳኔ ልትወስኑ ነው?

እርምጃ:-------------------------------------------------------------------------

ውሳኔያችሁ ግብረገባዊ ነበር? ለምን?-------------------------------------------------

•በተመስጦ አንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እየተመለከትክ/ሽ ቆይተህ/ሽ በመሓል ወደ መጸዳጃ ቤት ሄድክ/ሽ። ስትመለስ/ሽ ታናሽ ወንድምህ/ሽ ጣቢያዉን ቀይሮት አገኘኸዉ/ሽዉ።

3) ምን ዓይነት ውሳኔ ልታደርግ/ጊ ነው?

እርምጃ:---------------------------------------------------------------------------

ውሳኔህ/ሽ ግብረገባዊ ነበር? ለምን?-----------------------------------------------





•ለፈተና ማጥናት ትፈልጋለህ ነገር ግን የምትወደዉ ጓደኛህ ከአንተ ጋር እግር ኳስ መጫወት ይፈልጋል።

4) ምን ልትወስን ነው?

እርምጃ:---------------------------------------------------------------------------------

ውሳኔህ ግብረገባዊ ነበር? ለምን?-------------------------------------------------------------

•በመንገድ ላይ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ የኪስ ቦርሳ መሬት ላይ ወድቆ ታገኛለህ። ጓደኛህ አንሳዉና ዉሰደዉ ይልሃል።

5) ምን ትወስናለህ?

እርምጃ:-----------------------------------------------------------------------------------

ውሳኔህ ግብረገባዊ ነበር? ለምን?-------------------------------------------------------------------

# ምዕራፍ አራት

## የአካባቢ እንክብካቤ

*መግቢያ*

በምዕራፍ ሶስት ዉስጥ በዋናነት ስለ ግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ የተማራችሁ ሲሆን በዚህም ስር የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ-ሀሳብ ፣ የግብረገባዊ የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ፣ የተሻለ የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ ባህሪያት፣የጥሩ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች እና የመልካም ውሳኔ ተግዳሮቶችን ተመልክታችኋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለአካባቢ እንክብካቤ ፅንሰ-ሀሳብ ፣ አካባቢን የመንከባከብ ጥቅሞች ፣ አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶችንና አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን መዘዝ ትማራላችሁ።

**የመማር ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የአካባቢ እንክብካቤ ጽንሰ-ሐሳብን ትረዳላችሁ።
- የአካባቢ እንክብካቤ ለሚያስገኟቸውን ጥቅሞች ዋጋ ትሰጣላችሁ ።
- የአካባቢ መንከባከቢያ መንገዶች ላይ ትወያያላችሁ።
- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ችግሮች ትጠቅሳላችሁ።





**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ስለ አካባቢ ምን ታዉቃላችሁ?
- አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶች ምን ምንድ ናቸዉ?

### 4.1.1 'አካባቢ' ምንድን ነው?

'አካባቢ' የሚለው ቃል በሰፊው ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ሰፊ ጽንሰ-ሐሳብና ትርጉምም አለዉ። 'አካባቢ' የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? በዘልማድ ለአንዳንድ ሰዎች 'አካባቢ' የሚለው ቃል በቀላሉ 'ተፈጥሮ' ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ለአንዳን ሰዎች የተፈጥሮ መልክዓ-ምድራዊ ገጽታዎችንና ሁነቶችን የያዘ ሲሆን ለሌሎች ሰዎች ደግሞ 'አካባቢ' የሚለው ቃል በተወሰነ ደረጃ ሰዋዊ የሆኑ ነገሮችንም ያካትታል። ብዙ ሰዎች ለምሳሌ የግብርናና የአርብቶ አደር መልክአ ምድሮችን እንደ'አካባቢ አካል አድርገው ይመለከቱታል፤ ሌሎች ደግሞ የበለጠ አካታች ሲሆኑ የከተማ አካባቢዎችን ጨምሮ ሁሉንም የምድር ገጽ አካላትን እንደ አካባቢ ይመለከቷቸዋል።

'አካባቢ' በጥሬ ትርጉሙ በቀላሉ 'ዙሪያ' (አካባቢ) እንደ ማለት ነው። ስለዚህ 'አካባቢ' ሁሉንም ግላዊ፣ቁስ አካላዊና መዋቅራዊ ስርዓትን ያጠቃልላል።



ምስል 4.1፡ በአርባ ምንጭ በአባያ እናጫሞ ሀይቆች መካከል የሚገኝ ጥቅጥቅ ያለ ደን

### 4.2 የአካባቢ እንክብካቤ ጽንሰ-ሐሳብ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

ተግባር 4.1

- አካባቢን መንከባከብ ማለት ምን ማለት ነው?
- አካባቢን የመንከባከብ ትርጉም ተናገሩ።

አካባቢን መንከባከብ ማለት የአካባቢን ደህንነት መጠበቅሲሆን ለምሳሌ የፕላስቲክ ጠርሙሶችን ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ከመጣል ይልቅ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል እና መብራቶችን በማይፈልጉበት ጊዜ ማጥፋትና መቆጠብ የመሳሰሉት ማለት ነው፡፡ አካባቢን ለመንከባከብ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ የኛ ፋንታ ነው፡፡

አካባቢያችን ለመኖር የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ አሟልቶ ይዟል፤ ነገር ግን የምንፈልገውን እንዲሰጠን መንከባከብና መጠበቅ አለብን፡፡ ዛፎችን በመትከል አከባቢያችንን አረንጓዴ ማድረግለኑሮ ምቹና ተስማሚ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

አካባቢያችንን አረንጓዴና ምቹ ለማድረግ የሚረዱ በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ አካባቢን ተስማሚና ተመራጭ ለማድረግ የግድ ትልቅ ሰው መሆን አይጠበቅብንም፡፡ እንደ ውሃ፣ አፈር፤ እጽዋት ወዘተ የመሳሰሉትን የምድርን የተፈጥሮ ሀብቶች መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ቀጣዩ ትዉልድ በተመቻቸ አካባቢ ውሰጥ መኖር እንዲችል ዛሬ ላይ ያለው የሚጠበቅበትን ሁሉ መወጣት አለበት፡፡

**ተግባር 4.2**

1) የአካባቢ እንክብካቤ ምንድነው?

2) ከአከባቢያችሁ ስነ-ምህዳር ጋር እንዴት ተስማምታችሁ ትኖራናችሁ?

## 4.3 የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

**ተግባር 4.3**

- የአካባቢ እንክብካቤ የሚያስገኛቸውን አንዳንድ ጥቅሞች መጥቀስ ትችላለህ/ሽ?

በዙሪያችን ያለው አካባቢ ቤታችን ብቻ ሳይሆን በሕይወት እንድንኖር የሚያደርገን ሁሉ ነገራችን ነው፡፡ ከምንመገበው ምግብ፣ ከምንጠጣው ውሃ፣ ከምንተነፍሰው አየር፣ ከመጠለያችን እና ከሌሎችም ነገሮች አንፃር በሕይወት እንድንኖር ያስችለናል፡፡ ስለዚህ አካባቢን መንከባከብ በእኛ ውስጥ መለመድና መዳበር ያለበት ተግባር ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ተግባራችን እራሳችንን ጨምሮ በዙሪያችን ያሉትን ነገሮች ሁሉ አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ ከአካባቢያችን ጋር ያለን መስተጋብርና ተፈጥሮ የሚሰጠውን ሀብት የምንጠቀምበት መንገድ ዘላቂነት ባለው መልኩ መሆን አለበት፡፡ ካልሆነ ግን የችግሩ ግንባር ቀደም ተጠቂ የምንሆነው እኛው ራሳችን ነን፡፡





ስለዚህ እያንዳንዱ ተግባራችን በአካባቢው ምንም ጉዳት እንዳያደርስ ማረጋገጥና መጠንቀቅ አለብን፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጡትን የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነትን እንመልከት፡፡

### 4.3.1 አካባቢያችን ለእኛ ለሰው ልጆች ብቻ ነው እንደ ቤታችን የሆነልን ?

**ተግባር 4.4**

- የአካባቢ እንክባካቤ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ምንም እንኳን አንዳንዶቻችን ይህንን ጉዳይ አቅልለን ብንመለከተውም በተለይ ለእኛ ለሰው ልጆች የምንኖርበት ሌላ  አማራጭ ቦታ እንደሌለን አውቀን በጣም አስፈላጊ የሆነውን አካባቢያችንን በአግባቡ መጠበቅና መንከባከብ አለብን፡፡ ይህንን ካላደረግን ግን እናበላሻለን፤ በስራችንም ውጤት እንጎዳለን፡፡ አካባቢን የምንንከባከብ ከሆነ ግን በምላሹ ይንከባከበናል፡፡

የውሃ ምንጮችን በምንበክልበት ጊዜ የሚጠጣ ንጹህ ውሃ የምናጣው እኛ ነን፡፡ ለጊዜያዊ ጥቅም ብለን ዛፎችን ብንጨፈጭፍ ድርቅ ወይም የዝናብ እጥረት የሚጎዳን እኛኑ ነው፡፡ እነዚህና ሌሎች በርካታ አሉታዊ ሁኔታዎች እንዳይገጥሙን ህይወታችንን የምንወድ ከሆነ አካባቢን መውደድ አለብን፡፡

### 4.3.2 ንፁህ አካባቢ ማለት ጤናማ ህይወት ማለት ነው

አካባቢያችንን የበለጠ በተንከባከብን መጠን የበለጠ ንፁህና እና ምቹ መኖሪያ ቤት ይኖረናል፡፡ በሌላ በኩል አካባቢን ችላ የምንልና የሚጎዱ እርምጃዎችን የምንወስድ ከሆነ እንደ ውሃ፣ ምግብ እና መጠለያ ያሉትን መሰረታዊ ነገሮችን ለማግኘት የበለጠ እንቸገራለን፡፡

የተበከሉ የውሃ ምንጮች እና የተበከለ አየር እንደ ካንሰር እና ሌሎች የመተንፈሻ አካላት በሽታዎችን በማምጣት ለአስከፊ ጉዳት ይዳርጉናል፡፡ የአየር ብክለት ከተለያዩ በሽታዎች ጋር በቅርበት የተያያዘ ነው ፤ እንደ አስም፣የልብ ድካም፣ የሳንባ በሽታ እና ለሌሎችም በሽታዎች እንጋለጣለን፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሰው የሚኖርበትን አካባቢ መንከባከብና ንፅህ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና አለው፡፡

### 4.3.3 የሙቀት መጨመርን መቆጣጠር

በከባቢ አየር ውስጥ ያለው የሙቀት መጠን ትንሽ መጨመር እንኳን በአየር ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ለውጦችን ያመጣል፡፡ አማካኝ የአለም ሙቀት መጠን ከጨመረ በእፅዋትና በእንስሳት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያሳድር የአየር ንብረት ለውጥ ይከሰታል፡፡ ይህም ማለት በአንዳንድ አካባቢዎች ድርቅ በመሆን የምግብ እጥረት ሲያጋጥም በሌላ አካባቢዎች ደግሞ እንደ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ፣ጎርፍና የመሳሰሉትን በማስከተል በሰዎች ህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡

ለእነዚህ ሁሉ አሉታዊ ክስተቶች (ችግሮች) ዋነኛ ምክንያት የሚሆነው ራሱ የሰው ልጅ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ደን መጨፍጨፍ፣ ከተለያዩ ፋብሪካዎች የሚለቀቁ በካይ ጭስ እና ደካማ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት አካባቢ ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

**ተግባር 4.5**

- አካባቢያችሁን እንዴት ትንከባከባላችሁ?
- ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በአካባቢያችሁ ዛፍ ትተክላላችሁ?

### 4.3.4 ስነ-ምህዳርንና ሰብአዊነትን መጠበቅ

ሁሉም የእኛ እንቅስቃሴዎች (ተግባራት) በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በሥነ-ምህዳሩ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ማለት ይቻላል። በስርዓተ-ምህዳሩ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ካደረስን የተለያዩ እንስሳትም ይሁን ዕፅዋት ለአደጋ ይጋለጣሉ። ለምሳሌ የውሃ አካላትን በፕላስቲክ ወይም ከፋብሪካ በሚወጡ ዝቃጮች ብንበክል እዚያ የሚኖሩትን ህይወት ያላቸውን ዝርያዎች ለጉዳት እናጋልጣለን።

ስለዚህ ቁሳቁሶችን በምናመርትበት፣ በምንጠቀምበት እና በምናስወግድበት ጊዜ በሥነ-ምህዳሩ ላይ ምን ዓይነት ጉዳት እንደሚያመጣ ማሰብ አለብን። ይህ ካልሆነ ግን አሁንም በዙሪያችን ያሉትን ብቻ ሳይሆን እኛንም መልሶ ይጎዳል። አንዳንድ መርዛማ ጋዞች እና ቆሻሻዎች በቀጥታ በሰው ሕይወት ላይ አደጋ ያስከትላሉ።

### 4.3.5 ለሕይወታችን የብዝሃ ሕይወት አስፈላጊነት

ብዝሃ ህይወት የሚለው ቃል በዓለም ያሉትን የተለያዩ የእንስሳት፣ የእፅዋት እና ሌሎችንም ፍጥረታት መገኘትን ያመለክታል። የብዝሃ ህይወት መኖር የሰው ልጅ የሚፈልገውን ሁሉ እንዲያገኝ እድል ይሰጠዋል። ብዝሃ ህይወት በሰው ልጅ እንቅስቃሴም ሆነ በተፈጥሮ ሃይሎች በቀላሉ ሊጎዳ ይችላል።

በብዝሃ ህይወት ምክንያት ምግብ፣ አየር፣ ውሃ እና መጠለያ ማግኘት ችለናል። እነዚህ አስፈላጊ ነገሮች መገኘት እንዲችሉ በተለያዩ ዝርያዎች የተፈጠሩ ብዙ ተፈጥሯዊ ሂደቶች አሉ። በእነዚህ ሂደቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ነገር ከተፈጠረ አሉታዊ ግብረ-መልስ ሰንሰለት ሊከሰት ይችላል። ስለዚህ የአኗኗር ምንጫችንን ሊጎዱ የሚችሉ ክስተቶችን ለመከላከል አካባቢያችንን ልንጠነቀቅለት ይገባል።

### 4.3.6 አካባቢ የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን እና መኖሪያዎችን ያቀርባል

ለኑሯችን መሰረታዊ የሆኑትን እንደ ምግብ ፣ መጠለያ፣ አልባሳት፣ የቤት እቃዎችና የመሳሰሉትን የምናገኘዉ ከደን ሀብታችን ነዉ። ስለዚህ የደን ጭፍጨፋ ማለት እንዲህ ያሉ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን የማጣት አደጋ ነው።

በተጨማሪም ደኖች ለተለያዩ አዕዋፍና እንስሳትም መኖሪያነት ያገለግላሉ። በዓለም ላይ ካሉ





በርካታ ዝርያዎች መካከል ግማሽ ያህሉ በደኖች ውስጥ ይኖራሉ። ደኖቻችንን ካጠፋን የበርካታ ዝርያዎችን ቤት እናጠፋለን። ስለዚህ የደን ሀብቶችን ለአገልገሎት ስናዉል የደንን ስነ-ምህዳር በማይነካ መልኩ መጠቀማችንን ማረጋገጥ አለብን።

### 4.3.7 ግብረገባዊ ግዴታ አለብን

አካባቢያችን የመተዳደሪያችን ምንጭ ስለሆነ እኛም ለአካባቢያችን ጠንቃቃ መሆን አለብን። እያንዳንዱ ሰው አካባቢዉን የመንከባከብ ግብረገባዊ ግዴታ አለበት። ይሄን የምናደርገዉ አካባቢያችን ለኛ ጠቃሚ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ይህን ማድረግ ትክክለኛ ወይም አግባብ ስለሆነም ነዉ። አካባቢያችን በሕይወት ለመኖር የሚያስችለንን ሁሉንም ነገር በነጻ እያቀረበልን እኛ በምትኩ ስግብግብና ግድ የለሽ ሆነን ይህን ውብ አካባቢ መጠበቅ ካልቻልን የሚያቀርበውን ጣፋጭ ፍሬዎች ማጨድ አንችልም።

### 4.3.8 አካባቢን መጠበቅ ጥሩ ምላሽ ለማግኘት ወሳኝ ነው

አንድ የማያከራክር ነገር እኛ የምንኖረው አካባቢ የተፈጥሮ ሀብት ስለሚሰጠን ብቻ ነው። መስማት ብንፈልግም ባንፈልግም አካባቢ ከጠፋ እኛም አብረን እንጠፋለን። ስለዚህ አካባቢን መንከባከብ አማራጭ የሌለዉ ግዴታ ነው።

ሁሉ ነገራችን ህይወታችንም ጭምር እንዲንቀሳቀስ የሚያደርጉ ነገሮች ሁሉ ከአካባቢ የሚገኙ ናቸው። ለምሳሌ የሚታደሱም ሆነ የማይታደሱ የሃይል ምንጮች የሚገኙት ከዚሁ ከአካባቢ ነዉ። ስለዚህ አካባቢን ከጠበቅን ወደ ምቹዉ መኖሪያ ምድር መመለስ እንችላለን።

**ተግባር 4.6**

- አካባቢን መንከባከብ ለምን አስፈለገን?
- ብዝሃ ሕይወት ለሰው ልጆች ምን ጥቅሞች አሉት?

## 4.4 አካባቢን መንከባከቢያ መንገዶች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

**ተግባር 4.7**

- በዙሪያችሁ ያሉ አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶችን መጥቀስ ትችላላችሁ?

አካባቢያችንን ለመጠበቅ ከፈለግን እንዴት መንከባከብ እንዳለብን መንገዶቹን እንመልከት።

### 4.4.1 መቀነስ፣ እንደገና መጠቀም እና በሌላ መልኩ እንደገና መጠቀም

ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የምንጥለውን የቆሻሻ መጠን በቀነስን ቁጥር በምላሹ ደግሞ ብክለትን ለመቀነስ አንድ እርምጃ ይሆናል። ቁሳቁሶችን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ለምሳሌ ለእቃ መያዣነት ፌስታሎችን ከመጠቀም ይልቅ ከጨርቅ የተሰሩ መያዣዎችን ብንጠቀም ይመረጣል። እንደገና ልንጠቀምበት የምንችለውን ነገር ደግሞ በአግባቡ ሰብስበን ለአዳዲስ ምርቶች በጥሬ ዕቃነት ማዋል እንችላለን። ለምሳሌ ወረቀትን እንደገና ጥቅም ላይ ካዋልን አዲስ ወረቀት ለመሥራት ብዙ ዛፎችን መቁረጥ አያስፈልገንም።

እንዲሁም እንደገና ጥቅም ላይ ስናውል የወረቀት ቆሻሻዎች በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ እንዳይከመሩ እንከላከላለን። ይህ ደግሞ በአካባቢው ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ጎጂ ንጥረ ነገሮች ይፈጥራል። እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል እንደ ፕላስቲክ ያሉ ነገሮች በውሃማ አካላት ውስጥ (ሀይቅ፣ ባህር እና ውቅያኖሶች) ባሉ እንዳይገቡ ያደርጋል። ይህ በመደረጉ ደግሞ በውሃማ አካላት ዉስጥ በሚኖሩ ብዝሃ-ህይወት ላይ የሚከሰት አደጋን ይቀንሳል ።

### 4.4.2 የውሃ ሀብትን መጠበቅ

አካባቢን መጠበቅ በጣም የተወሳሰበ ተግባር መሆን የለበትም.። ትናንሽ የሚመስሉ ግን ቀላል ነገሮች ሳይቀር በዚህ ውስጥ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ለምሳሌ ከውሃ ጋር በተያያዘ የውሃ ቧንቧዎችን ከተጠቀምን በኋላ መዝጋታችንን አለመዘነጋት እንዲሁም የሚያንጠባጥብ ቧንቧ ካለ ተጨማሪ ውሃ እንዳይፈስ ቶሎ ማስተካከል ተገቢ ነው። ይህንን በጣም አስፈላጊ ሀብት እንዳናባክን ያረጋግጣል። እነዚያ ችላ ያልናቸው ጥቃቅን ጠብታዎች በየቀኑ ተደማምረዉ ከፍተኛ መጠን ላለዉ ብክነት ይዳርጉናል።

> **ተግባር 4.8**
>
> • በቤት ዉስጥም ሆነ በትምህርት ቤት የውሃ ቧንቧን ከፍታችሁ ከተጠቀማችሁ በኋላ ወዲያዉኑ ትዘጉታላችሁ?

### 4.4.3 ንጹህ የኃይል ምንጮችን መጠቀም

የዕለት ተዕለት ህይወታችንን ለመምራት የምንጠቀምባቸው አብዛኛዎቹ የኃይል ምንጮች ለአካባቢ ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ ልቀቶችን ያመነጫሉ። ለምሳሌ ነዳጅን ስንጠቀም ለአካባቢ ጎጂ የሆኑ ጋዞችን ($CO_2$) በመልቀቅ ለብክለት መንስዔ ይሆናል።

ስለዚህ የእንደዚህ አይነት ምርቶች አጠቃቀም በመቀነስ እምቅ የጋዝ ልቀትን (green-house effect) ተፅዕኖን በመከላከል አከባቢን ንጹህ ማድረግ ይቻላል። እንዲሁም በመጓጓዣ ጊዜ ፔትሮሊየም





እየሚፈስ ከሆነ በውሃ አካላት እና በመሬት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል።

ስለዚህ ንፁህ የሃይልን ምንጮችን ለምሳሌ እንደ ፀሀይ፣ ንፋስ፣ ውሀ፣ባዮማስ እና ሌሎችንም ታዳሽ የሆኑ የሀይል ምንጮችን መጠቀም አለብን። የቀጣዩን ትውልድ ዋስትና የምናረጋግጠው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

> **ተግባር 4.9**
>
> • በአካባቢያችሁ ያሉትን ታዳሽ የኃይል ምንጮች መጥቀስ ትችላላችሁ?

### 4.4.4 ከብክለት የፀዳ ግብይት

ገበያ ስንሄድ አንዳንድ ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ለምሳሌ የምንገዛቸዉ ምርቶች ማሸጊያ ወይም የማሸጊያ ቁሳቁሶች የፕላስቲክ ከረጢቶችን ከሆኑ በምትካቸዉ በቀላሉ የሚበሰብሱና ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ ከረጢቶችን መጠቀም ያስፈልጋል። ይህም በየቀኑ የምናመርተውን የፕላስቲክ መጠን መቀነስ ያስችለናል። አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉትን መያዣዎች ከመግዛት ይልቅ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትን ለግብይት መጠቀም በጣም ጥሩ ነው። እንዲሁም አነስተኛ የታሸገ ውሃ መግዛት በመተዉ በአካባቢያችን ያለውን የፕላስቲክ መጠን መቀነስ እንችላለን በምትኩ የተጣራ ውሃ መጠቀም እና እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንደ ብርጭቆዎችንና ጠርሙሶችን መግዛት እንችላለን። ይህ በአንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፕላስቲክ መያዣዎችን ከመጠቀም እንድንቆጠብ ይረዳናል በመሆኑም አካቢያችንን ከብክለት መታደግ እንችላለን።

### 4.4.5 የኬሚካል አጠቃቀምን መቀነስ

የተለያዩ ኬሚካሎችን ለግብርና ስራ የምንጠቀም ከሆነ ኬሚካሎቹ በአፈር ውስጥ እና በውሃ አካላት ውስጥ ይደርሳሉ።እነዚህ ኬሚካሎች በእፅዋትና እንስሳት እንዲሁም በሰው ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ወደ ወንዞች እና ውቅያኖሶች የሚገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በሥርዓተ-ምህዳሩ ውስጥ ጎጂ እና አልፎ ተርፎም ገዳይ ውጤቶችን ያስከትላሉ። ስለዚህ የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ሁልጊዜ የምናስወግዳቸውን ነገሮች በጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

### ተግባር 4.10

**በዚህ ተግባር ላይ ትክክለኛ የሆኑትን ቃላት በመጠቀም ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ።**

ለምን መቀነስ፣ እንደገና መጠቀም እና በሌላ መልኩ እንደገና መጠቀምን እንደሚገባ ተገንዝባችኋል። ብዙዎቻችን ልጆችንም ጨምሮ ቆሻሻ አካባቢያችንን እንዳይበክል ከምንጠብቅበት አስፈላጊ መንገዶች መካከል መቀነስ፣ እንደገና መጠቀም እና-----------ናቸዉ። የተጠቀምንባቸዉን የተለያዩ ቁሳቁሶች እንደገና መጠቀም የምንችልባቸውን መንገዶች ስናስብ ወይም ቆሻሻን በየቦታዉ ከመጣል በአግባቡ ወደ ማከማቻ ዉስጥ ስንሰበስበው የእኛን---------- ንጽህና (አየር፣ውሃ እና አፈርን ጨምሮ) ለመጠበቅ ይረዳናል። ለምሳሌ የተጠቀምንበትን ቁሳቁሶች በሌላ መልኩ እንደገና ጥቅም ላይ ስናውል በመሬት ውስጥ ባሉ ትላልቅ ጉድጓዶች ውስጥ አነስተኛ ቆሻሻ ይከማቻል። ይህም ጉድጓድ-----------ተብሎ ይጠራል። በተጨማሪም አዲስ ምርቶችን ከመግዛት ይልቅ ያገለገሉ እቃዎቻችን እንደገና ስንጠቀም ለምሳሌ እንደ አሮጌ የጽህፈት መሳሪያዎች መያዣ ያሉትን በመጠቀም አየሩን ከብክለት እንጠብቃለን፡ ፡ በሌላ አነጋገር ያገለገሉ ምርቶችን እንደገና መጠቀም ማለት ፋብሪካዎች ብዙ አዳዲስ ምርቶችን ማምረት አያስፈልጋቸውም። ይህ ደግሞ ኃይልን ይቆጥባል እናም ፋብሪካዎች ወደ አየር የሚለቁትን----------- መጠን ይቀንሳሉ።

## 4.5 አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለው መዘዝ

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

### ተግባር 4.11

- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን መዘዝ መጥቀስ ትችላላችሁ?



ምስል 4.2፡ በቆሻሻ የተበከለ አካባቢ





### 4.5.1 የውሃ እጥረት

አካባቢያችንን አለመንከባከብ የአካባቢ ብክለትን እና መበላሸትን ያመጣል። ለምሳሌ የንጹህ ውሃ ምንጮችን የምንበክል ከሆነ ለምግብ ፍጆታ የሚሆን ንጹህ ውሃ አይኖርም ማለት ነው።ውሃ ለህይወት እጅግ አስፈላጊ ነው ሲባል ያለሱ ህይወት የለም ማለት ነዉ። ስለዚህ ለእንስሳትም ሆነ ለተክሎች ንጹህ ውሃ ከሌለ ህይወትን እናጣለን ማለት ነው ።

### 4.5.2 የአየር ብክለት

የምንነዳቸው መኪኖች፣ ኢንዱስትሪዎች እና የኃይል ማመንጫዎች ሁሉም በአካባቢ ላይ ጎጂ የሆኑ ጋዞችን ያመነጫሉ። ከባቢ አየር በተበከለ መጠን ብዙ ተግዳሮቶች እና በሽታዎች ያጋጥሙናል። የአየር ብክለት አንዳንድ ጊዜ ለሰው ልጅ ገዳይ የሆኑ ብዙ ሥር የሰደደ የጤና ችግሮችን ያስከትላል። እንደ አሲዳማ ዝናብ ያሉ ነገሮች በብክለት ምክንያት የሚከሰቱ ሲሆን ይህ ደግሞ በእጽዋት እና በእንስሳት ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። በተጨማሪም የአየር ብክለት የአለም ሙቀትን በመጨመር የአየር ሁኔታ ለውጦች እንዲከሰቱ ያደርጋል ። ለምሳሌ ጎርፍ፣ኃይለኛ አውሎ ነፋሶች፣ድረቅ፣በረሃማነት ሌሎችንም ያስከትላል።

### 4.5.3 ደረቅና አደገኛ ቆሻሻዎች

በየቦታው የምንጥላቸዉ ደረቅ ቆሻሻዎች ሲጠራቀሙ ለአደገኛ በሽታ አምጪ ትህዋሲያን መራቢያ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ለእኛም ሆነ ለመጪው ትውልድ ጎጂ ናቸው። አንዳንድ ደረቅ ቆሻሻዎች የውሃ መተላለፊያዎችን እና የውሃ ማፋሰሻዎችን ይዘጋሉ ይህም በሰው ህይወት ላይ ትልቅ አደጋን ይፈጥራል።

### 4.5.4 የምግብ እጥረት

የአፈርን ለምነት ከሚቀንሱ ተግባራት መካከል የደን መጨፍጨፍና ማዕድን ማውጣት ይጠቀሳሉ። የአፈር ለምነት ማጣት ማለት የምግብ ምርት እጥረት ማለት ነዉ። ስለዚህ ሰዎች የምግብ እጥረት ይገጥማቸዋል። የአፈር መራቆት ለምግብ ምርት መቀነስ አሳሳቢ ጉዳይ ሲሆን በደንብ ካልተመረተ ደግሞ የምግብ እጥረትን ያስከትላል።

የደን መጨፍጨፍ የዝናብ መጠንን ይቀንሳል ይህም የንጹህ ውሃ መጠንን ብቻ ሳይሆን የምግብ ምርትን ይቀንሳል። ዝናብ ከሌለ የምግብ ምርት ይቀንሳል!



ምስል 4.3፡ የተበከለና ንጹህ አካባቢ

### 4.5.5 የብዝሃ ህይወት መጥፋት

አካባቢያችንን ካልተንከባከብን ለበርካታ ዝርያዎች ከምድረ-ገፅ መጥፋት ምክንያት እንሆናለን፡፡ የአንዳንድ ብዝሃ ህይወት ማነስ የሚያመለክተው በህይወታችን ውስጥ አንዳንድ በጣም አስፈላጊ ነገሮች እንደሚጎድሉን ነው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ የመድኃኒት ዕፅዋት ሊጠፉ ይችላሉ፣ ይህም ለእኛ ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ በተጨማሪም የአካባቢያችንን ውበት ይቀንሳል፡፡ እናም ከዚህ ቀደም የምናውቃቸው የተለያዩ ዕፅዋትና እንስሳት በመጥፋታቸዉ አካባቢዉ የተለመደዉን ደስታ አይሰጥም፡፡



ምስል 4.4: የደን ጭፍጨፋ

**ተግባር 4.12**

- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለው መዘዝ ምንድን ነው?
- የአየር ብክለት የሚያስከትለው መዘዝ ምንድን ነው?
- የብዝሃ ህይወት ማነስ ማለት----------------------------------.





### 4.6 የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአካባቢ እንክብካቤን ጽንሰ-ሀሳብ፣ አካባቢን የመንከባከብ አስፈላጊነት፣ አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶች እና አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለዉን መዘዝን ተምራችኋል፡፡ ይህ ምዕራፍ የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት እና እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ለመገንዘብ እንደረዳችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

አካባቢን በሚመለከት አሁን እያጋጠመን ያለው ችግር ከባድ ነው፡፡ ሆኖም ግን ጥሩው ነገር አካባቢን ለመንከባከብ የግድ ባለሙያ ወይም ባለሃብት መሆን አይጠበቅብንም፡፡ ሁሉም ሰው ለአካባቢው የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር እያንዳንዳችን በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ጠንቃቃ ከሆንን እና አካባቢያችንን ለመታደግ አንዳንድ ቀላል እርምጃዎችን ለመውሰድ ፈቃደኛ ከሆንን ትልቅ አስተዋፅዖ ማድረግ እንችላለን፡፡ አካባቢህን ሳትጎዳ ጠብቀህና ተንከባክበህ ኑር፡፡ ከዚህ የተለዩ ምርጫ እንደሌለን አዉቀን አካባቢያችንን መንከባከብ የግድ ነው፡፡ ለራሳችን ጤናማ ህይወትእንዲሁም ለመጪው ትውልድ ጥሩ የህይወት ዋስትና ለመሆን አካባቢያችንን መጠበቅ አለብን፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

| | | |
|---|---|---|
| •አካባቢ | •የደን ጭፍጨፋ | • በሌላ መልኩ እንደገና መጠቀም |
| •ጋዞች | •መኖሪያ•ብክለት | |
| •ሥነ ምህዳር•ጥበቃ | •የቆሻሻ ጉድጓድ | |

## ማጠቃለያ መልመጃ 4.1

### ትዕዛዝ 1:የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1) የሰው ልጅ በአካባቢው ላይ በአዎንታዊ እና በአሉታዊ መልኩ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

2) ዕፅዋት ከፍተኛውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ያመርታሉ፡፡

### ትዕዛዝ II:የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኂላ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1) አካባቢን ለመንከባከብየምትችሉበት አንዱ መንገድ ምንድን ነው?

(ሀ) ቆሻሻን በየቦታዉ መጣል

(ለ) ውሃ ማባከን

(ሐ) የደን መጨፍጨፍ

(መ) ቆሻሻን በተገቢው መንገድ ማስወገድ

2) አንድ ሰው ቆሻሻን ባገኘበት ቦታ ሲጥል ብታይ ምን ታደርጋለህ?

(ሀ) ምንም

(ለ) እኔም እጥላለሁ

(ሐ) እንዲያነሳ እነግረዋለሁ ካለሆነ በህግ እንዲጠየቅ አደርገዋለሁ

(መ) ቆሻሻውን ረግጨዉ አለፋለሁ

3) በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድረዉ የትኛው ነው?

(ሀ) የፀሐይ መሰብሰቢያ መጠቀም

(ለ) የተፈጥሮ ሀብቶችን ከመጠን በላይ መጠቀም

(ሐ) የኃይል አማራጮችን መጠቀም

(መ) ቆሻሻን በሌላ መልኩ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል





4) እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

(ሀ) የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታን ይቆጥባል

(ለ) ገንዘብ ይቆጥባል

(ሐ) የተፈጥሮ ሀብቶችን ይቆጥባል

(መ) ሁሉም መልስ ናቸዉ

5) ጥበቃ ማለት፦

(ሀ) ሀብትን ማባከን

(ለ) ሀብቱን እንደገና ለመጠቀም

(ሐ) ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ሀብቶችን መቆጠብ

(መ) ሀብቶችን ማምረት

### ትዕዛዝ III: አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡
2. አካባቢ አለመንከባበከብ የሚያስከትለው መዘዝ ምንድንነዉ?

# ምዕራፍ አምስት

# የማህበራዊ ድረገፆች አጠቃቀም ስነ-ምግባር

**መግቢያ**

ይህ ምዕራፍ ማህበራዊ ድረገፆችን የመጠቀም ስነ-ምግባር በሚል በአምስት ንዑሳን ትምህርት የተከፋፈለ ሲሆን እነዚህም የማህበራዊ ድረገፆች ትርጉም፣አስፈላጊነት ፣ ሥነ-ምግባራዊ እና ሥነ-ምግባር የጎደለው አጠቃቀም ስጋቶችን ይመለከታል። ተማሪዎች ወደ ምናባዊ ትምህርት ዘልቀው መግባት ሲጀምሩ የማህበራዊ ድረገፅ የመጠቀም ፍላጎታቸዉ ይጨምራል።

በትምህርት ዓለም ዉስጥ ዋናው ነገር ሌሎች እንዴት ለራሳቸው ማሰብ እንደሚችሉ ማስተማር ነው። በመማር ማስተማር  ሂደት ውስጥ ማህበራዊ ድረገፆችን መጠቀም ተማሪዎችን እና መምህራንን ለምናባዊ ትምህርት አስፈላጊ ሊሆን በሚችል አዲስ ክህሎት ለማዳበር ይረዳል። በዚህ ጊዜ በተለይ ወላጆች የልጆቻቸዉን የማሕበራዊ ድረገፅ  አጠቃቀም መከታተል ይጠበቅባቸዋል።

**የመማር ውጤቶች፦ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- ማህበራዊ ድረገፆች ምን ማለት እንደሆኑ ታብራራላችሁ።
- የማህበራዊ ድረገፆችን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ታስገባላችሁ።
- ማህበራዊ ድረገፆችን የመጠቀም ስነ-ምግባርን ታሳያላችሁ።
- ማህበራዊ ድረገፆችን ከሥነ ምግባር ውጭ የመጠቀም ስጋቶችን ትለያላችሁ።





## 5.1 የማህበራዊ ድረ ገፆች ትርጉም

ማህበራዊ ድረገፅ በ በይነመረብ ላይ የተመሰረተ የግንኙነት አይነት ነው።

ማህበራዊ ድረገፅ ከሌሎች ሰዎች ጋር መጋራት ወይም መግባባት ብቻ አይደለም። ከዚህም በላይ ዘርፈ ብዙ የሆነ ጽንሰ-ሀሳብን አጠቃሎ የያዘ ነዉ። አሁን በምንኖርበት ዓለም ላይ ትልቅ ለዉጥ እያመጣ ያለዉ ማሕበራዊ ድረገፅ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- የማህበራዊ ትስስር ገጾች (እንደ ፌስቡክ እና ቴሌግራም ያሉ)፣
- ቪዲዮችን የሚያጋሩ (ለምሳሌ፡ ዩቱብ) እና
- ምስል የሚጋሩ (ለምሳሌ፡ ኢንስታግራም)።

ማህበራዊ ድረገፅ ለመዝናኛነት የሚገለግሉ በርካታ የመስመር ላይ ማጫዎቻዎችን (online games) ሊያካትት ይችላል። በተጨማሪም ለሞባል እና ተመሳሳይ ለሆኑ መሳሪያዎች (ለምሳሌ ላፕቶፕ፣አይፓድ) ላይ የሚውሉ ማስተግበሪያዎች ለማህበራዊ ድረገፅ የተሰጠውን ፍቺ ያሟላሉ።




ምስል 5.1፡ተማሪዎች ላፕቶፕ እየተመለከቱ

**ተግባር 5.1**

- ጥንድ ሆናችሁ በመቀመጥ ከላይ ባለው ሥዕል ላይ ስላያችሁት ነገር ተወያዩ። የቡድናችሁን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ለመናገር ተዘጋጁ።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎች ማህበራዊ ድረገፆችን መጠቀም የሚጀምሩት ወይም የሚፈልጉት ለተግባቦት ብቻ ሳይሆን መረጃ ለማገኘት፣ ሀሳብ ለመለዋወጥና ለተለያዩ የፈጠራ ስራዎች ለመስራት ነዉ።

**ተግባር 5.2**

- 3 ወይም 4 ተማሪዎችን የያዘ ቡድን መስርቱና የማህበራዊ ድረ ገፆች ትርጉም ምን እንደሆነ ተወያዩ?
- ለየቡድኖቻችሁ አንድ አንድ ተወካይ ተማሪ ምረጡና መልሶቻችሁን ለጓደኞቻችሁ በክፍል ዉስጥ አቅረቡ ።

የማህበራዊ ድረገፅ ሃይል ሰዎች መረጃን በአንድ ጊዜ ለሌሎች ብዙ ሰዎች በፍጥነት ማዳረስ እንዲችሉ ማስቻሉ ነዉ።

## 5.2 የማህበራዊ ድረገፆች አስፈላጊነት

ማህበራ ዊድረገፅ ሁላችንም በመስመር ላይ የምንገናኝበትን እድል አመቻችቶልናል። ከዚህ በታች ያሉትን ሁሉ እንድንመረምር አስችሎናል፡-

- በአለም ላይ አሁን በዚህ ሰዓት ምን እየተደረገ እንደሆነ፣
- እርስ በርስ እና በሩቅ ካሉ ከማንኛዉም ሰዉ ጋር ለመገናኘት፣
- የምንፈልገዉን መረጃ ሁሉ በመዳፋችን ላይ ለማግኘትና
- ትክክለኛና አስተማሪ የሆኑ መረጃዎችን በበቂ ሁኔታ ለማግኘት።

በማህበራዊ ድረገፅ አማካይነት በርካታ ሰዎች ሆነው የሚጫወቱት የተለያዩ የመስመር ላይ ጨዋታዎች (online games) እና ሌሎች በይነመረብ ላይ የተመሰረቱ ጨዋታዎችን ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ በሞባይል ስልክ እና በሌሎች መሳሪያዎች ላይ የሚገኙ ብዙ መተግበሪየዎች ወይም አፕሊኬሽኖች ከየማህበራዊ ድረገፅ ፍፎ ጋር ይስማማሉ።

በአለም ዙሪያ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች መረጃን ለመለዋወጥ እና ግንኙነት ለመፍጠር ማህበራዊ ድረ ገፆች ይጠቀማሉ።

**•በግለሰብ ደረጃ፡-** ማህበራዊ ድረገፅ ከጓደኛ እና ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት፣ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር፣ እና ለመዝናናት ይጠቅማል።

**•በባለሙያ ደረጃ፡-** በልዩ ልዩ መስክ ያለንን እውቀት ለማስፋት እና ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመገናኘት ያለንን ሙያዊ አውታረመረብ ለመገንባት ማህበራዊ ድረገፆች መጠቀም ይቻላል።

**•መስሪያ ቤት ደረጃ፡-** ማህበራዊ ድረገፅ ድርጅቱ ከሰራተኞቹ ጋር እንዲወያይ፣ የደንበኞችን አስተያየት እንዲያገኝ እና ምርትና ስሙን ለማስተዋወቅ ያስችለዋል።





## 5.3. ማህበራዊ ድረገፆች የመጠቀም ሥነ-ምግባር

ተማሪዎች የማህበራዊ ድረገፆች ሲጠቀሙ መከተል ያለባቸው ስለሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች መማር፣ እንዴት በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚችሉና የመሳሰሉትን መማር አለባቸው።

ማህበራዊ ድህረ-ገጾችን ስትጠቀሙ ወላጆች በእናንተ ላይ እምነት ይጥላሉ። ከወላጆች እርቃችሁ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ ስትሆኑና ስትጠቀሙ ሙሉ ኃላፊነት እንዳለባችሁ ተገንዘቡ።

በሞባይል ስልካችሁ ላይ ማህበራዊ ድረገፆች ለመጠቀም የሚረዱዋችሁ አንዳንድ የስነ-ምግባር መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው።

1) ለምታዉቋቸው ቁጥሮች ብቻ ጥሪዎችን መልሱ። ይህ ከብዙ መልካም ካልሆኑ ሰዎች (የቴሌማርኬት ነጋዴዎችን፣ አዳኞችን፣ ጉልበተኞችና ዘራፊዎች) ይጠብቃል።

2) ማንኛውንም ፋይሎች ወይም መተግበሪያዎች ከማውረድና ከመጠቀማችሁ በፊት ፈቃድ አግኙ።

3) ከባህል ያፈነገጡ ዓይነት ፎቶዎን ማጋራት ውስጥ አትሳተፉ፤ፎቶዎችን በበይነመረቡ ላይ ከለቀቃችሁ እስከ መጨረሻ እዚያው ሊቆዩ እንደሚችሉ ማወቅ አለባችሁ።

4) አንድን ሰውፎ ቶግራፍ ከማንሳታችን ወይም ቪዲዮ ከመቅረፃችን በፊት ማስፈቀድ ያስፈልጋል።

ማህበራዊድረ ገፅ ለሰዎች የሚሰጠውን ያህል ከፍተኛ አገልግሎት ለመጥፎ ተግባርም ሊውል ስለሚችል ጥንቃቄና ክትትል ያስፈልገዋል። ሰዎች ማህበራዊ ድረ ገፆች በመጠቀም ብዙ ጊዜ ጎጂ የሆኑ መረጃዎችን በመፍጠርና በማሰራጨት ለተንኮል ስለሚያውሉት የምናገኛቸውን መረጃዎች ከመቀበላችን በፊት ማጣራት ተገቢ ነው። የውሸት መረጃ ስርጭትን እና ጎጂ ውጤቶቹን ለማስቀም አንድ ሰው ያገኘውን ሁሉ ማጋራት ወይም መለጠፍ የለበትም። መረጃው ሊያመጣ የሚችለውን ተፅእኖና አውነተኛነቱን በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል።

በማህበራዊ ድረገፆች ላይ ምንም ነገር ከመለጠፋችን በፊት በደንብ ልናስብበት ይገባል። ይህን ማድረጋችን ከችግር መራቅ ብቻ ሳይሆን ግጭቶችን ማስወገድና በሌሎች ዘንድ ትልቅ ተአማኒነትን እንድናገኝ ያስችለናል። በተጨማሪም በርካታ የትምህርትና የስራ እድል ለማግኘት ስናመለክት ሰፊ እድሎችን የሚሰጡ ጠንካራ የመስመር ላይ ስም እንገነባለን። የስራ ቀጣሪዎችና የነፃት ትምህርት ዕድል ሰጪዎች የእኛን እውነተኛ፣ አጋዥ፣ አነቃቂ፣ አስፈላጊ እና መልካም በሆኑ ልጥፎች የተሞላ መሆኑን ሲያውቁ ሥራ የማግኘት ወይም ነፃ የትምህርት ዕድል (የስኮላርሺፕ) ተቀባይነትን የማግኘት እድላችን ይጨምራል።




ምስል 5.2: አስብ

የተከታዮቹን ጥያቄዎች መልስ በሚገባ ማሰብ አለብን፡፡
የእነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛው መልስ መስጠፍ ወይም አለመስጠፍ እንዳለብን ጥሩ ውሳኔ ለመወሰን ይረዳናል፡፡

•እውነተኛ ነው? እውነተናኛቱን 100% እርግጠኛ ካልሆንን በስተቀር መረጃን አንለጥፍ ወይም አናጋራ፡፡

•ጠቃሚ ነው? የምንለጥፈው ለታዳሚዎችዎ (ለተመልካች ወይም አድማጭ) ጥቅም ይሰጣል? ወይም ለእኛ ጠቃሚ የሆነ ግብረመልስ ያመጣል? የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ "አይሆንም" ከሆነ ያንን መልእክት ከመለጠፋችን በፊት እንደገና እናስብበት፡፡

•የሚያነሳሳነው? ሁሉም ልጥፎች አበረታች ወይም አነሳሽ እንዲሆኑ አይጠበቅም፤ ነገርግን ይህ ሌሎችን የማያስቀይም ወይም ተስፋ የማያስቆርጥ መሆን አለበት፡፡ የልጥፉ ዓላማ የሌሎችን ተስፋ የሚሸረሽር ከሆነ ያንን ልጥፍ እንደገና ማየት ተገቢ ነው፡፡

•አስፈላጊነው? ልጥፋችን አጣዳፊ ወይም በጣም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፤ ግን ሌሎች ከዚህ መረጃ ይጠቀማሉ? ሌሎች ማወቅ ያለባቸውን ዜና እያስተላለፍንላችሁ ነው? ከሆነ ይለጥፉ! ነገርግን የግል መረጃን እያጋራን ከሆነ ወይም ሌሎች ማየት የማይፈልጓቸው ወሬዎች መለጠፍ አያስፈልግም፡፡

•መልካም ነው? መልእክቱን በድጋሚ ለመጨረሻ ጊዜ አረጋግጡ፡፡ ሰዎች በተለያየ መንገድ ሊተረጉሙት ስለሚችሉ ወይም አሽሙር የሚመስል ነገር ካለው ልጥፉን እንደ ስድብ ስለሚወስዱት ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡

ማህበራዊ ድረ ገፆች በምትጠቀሙበት ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ ሥነ-ምግባራዊ ተግባራት፡-

- ትልቅ ወይም አዋቂ ሰው ባጠገባችሁ ሲኖር ብቻ ኮምፒተር ተጠቀሙ፡፡
- በይነመረብ ከመጠቀማችሁ በፊት ሁልጊዜ ፈቃድጠይቁ፡፡
- በቀጥታ መስመር ላይ የሆነ ሰው እናንተን ማግኘት ከፈለገ ሁልጊዜ ለአዋቂ ሰው ንገሩ ወይም አማክሩ፡፡





- የማትወዷቸውን ድረገጾች ወዲያውኑ ዝጉ፡፡

## 5.4 ማህበራዊ ድረገፆች ከሥነ-ምግባር ውጭ የመጠቀም አደጋ

ሥነ-ምግባር የጎደለው የማህበራዊ ድረገፅ አጠቃቀም የግለሰብን አካላዊና የመረጃ ደህንነትን አደጋ ላይ ይጥላል፡፡

የቅርብ ጊዜ ጥናቶች በግልጽ እንደሚያሳዩት ማኅበራዊ ድረ ገፅ ልጆች ጎጂ ለሆኑ ይዘቶች እንዲጋለጡ ብዙ እድሎችን ይሰጣል፡፡ ሰዎች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተለየ ስምና ማንነትን በመላበስ በተለያዩ ወንጀሎች ላይ ጭምር ይሳተፋሉ፡፡ በተለይ ለዚህ ተጋላጭ የሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ መግባትና ረዳት አልባ መሆን ወይም አለማወቅ ወደ አደገኛ፣ አዋራጅ እና አስጨናቂ ክስተቶች ሊመራን ይችላል፡፡

ማንም ወላጅ ልጆቹ እንደዚህ አይነት ነገር እንዲያጋጥማቸው አይፈልግም፤ ለዚህም ነው እያንዳንዱ ትናንሽ የመረጃ የደህንነት ችግር ከማህበራዊ ድረገፆች ስነ-ምግባር አጠቃቀም ጋር ይገናኛል፡፡

ማህበራዊ ድረገፆች ከሥነ-ምግባር ውጭ በመስመር ላይ እየተጠቀማችሁ ከሆነ ለሚከተሉት ችግሮች ልትጋለጡ ትችላላችሁ፡፡

**•ለጥቃት፡-** ዲጂታል መሳሪያዎችን፣ ጣቢያዎችን እና መተግበሪያዎችን በመጠቀም ሊያስፈራሩን፣ሊረብሹን፣ሊጎዱንና ሊያናድዱን ለሚችሉ ግለሰቦችና ሊያጋልጡን ይችላሉ፡፡

**•ለአስመሳዮች፡-** ከማናውቃቸው ሰዎች ጋር መገናኘት አደጋ ሊኖረው ይችላል፡፡ መተማመንን ለመፍጠር ጓደኛ መስለው ወይም በሆነ መንገድ ግንኙነት ፈጥረው ችግር ውስጥ ሊያስገቡን ይችላሉ፡፡

ማህበራዊ ድረገፆች ሥነ-ምግባር በጎደለው መንገድ ስንጠቀም፡-

- ስምህን፣ እድሜህን፣ አድራሻህን፣ ስልክ ቁጥርህን ወይም የይለፍ ቃልን በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ መስጠት፡፡
- ለማናውቀው ሰው ሁሉ የራስን ምስል መላክ፡፡
- ከማታውቁት ሰው የተላኩ ኢሜይሎችን ወይም ፋይሎችን መክፈት፡፡
- ለማታውቁት ሰው ምላሽ መስጠት፡፡
- ጸያፍ ወይም ትህትና የጎደለው ቋንቋ መጠቀም፡፡
- ለወላጆቻችን ወይም ለአሳዳጊዎቻችን ሳናሳውቅ በመስመር ላይ ብቻ ከተዋወቅነው/ናት ሰው ጋር ፊትለፊት ለመገናኘት መዘጋጀት፡፡ አስታውሱ በመስመር ላይ የተዋወቅናቸው ሰዎች

እኛ እንደምናስባቸው አይነት ላይሆኑ ይችላሉ::

**ተግባር 5.3**

በቡድን ተቀምጣችሁ የሚከተለውን የሳራን መሳጭ ታሪክ አንብቡ::

**የፌስቡክ ጓደኝነት ሚስጥር**

ሳራ የምትኖረው በሀዋሳ ከተማ ውስጥ በሚገኝ አንድ አፓርታማ ላይ ነው:: ወላጆቿ ኮምፒውተር እንድትማር ይፈልጋሉ:: ሳራም ፈቃደኛ በመሆኗ ቤተሰቦቿ ደስ አላቸው:: በዚህም ለትምህርቷና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃ ለማግኘት እና ኢሜል ለመላክ ኮምፒዉተሯን ትጠቀምበት ጀመር:: የሳራ አክስትም ከእነሱ ጋር አብራ ትኖራለች:: ሁሉም ታታ ይሏታል::አንዳንድ ጊዜ ከቁርስ በኋላ ሳራ እና ታታ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ:: ነገርግን ሳራ የኮምፒዩተር ላይ ጨዋታዎችን መጫወት ትወዳለች::

ኮምፒዩተሩ ጨዋታዎች (games) ብቻ ሳይሆን ያሉት ፌስቡክም አለው:: ሳራ ፌስቡክን የተቀላቀለችው ከሁለት ወራት በፊት በአስራ ሶስተኛው ዓመት የልደቷ ቀን ነው:: ከቁርስና ከሻይ በኋላ ከትምህርት ቤት ጓደኞቿ ጋር በፌስቡክ ታወራለች:: በትምህርት ቤት አውቶቡስ ውስጥ እያሉ ያደረጉትን እርስበርስ ይነጋገራሉ::

**አንድ ጓደኛዋ፡-** “ስታወሪ ትጮሂ ነበር” ይላል::

ሳራ በዚህ ተናደደች:: ጓደኞቿን ከፌስቡክ ላይ ለመሰረዝ ወሰነች:: ከዚያ በኋላ አጣቻቸዉ::

ግን በጓደኞቿ ማዘኗን ከመንገሯ በፊት አዲስ የፌስቡክ የጓደኝነት ጥያቄ ቀረበላት:: ሜሮን ከምትባል ልጅ ነበር:: እሷም ልክ እንደ ፊልም ተዋናይት በጣም ቆንጆ ነች::

ሳራ ወዲያዉኑ ኮምፒዉተሯን ጠቅ አድርጋ የሜሮንን ጥያቄ ተቀበለች::

**ሜሮን ጻፈች:** “ብዙ ጓደኞች አሉሽ?”

**ሳራ መለሰች:** “አይ! ዛሬ የተወሰኑ ጓደኞቼን ከፌስቡክ ላይ ሰረዝኳቸዉ::” የሚያሳዝን ፊት ገላጭ ጨምራበት:: ”

**ሜሮን ጻፈች:** ”እና ምን? ምንም ያህል ጓደኞች ቢኖሩሽም ምንም ማለት አደለም::- ትልቁ ነገር የጓደኝነታችሁ ሁኔታ ነው:: እናም አሁን እኔ አለሁልሽ!” ሳራ ይህን ድምጽ ወደደችዉ::

**ሳራ መለሰች:** “የት ት/ቤት ነዉ የምትማሪዉ?”

**ሜሮን ጻፈች:** “የአንቺ ትምህርት ቤት አጠገብ”

**ሳራ መለሰች:** “የት ትምህርት ቤት እንደምማር እንዴት አወቅሽዉ?” ሳራ ተገረማለች::

**ሜሮን ጻፈች:-**”ምክንያቱም ትምህርት ቤትሽ ለኔ ቅረቤ ስለሆነ”

**ሳራ መለሰች:** ጥሩነው:: መገናኘት እንችላለን!”ሜሮን በረጅሙ ተነፈሰች::

**ሜሮን ጻፈች:-** “አዎ! እናም እኛ እስከመጨሻዉ ምርጥ ጓደኞች እንሆናለን:: ቻዉ!”

በማግስቱ ጠዋት ሳራ በአቅራቢያዋ ትምህርት ቤት ተፈለጋለች:: ነገር ግንምንም ማግኘት አልቻለችም:: በአቅራቢያዋ ስለሌላ ትምህርት ቤት አለመስማቷ ትንሽ እንግዳ ነገር ሆኖባታል:: ሜሮን ግን ከጓደኞቿ ሁሉ ብልህ ነች::ሜሮን የማንም ጓደኛ ሳትሆን የሳራ ልዩ ጓደኛነች::

ዛሬ ሳራ የያዘችዉ የምትወደው ምግብ ቢሆንም ምሳዋን ግን አልበላችም::

ታታ ምን ሆና ነዉ ያልበላችዉ ብላ አሰበች::

**ታታ:** “ደህና አይደለሽም እንዴ?”

**ሳራ:-** “ብዙ የቤት ሥራ ነበረብኝ ” በማለት ሳራ ዋሸች::

**ታታ:-** “እንግዲያው ሂጂና የቤት ስራሽን ጨርስ፤እኔም ትንሽ ልተኛ” አለች አክስቷ::

ሳራ ግን የቤት ስራዋን አትሰራም:: በምትኩ ኮምፒውተሯን መነካካት ትጀምራለች፤ቀጥታ መስመር ላይ (online) ገብታ አዲሷን ጓደኛዋን ማዋራት ጀመረች::ወዲያዉኑ ከሜሮን መልእክት ደረሳት::

**ሜሮን ጻፈች:** “ሠላም ጓደኛዬ እንዴት ነሽ?”

**ሳራ መለሰች:-** “ደህና ነኝ ምሳዬን ሳልበላ ነዉ የዋልኩት”

**ሜሮን ጻፈች:** “ለምን?”

**ሳራ መለሰች:-**ከአንቺ ጋር ተገናኝተን ማዉራት ስለምፈልግ::

**ሜሮን ጻፈች:** “በጣም ጥሩ አሁን ፎቶሽን ልትልኪልኝ ትችያለሽ? እንድደውልልሽ ቁጥርሽንም ስጪኝ”

**ሳራ መለሰች:-**“ስልኬ ካሜራ የለዉም አዝናለሁ” ሜሮንለሳራ ካሜራ ያለዉ ስልክ እሰጥሻለሁ አለቻት::

**ሜሮን ጻፈች:** -“እሁድ እንገናኝ:: ከዚያ ያንቺን ፎቶ እወስዳለሁ::አሮጌዉንም ስልኬን እሰጥሻለሁ::”

ሳራ ሁልጊዜ ካሜራ ያለው ስልክ ትመኝ ነበር::

**ሳራ መለሰች:-“** የት እንገናኝ?”

**ሜሮን ጻፈች**:"አኩኩሉ ሆቴል እንገናኝ"

**ሳራ መለሰች**፡-"ስንት ሰዓት?"

**ሜሮን ጻፈች**: "ከቀኑ 8 ሰዓት ላይ"

ታታ ለማጽዳት ሳራ ወዳለችበት ክፍል መጣች፡፡

**ታታ**፡- "ሳራ ምን እየሰራሽ ነው?"

**ሳራ**፡- "ታታ አዲስ ጓደኛ ተዋወቅሁ!" ታታ በሳራ ትከሻ ላይ ሆና የሜሮንን ፎቶ ተመለከተች፡፡

**ታታ**: - ይህቺ ኮ በጣም የምወዳት የፊልም ተዋናይት ሳያት ደምሴ ነች፡፡ ጓደኛሽ ናት? "

ሳራ መለሰች፡-"አዎ ስሟ ግን ሜሮን ትባላለች፡፡"

ታታ እየሳቀች ጭንቅላቷን ነቀነቀች፡፡

**ታታ**: ይህቺ እኮ ሳያት ነች ሁሉንም ፊልሞቿን አይቻቸዋለሁ፡፡ እስከ አሁን ትልቅ ሰዉ ትሆናለች፡፡

**ሳራ መለሰች**፡- "እረ እሷ የእኔ እኩያ ናት!" ስትል ሣራ ተናገረች፡፡

**ታታ**፡- "አይ!አይ! እሷ እኮ የእኔ እኩያ ነች ያፎቶ የተወሰደዉ ገና ትምህርት ቤት እያለች ከመጀመሪያዋ ፊልም ላይ ነው፡፡"

ሳራ በታታ ተናደደች፤ከዚያም ማሰብ ጀመረች፡፡
ሜሮን ያሳየችኝ የሌላ ሰው ፎቶ ነዉ ማለት ነዉ?

**ሳራ መለሰች**፡- "ስንት ዓመትሽ ነው?"

**ሜሮን ጻፈች**:"ነገርኩሽ አይደል 13 ዓመቴ ነዉ ብዬ"

**ሳራ መለሰች**፡- በጣም ጥሩ! የቅርብ ጓደኞሞች እድሜያቸው ተመሳሳይ ሲሆን ደስ ይላል፡፡"

**ሳራ ጻፈች**፡- "ሄይ! በፌስቡክ ገጽሽ ፎቶሽ ላይ ያሉት የጆሮ ጌጦች በጣምያማምራሉ!"

**ሜሮን ጻፈች**: "አመሰግናለሁ እኔ ራሴ የሰራኋቸው ናቸዉ፡፡"

**ሳራ መለሰች**: "ዋዉ! ነገ ስንገናኝ አደርገሻቸዉ ነይ!"

**ሜሮን ጻፈች**: "እሺ ግን ብቻሽን ከመጣሽ ነዋ!"

**ሳራ መለሰች**: "ለምን?"

**ሜሮን ጻፈች**: "እኔም ብቻዬን ስለምመጣነው! ሚስጥር እንድናወራ!" አለችና ሜሮን ከመስመር ወጥታለች፡፡

ሳራ በጣም ግራ ተጋባች፡፡ ስለአዲሷ ጓደኛዋ እንግዳ ነገር አለ? ዋሽታኝ ይሆን እንዴ? እያለች የቤት ስራዋ ላይ ማተኮር አልቻለችም፡፡

ሳራ፡:" ታታ!"ብላ ተጣራች፡፡

ታታ: "አቤት ልጅ" ምን ሆንሽ! ችግር አለ? " ሳራ ስለሜሮን እውነቱን ለመናገር ወሰነች፡፡

ሳራ: "ታታ! ምን ማድረግ አለብኝ?"

በማግስቱ ሳራ እና ታታ ከቀኑ 8 ሰአት በፊት አኩኩሉ ሆቴል ደርሰው በሆቴሉ በር ፊትለፊት ቆሙ፡፡አዲሷ ጓደኛዋ ታማኝ መሆኗን ወይም አለመሆኗን ለማወቅ ሚስጥራዊ እቅድ አላቸው፡፡

ታታ: -"የሆቴሉን ሥራ አስኪያጅ እንዲረዳን ሄጄ አነጋግረዋለሁ፡፡" አለች

8 ሰዓትላይ ሳራ ዙሪያዋን መመልከት ጀመረች፡፡ ሜሮን የት እንደምትጠብቃት በሆቴሉ ውስጥ ይሁን ከሆቴሉ ውጪ አታስታውስም፡፡

ታታ የትሄደች? አጠገቧ የለችም፡፡ ብዙ ሰዎች ወደ ሆቴል ይመጣሉ ይገባሉ፡፡ነገር ግን ሜሮንን የሚመስል የለም፡፡

አንድ በዕድሜ አባቷን የሚያህል ሰው ወደ ሳራ መጣ፡፡

ፈገግ አለ፡፡

**እንግዳዉ ሰዉዬ**: "ሳራ እንዴት ነሽ!"አላት

ሳራ ደነገጠች፡፡ እሱን አታውቀውም፡፡

**እንግዳዉ ሰዉዬ**: "አንቺን ስላገኘሁሽ ደስ ብሎኛል!"

**ሳራ**፡- "ማነህ...ማነሽ–አንቺሚሪ...ሜሮንአይደለሽም!" ስትል ሣራ፡፡

**እንግዳዉ ሰዉዬ**: "አይ! እኔ አጎቷ ነኝ እናም ጓደኛሽ መሆን እፈልጋለሁ፡፡"
"እንዳንቺ ከሆኑ ወጣት ልጃገረዶች ጋር ጓደኝነት መመሥረት እወዳለሁ፡፡" አለ ሜሮንን ያልሆነዉ እንግዳው ሰዉዬ፡፡

**ሳራ**: እእእ.......!ሳራጮኸች፡፡

ታታ ከሆቴሉ አስተዳዳሪ ጋር በሰከንድ ዉስጥ አጠገቧ ደረሱ፡፡

እንግዳዉ ሰዉዬ ተገረመ፡፡ ሳራ ሁለት ጎልማሶችን ታመጣለች ብሎ አልጠበቀም ነበር፡፡

ታታ በቦርሳዋ መታችው::

ከዚያም ጮኸች::

ታታ፡- "የእህቴን ልጅ እንዴት ብትደፍረኝ ነዉ! አታፍርም!" "ኦው!" እሱደነገጠ::

ከዛም ወደ ጎዳና ሮጠ:: የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ሰውየውን ለመያዝ ሞከረ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ያሉበት ዉስጥ ገብቶ ተሰወረ:: ሁሉም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዱ::

**ፖሊስ፡-** "ጎበዞች ናችሁ! -ስለዚህ አስመሳይ ሰዉዬ ስላሳወቃችሁን እናመሰግናለን:: "ሳራ ይሄን በማሳወቅሽ ጎበዝ ነሽ:: እባክሽን ይሄንን ፖስተር በትምህርት ቤትሽ ውስጥ ለጥንቃቄ ሲባል ለጥፊዉ::" እንዲሁም በትምህርት ቤትሽ ውስጥ መጥተን ከእንደነዚህ ዓይነት አጭበረባሪ ሰዎች ተማሪዎች ራሳቸዉን እንዲጠብቁ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትን መስጠት እንፈልጋለን::

**ፖሊስ፡** የሳይበር ወንጀልን የሚከታተል ባለሙያ የሳራን ኮምፒተር ማጣራት ይፈልጋል::

በማግስቱ አንድ የሳይበር ወንጀል ባለሙያ በሳራ ኮምፒዩተር ውስጥ ጠቃሚ መረጃ አገኘ:: በሰዓታት ጊዜ ውስጥ ሜሮንን መስሎ ሲያጭበረብር የነበረውን ሰው ፖሊስ አገኘው:: ከሚሰራበት ኮምቦልቻ ከሚገኘውቢሮውዉስጥ ያዙት:: በማህበራዊ ድረገፅ ከብዙ ወጣት ልጃገረዶች እና ወንዶች ልጆች ጋር ጓደኝነት ለመመሥረት ሲሞክር አገኙት:: ሳራ ከራሷ ትምህርት ቤት ብቻ ጓደኞች እንዲኖሯት ወሰነች:: ከፌስቡክ ጓደኛዋ ጋር ስለገጠማት አስፈሪ ሁኔታ ለጓደኞቿ መንገር አልፈገለችም::

1) እናንተ በሳራ ቦታ ብትሆኑና ጓደኞቻችሁ ቢያሾፉባችሁ ምን ይሰማችኋል? ለምን?

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

2) ከፌስቡክ ጓደኛችሁ ጋር የምታጋሩት አንድ የግል መረጃ ምንድነው? ለምን?

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

3) ለፌስቡክ ጓደኛችሁ የማታጋሩት አንድ የግል መረጃ ምንድን ነው? ለምን አይሆንም?

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------





4) እናንተ በሳራ ቦታ ብትሆኑና የፌስቡክ ጓደኛችሁ በአካል እንድትገናኙ ቢጠይቃችሁ ምን ትወስናላችሁ? ለምን?

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

5) እናንተ በሳራ ቦታ ብትሆኑና የፌስቡክ ጓደኛችሁ ቀጠሮ ቢያስዛችሁ ለቤተሰብ ታሳዉቁ ነበር? ለምን?

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

## 5.5 የምዕራፉ ማጠቃለያ

ማህበራዊ ድረገፆች እና በሌሎች የኦንላይን ገጾች (ለምሳሌ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ኢንስታግራም፣ ቴሌግራም፣ ዩቲዩብ እና ሊንክዲኤን) በትላልቅ ቡድኖች መረጃን ለመለዋወጥ፣ማህበራዊና ሙያዊ ግንኙነቶችን ለማዳበር እና የንግድስራን ለማስተዋወቅ በሚጠቅሙ መንገዶች መግባባት ነው::

ማህበራዊ ድረገፆች ስለመጠቀም ስንናገር ትልቁ ነገር ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ለማምጣት ብዙ መማር መቻላቸው ነው::

•ማህበራዊ ድረገፅ በኮምፒዩተር ላይ የተመሰረተ ቴክኖሎጂ ሲሆን ሃሳብን፣ አመለካከን፣ እዉቀትንና መረጃዎችን በምናባዊ ትስስር (virtual networking) አማካኝነት ማህበረሰብን ማስተማር ነው::

•በአሁኑ ወቅት ትልቁ የማህበራዊ ድረገፆች አውታረ-መረቦች ፌስቡክ፣ ኢንስታግራም፣ ቲክቶክ፣ ዩቱብ፣ ቴሌግራም ያካትታል::

•ማህበራዊ ድረገፅ ግለሰቦች ከጓደኞቻቸው እና ከዘመዶቻቸው ጋር እንዲገናኙ ያስችላቸዋል::

•አንዳንድ ሰዎች አውታረ-መረብ ለመፍጠር እና የስራ እድሎችን ለማግኘት በዓለም ዙሪያ ካሉ ሰዎች ጋር ከባለሙያዎች ጋር ለመገናኘት እና የራሳቸውን ሃሳብ፣ ስሜት እና ግንዛቤ በመስመር ላይ ለማካፈል የተለያዩ የማህበራዊ ድረገፅ መተግበሪያዎችን ይጠቀማሉ::

•ማህበራዊ ድረገፆች ብዙ ጥቅሞች አሉት እናም ድንቅ ቴክኖሎጂ ነው:: ነገር ግን አላግባብ ጥቅም ላይ ከዋለ ችግር ሊያስከትል ይችላል:: ኢንተርኔትን ባግባቡ ተጠቀም::

## ቁልፍ ቃላት

- •ማህበራዊ ድረገፆች
- • ሥነ-ምግባራዊ
- •ሥነ-ምግባር የጎደለው
- • ጥቃት
- •አስመሳዮች
- • አስብ

## 5.1 የማጠቃለያ መልመጃ

ትዕዛዝ፡-ከተስማማህ "አዎ" ካልተስማማህ "አይ" የሚለዉን ክበብ።

1) ስለምጠቀምባቸው ማህበራዊ ድረገፆች በጥንቃቄ ምርጫዎችን አደርጋለሁ። (አዎ/አይ)
2) ሰዎችን በመስመር ላይ ስም ወይም በአካል በመጥፎ ስም ፈጽሞ አልጠራቸውም። (አዎ/አይ)
3) የእነርሱ ፍቃድ ከሌለኝ በስተቀር ስለሌሎች ሰዎች ፎቶዎችን፣ ቪዲዮዎችን ወይም መረጃዎችን አላጋራም። (አዎ/አይ)
4) በመስመር ላይ የማየው ነገር ሁሉ እውነት ያልሆኑ እንዳሉ አውቃለሁ። (አዎ/አይ)
5) የሌላ ሰውን ስራ አልገለብጥም ወይም አላጋራም እና የእኔ እንደሆነ አልናገርም። (አዎ/አይ)
6) መረጃን በመስመር ላይ ከማጋራቴ በፊት የማምነውን አዋቂ እጠይቃለሁ። (አዎ/አይ)





# ምዕራፍ ሥድስት

# የባህል ትስስር

መግቢያ

በቀደመው ምዕራፍ የማህበራዊ ድረገፅ አጠቃቀም ስነ-ምግባርን በተመለከተ የማህበራዊ ድረገፆች ምንነት፣የማህበራዊ ድረገፅ አይነቶች፣ የማህበራዊ ድረገፅ አስፈላጊነት፣ የማህበራዊ ድረገፆች አጠቃቀም ስነ-ምግባር እና የማህበራዊ ድረ ገፅ ስነ-ምግባር የጎደለው አጠቃቀምን በተመለከተ ተምራችኋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥደ ግሞ ስለባህል ትስስር የሚያተኩር ሆኖ የባህል ትስስር ትርጉም፣ የባህል ትስስር አስፈላጊነት እና የባህላዊ ግንኙነቶች አመልካቾችን ትማራላችሁ።

**የመማር ውጤቶች፡-ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- •የባህል ትስስር ትርጉም ታብራራላችሁ።
- •የባህል ትስስር አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ታስገባላችሁ።
- •የባህላዊ ግንኙነቶች አካል ወይም አመላካቾችን ትለያላችሁ።
- •ውጤታማ የባህል ትስስር ታሳያላችሁ።

## 6.1 መግቢያ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- የባህል ትስስር ምንድን ነው?
- የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች በባህል ትስስር ላይ ምን ተጽእኖ አላቸው?

ቅድመ አያቶቻችን በተወለዱባቸው መንደሮች ውስጥ ይኖሩ ነበር እናም አብዛኛውን መረጃ የሚለዋወጡት በአካል ፊት ለፊት በመገናኘት ነበር:: ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ የላቁ የትራንስፖርት ሥርዓቶች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች፣ የንግድ፣ የትምህርት እና የፖለቲካ አውታር መስፋፋት ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ሰዎችን  በቀላሉ እንዲገናኙ አድርጓቸዋል::

ዓለም አንድ መንደር ሆናለች የተሰኘበት ዋናው ምክንያት ከመገናኛ ቴክኖሎጂዎች መዘመን ጋር ተያይዞ ማንኛውንም መረጃ ወይም ዜና በጣም ሩቅ ወደ ሆኑ የአለም ክፍሎች እጅግ ባጠረ ጊዜ የሚያደርሱበትን ክስተት ለመግለጽ ነው:: አሁን ላይ የሰው ልጅ መልከዓ-ምድራዊ ድንበሮች ሳይወስኑት ሀሳቦችን በቀላሉና በፍጥነት መለዋወጥ ይችላል:: ይህም በበኩሉ የሰውን ልጅ የተግባቦት ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ ለወጠው::

ባለፉት ዓመታት አንድ ሰው የሚሄድበት ርቀት በተለምዶ በማህበራዊ ግንኙነቶች የተገደበ ነበር:: የስልክ፣ የፋክስ፣ የኢሜል፣ የኢንተርኔት እና የማህበራዊ ድረ-ገጾች አቅርቦት በመኖሩ ከሌሎች ጋር የሚገናኙበት መንገዶች እየበዙ በመምጣታቸው የሰው ልጅ ግንኙነቱ በብዙ እጥፍ እያሳደገ ሄዷል:: ይህ ጊዜ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እርስበርስ የተሳሰሩ ሆነዋል፡ ፡ በመሆኑም  የባህል ትስስሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ይበልጥ ውስብስብ እየሆነ የመጣበት ወቅት ነው::



ምስል 6.1: የባህል ትስስር





## 6.2 የባህል ትስስር ትርጉም

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

1. የባህል ትስስር ምንድን ነው?
2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ባሉ ተማሪዎች መካከል ያሉትን የባህል ልዩነቶችን ዘረዝሩ?

የባህል ትስስር በአንፃራዊነት አዲስ መደበኛ የሆነ የማህበራዊ ሳይንስ ጥናት መስክ ነው:: ከሌሎች ጋር በተለይም የተለያየ ባህል ካላቸው ጋር የመስማማት ችሎታን ይመለከታል::

ግላዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን መጀመር እና ማቆየት የሰው ልጅ አስፈላጊ የህይወት ክፍል ነው::

የሰዎች ግንኙነት በማህበራዊ ፍላጎቶች ላይ ተመስርቶ ከሌሎች ጋር የማገናኘት መስተጋብር ሂደት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል:: ሰዎች በማህበራዊ ቡድኖች፣በቤተሰብ፣ በጓደኝነት፣ በጎሳ በመሳሰሉት በመደራጀት እርስ በእርስ የተሳሰሩ ናቸዉ:: በእንዲህ ዓይነቱም ግንኙነት ራሳቸዉን ይገልጻሉ፤ሌሎችንም ይገመግማሉ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተሰጠ ያለዉ **የባህል ትስስር ጥናት** በማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዉስጥ ሰዎች ከራሳቸው ባህል ውጭ እንዲረዱ፣ እንዲግባቡ እና የተወሰኑ ግቦችን እንዲያሳኩ ለማሰልጠን የተነደፈ ተግባራዊና ባለብዙ መስክ ጥናት ነው:: የባህላዊ ግንኙነቶች በመሠረታዊ ደረጃ ራስን እና ዓለምን በሌላ ዓይን እንዴት ማየት እንደሚችሉ መማርን ያካትታል:: ሰዎችን ከራሳቸው ጋር ለሚመሳሰሉ ባህሎች (ለምሳሌ በራሱ አካባቢ ወይም ሀገር ውስጥ የተለየ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ቡድን) ወይም ከራሳቸው በጣም የተለየ ባህሎች ጋር እንዲገናኙ ለማዘጋጀት ይረዳል:: አንዳንድ የባህላዊ ትስስር ገጽታዎች አቅማቸዉና ባህላዊ ማንነታቸው ከሌሎች የውጭ ሀገራት ጋር ያለው ትስስር እንዴት መከበር እንዳለበት ያካትታል::

ዛሬ ላይ ዓለማችን በመገናኛ ብዙኃን፣ ኢንተርኔት እና ቴክኖሎጂ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ላይ በሚያሳድሩት ተጽዕኖ ምክንያት ብሔራዊ ድንበሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደበዘዙ በመምጣት ዓለም ወደ ሉላዊነት ተለዉጣለች:: እነዚህ ምክንያቶች የተለያዩ ግለሰቦች እንዲገናኙ እና በቀላሉ የባህል ልውውጥ እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: ስለዚህ ስለባህላዊ ግንኙነቶች እና እነዚህ ትስስሮች ስለሚፈጥሯቸዉ እድሎች እና ስለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ማውራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ አያስደንቅም::




ምስል 6.2፡ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች መገኛ መሆኗን የሚያሳይ ምስል



ምስል 6.3: ልዩነቶችን አድንቁ

### ተግባር 6.1

1. ከላይ ባለው ሥዕል ላይካሉት ልጆች መካከል ምን ዓይነት ተመሳሳይነት ተመለከታችሁ? ምን ልዩነቶችስ ማየት ቻላችሁ? በክፍል ዉስጥ ተወያዩበት፡፡
2. በልጆቹ መካከል የተመለከታችሁትን 5 ልዩነቶ ችፃፉ፡፡

(ሀ) ------------------------------------------------------------------------------------

(ለ)------------------------------------------------------------------------------------

(ሐ)------------------------------------------------------------------------------------

(መ)------------------------------------------------------------------------------------

(ሠ)------------------------------------------------------------------------------------

3. ልጆቹን የሚያመሳስሏቸውን ነገሮች ጻፉ፡፡

   ---------------------------------------------------------------------------------



የግብረ ገብ ትምህርት

## 6.3 የባህል ትስስር አስፈላጊነት

የባህል ትስስር አስፈላጊነት ምንድ ነው? በባህል ትስስር ውስጥ መሆን ብዙ ፈተናዎችን ሊያመጣ ይችላል፤ ከግራመጋባት እና ስለምትወደው ሰው ባህሪ ካለመረዳት እስከልዩነትን መፍራት፡፡ ነገርግን በባህል መካከል ያለው ግንኙነት እየጨመረ ሲሄድ ለእነዚህ ግንኙነቶች በርካታ የማይናቅ ጠቀሜታዎች ያስገኛሉ፡፡

1) **አዲስ ባህልን መተዋወቅ**

ከአዳዲስ ባሕሎች ጋር ግንኙነት ስትጀምር የራሱ የሆነ ወጎችና ልማዶች ስላለው አንተ ስለማታውቀው ባህል መማር ጀመርክ ማለት ነው፡፡ የምንግባባባቸው መንገዶች ከድምፃችን አወጣጥ አንስቶ እስከምናራምደዉ የግል አቋም (ፅንሰ-ሀሳቦቻችን) እና የምናሳያቸዉ ምልክቶች በባህሎቻችን ከፍተኛ ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል፡፡ ሃይማኖቶቻችን፣ የምንናገርባቸው መንገዶች፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር ያለ ንግንኙነት እና ብዙ ጊዜ የምናደርጋቸው የአምልኮ ሥርዓቶችም እንዲሁ፡፡

2) **አዳዲስ ክህሎትን መማር**

ባህል የአንድ የተወሰነ የሰዎችን ቡድን ሰፊ ልምዶችን ይገልፃል፡፡ የሚመገቡትን ምግብ፣ የሚሰሙትን ሙዚቃ እና የሚጫወቱትን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እና የሚያነቡትን መጽሐፍ ያጠቃልላል፡፡ ከባህላችን ጋር የተያያዙትን አብዛኞቹን ክህሎቶች እናዉቅ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በባህል ትስስር ውስጥ ስንሆን ሙሉ ለሙሉ ከአዳዲስ ባህሎች ጋር መተዋወቅ ይጠበቅብናል፡፡ ለምሳሌ በተለያየ የኢትዮጵያ ቦታዎች የሚደረጉ የስፖርት ልምምዶችን ስናደርግ፣ ከጓደኞቻችን ወይም ከቤተሰብ አባላት ጋር ስንዝናና እና አንዳንድ ጽሑፎች ስናነብ የተለያዩ ባህሎችን እንማራለን ወይም እንተዋወቃለን፡፡

3) **ያለፈ ጥላቻን ማስወገድ**

የባህል ትስስር ከሚያስገኛቸው ትላልቅ ጥቅሞች ዉስጥ አንዱ በሁለት ሰዎች አማካኝነት ተጀምሮ ተጽዕኖዉ በእያንዳንዱ ሰዉ ላይ መድረስ መቻሉ ነዉ፡፡ በአንድ ወይም በጥቂቶች አነሳሽነት የሚመጣ ጭፍን ጥላቻ የሚያስከትለዉን ስቃይ ቢያንስ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ጤናማ በሆነ ግንኙነት መፍታት ይችላል፡፡ የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞች እና የማያውቋቸው ሰዎች ጭፍን ጥላቻ ከፊት ለፊታቸው ካለው ጥሩ ግንኙነት ጋር ምንም ተያያዥነት እንደሌለው ሲያውቁ ይህ የእርቅ ውጤት ሊያድግ እና ሊያብብ ይችላል፡፡ በዛሬው ማህበረሰብ ውስጥ ብዙ ዓይነት የባህል ግንኙነቶች አሉ፡፡ የባህላዊ ትስስር ዘር፣ እድሜ፣ ሀይማኖት፣ መደብ፣ ዜግነት፣ የፆታ ምርጫ እና የአካል እና የአዕምሮ ችሎታዎችን ልዩነቶችን ያሏቸውን ሰዎችን ማካተታቸው የተለመዱ ሆነዋል፡፡

ከባህላችን ከሚለዩ የተለያዩ ግለሰቦች ጋር ያለን ግንኙነት በጋብቻ፣ በቤተሰብ በኩል ከምናገኛቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት፣የስራ ቦታ ወይም የትምህርት ቤት ጓደኝነት፣ በጉዞ ከምንተዋወቃቸዉ ወዘተ

ጋር በሰላም አብሮ የመኖርን መርህ መቀበል ያስፈልጋል።

የባህል ትስስርን መጠበቅ ሶስት መሰረታዊ ማህበራዊ ፍላጎቶችን ያሟላል።

•መካተት (የባለቤትነት ስሜት)

•ፍቅር (ለሌሎች ፍቅር መስጠትና መወደድ) እና

•ማሳመን (ሌሎችን ለማሳመን ወይም የሌሎችን ለመቀበል ዝግጁ መሆን)

ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች የመካተት ፣ፍቅር የመስጠትና ማመን ፍላጎቶችን የሚያሟሉት በተለያየ መንገድ ነዉ። ለምሳሌ በአንዳንድ ባህሎች ወንዶች ሴቶችን በር ከፍተዉ እንዲያስገቧቸዉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሌላ ባህል ውስጥ ደግሞ አንዲት ሴት ጥቂት እርምጃዎችን ወደ ኋላ እንድትሄድ ይጠበቅባታል ይህም ወንድነቱን ከማክበር ጋር ይያያዛል፡፡

1. በአካባቢያችሁ የሚከበሩ የተለመዱ ባህሎችን ጥቀሱ?
2. ዓለም አንድ መንደር ናት ሲባል ምን ማለት ነዉ?
3. ከላይ በተ.ቁ 2 ለተሰጠዉ መገለጫዎቹ ምን ምን ናቸዉ?
4. የባህላዊ ትስስር ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው? እንዴት ነው የሚፈቱት?

ሉላዊነት ኣለምን ወደ አንድ መንደርነት የአለምን ህዝቦች አቀራርቧል። ይሁን እንጂ መድልዎ እና ሌሎች አለመቻቻል ችግር መፍጠራቸውን ቀጥለዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው የብዝሃ-ባህላዊ ማህበረሰብ ውስጥ እነዚህ ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ በጎሳ፣ በዘርና በቋንቋ ዘዉግ ላይ ተመስርቶ ወደ መገለል እና ወደ ጉልህ ልዩነት ያመራል፡፡

የባህል ትስስሮችን መገንባት ፈታኝ ነው። ግለሰቦች በባህል የተለያዩ መሆናቸዉ አንዱ የሌላዉን ባህል እንዲያከብር ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ግለሰቦች ወይም ቡደኖች ከራሳቸዉ ዉጭ ያለዉን ባህልና የባህል ህግጋት በመጣስ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነታቸዉ ሊጎዳ ይችላል፡፡ በቡድን ግንኙነት ላይ ጥናት ያደረገ አንድ የምርምር ዉጤት የሚያመለክተው ሰዎችን በቡድን መከፋፈል ብቻውን አድልዎን ለመፍጠርና ለማባባስ በቂ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም እኛ (ቡድን ውስጥ ያለነው) ወይም የእኛ ወደሚል የቡድናዊነት ግንዛቤ ይመራናል፡፡ ይህም እነሱ ብለን የምንሰይማቸው የተለዩ ቡድኖች ከእኛ ስለሚለዩ ጥሩዎች አይደሉም ወደሚል ድምዳሜ ወስደናል። በመሆኑም ይህ የተዛባ አመለካከት አላስፈላጊ የቡድን ተፎካካሪነትና የማይፈለጉ ፍረጃዎችን ብሎም ጭፍን ጥላቻን ያስከትላል፡፡

ከዚህ በመነሳት የተዛባ አመለካከት፣ ጭፍን ጥላቻ እና መድልዎ በፆታ፣ በማህበራዊ መደብ፣ በሃይማኖት፣ በዘር ወይም በሌሎችም ላይ የተመሰረተ ይሆንና በስራ፣ በመኖሪያ ቤት፣ በፖለቲካዊ





መብቶች፣ በትምህርት እድሎች እና በሌሎች ቦታዎች ላይ ይንጸባረቃል።

እነዚህ በባህል ትስስር ላይ ጠንካራ ተጽእኖ ስላላቸው ለመልካም የባህል መስተጋብር ትልቅ እንቅፋት ናቸው። ስለዚህ ከኛ ዉጭ ላሉት የተለያዩ ባህሎች እዉቅና በመስጠት በባህል መካከል መተሳሰብን ማዳበር አለብን። በአንድ አለም ዉስጥ እንደመኖራችን መጠን በባህል የተዋሃዱ ግንኙነቶችን መገንባት አስፈላጊ ነገር ሆኗል፡፡

ምሁራን እንደሚሉት ሉላዊነት እየተጠናከረ ሲሄድ ድንበሮችና ወሰኖች አንድ እየሆኑ በማህበረሰብ ባህሎች መካከል ይበልጥ መተሳሰር እና መተሳሰብ እየተፈጠረ ይሄዳል፡፡ ይህ ሂደት ግለሰብና እና ማህበረሰብ በመልከዓ-ምድር ብዙ ጫና ሳይኖርባቸዉ በቀላሉ የመገናኘት እድላቸዉን እያሰፋዉ መጥቷል፡፡

የባህል ትስስር መጨመር የባህል ልዩነቶችን በማጥፋት ወደ አንድ ዓለም አቀፋዊ ባህል እየተዋጡ ነው ማለት አይደለም። አዳዲስ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ያቀራርቡናል፤ ይህ ማለት ግን በተዋኸደዉ ዓለም ዉስጥ ድርሻ የለንም ማለትአይደለም።

በአንድ በኩል በኢኮኖሚና በፖለቲካዊ መደጋገፍ፣ በትራንስፖርትና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት ምክንያት በአንድ ወቅት የባህል ልዩነትን አስከትሎት የነበረውን መገለል እየጠፋ እንዲሄድ ሲያደርጉት በሌላ በኩል እነዚሁ ዝንባሌዎች በባህል የተለዩ ምላሾችን እና ለባህል-ተኮር ምርቶች የተሻሻሉ እድሎችን ይፈጥራሉ።

በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች በአዲስ የግንኙነት ቴክኖሎጂ አማካኝነት በቀጥታ መገናኘት እንዲችሉ በማድረግ አንዱ ሌላኛዉን እንዲመለከት ይረዳዋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ቴክኖሎጂዎች የአገር በቀል ባህሎች የራሳቸውን የሚዲያ አውታሮች እንዲፈጥሩ እና ሌሎቹን በእንግድነት በመቀበል የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

የማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስሪት ዓለማቀፋዊነትን ወደ አንድ ማዕቀፍነት በማጥበብ ሲወስደን ይህም በአንድ ወጥ በሆነ ስርዓት ዉስጥ እንድንገዛ ያደርገናል፡፡

የባህል ትስስርን ለመገንባት አንዱ እንቅፋት የሚሆነዉ ብሔር ተኮርነት ሲሆን እሳቤዉም የራስን ባህል ከፍ በማድረግ የሌሎች ባህሎች ያነሱ እንደሆኑ አድርጎ ማየት ነዉ፡፡ ብሔር ተኮርነት ብዙውን ጊዜ የራስን ቡድን ትክክል አድረጎ መዉሰድና ከቡድን ውጭ ባሉ አባላት ላይ የተሳሳተ አመለካከት በመያዝ የሚመሰረት ነው።የተዛባ አመለካከታችን የግምታችንን መሳሳትን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዳናይ ይከለክለናል።

ለሰዎች በባህላቸዉ መካከል ያለዉን ግንኙነት የበለጠለ ማዳበር ብሄር ተኮርነትን መቀነስ እና ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ተግባቦት በህግ የሚመራ ባህሪ ነው፤ ነገርግን ህጎች ከባህል ባህል ይለያያሉ። በባህላዊ ግንኙነት ውስጥ ስንገባ በሌላ ባህል ውስጥ ተገቢውን ባህሪ

የሚቆጣጠሩትን ሁሉንም ህጎች ላናውቅ እንችላለን:: የእኛ አመለካከቶች እና ፍረጃዎች አዎንታዊ እይታ እንዳንይዝ እና የምንተገብረዉ ነገር ምናልባት ብቸኛው ወይም የተሻለው የአሠራር መንገድ እንዳል ሆነ እንዳንገነዘብ እና እንደሁኔታው የመግባቢያ ስልታችንን በማስተካከል ረገድ ዝግጁ እንዳንሆን ያደርገናል::

1) የባህል ትስስር አስፈላጊነት ምንድነው?

2) የባህል ትስስር ዓይነቶችን ዘርዝሩ::

3) የባህል ትስስር ፈተናዎች ምንድን ናቸው?

## 6.4 የባህል ትስስር አመላካቾች

በርካታ የባህል ትስስር አመላካቾች አሉ:: ከነዚህም መካከል ውጤታማ ተግባቦት፣ባህላዊ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ ድልድዮች እና ብቃት ያለዉ የተግባቦት ባህሪ ሲሆኑ ቀጥሎ እያንዳንዳቸውን እንመልከት::

### 6.4.1 ውጤታማ ተግባቦት

- ውጤታማ ተግባቦት ምንድንነው?
- ከጓደኞቻችሁ ጋር ጥሩ ተግባቦት እንዳላችሁ ይሰማችኋል?

ዉጤታማ ተግባቦት የሚባለዉ ላኪዉ ያቀረበዉን ሃሳብ፣ አመለካከት፣ እዉቀትና መረጃ በተሟላ መንገድ ለተቀባዩ የመድረስ እንዲሁም የተቀባዩን መረጃ ለላኪዉ የመለዋወጥ ሂደት ነዉ:: በሌላ መንገድ የመረጃ ልውውጥ በላኪና በተቀባይ መካከል ዓላማውን ጠብቆ የማከናወን ሂደት ነው::

በአጠቃላይ ዉጤታማ ተግባቦት የሚያካትተዉ:-

(ሀ)ላኪ:- መልእክት በመላክ የግንኙነትሂደቱን የሚጀምረው ሰው ነው::

(ለ)ተቀባይ:-መልእክቱ ሊደርስለት የሚገባው ሰው ነው::

ተግባር6.2:

ተማሪዎች በረድፍ ሆናችሁ በመቀመጥ ከአንዱ ጎን አንድ ረድፍ የመጀመሪያው ተማሪ አንድ ቃል በዝቅተኛ ድምጽ ለሚቀጥለው ተማሪ ንገረው ከዚያም በዚህ ረድፍ ውስጥ እስከ መጨረሻ ያለው ተማሪ ድረስ ቅብብሉ ይቀጥል:: ከዚያም 1ኛውን ተማሪ ለቀጣዩ ተማሪ የነገረውን ቃል ጠይቅ እና ቃሉ በመጨረሻው ተማሪ ከተናገረው ቃል ጋር አንድ አይነት መሆኑን አረጋግጥ::

- ለመጨረሻው ተማሪ የተነገረው ቃል ከአንደኛው ጋር አንድ አይነት ነው?
- የተለየ ከሆነ ለምን?





**የውጤታማ ተግባቦት ባህሪያት**

ለውጤታማ ተግባቦት መልእክት ማስተላለፍ ብቻ በቂ አይደለም:: የላኪውን ዓላማ ማሟላትአለበት:: ይህንን ታሳቢ አድርገን ተግባቦትን ውጤታማ ስለሚያደርጉት ዋና ዋና ነገሮች እንወያይ:-

**•ግልጽ መልእክት:** ላኪው ማስተላለፍ የሚፈልገው መልእክት ቀላል፣ ለመረዳት የማያስቸግርና ትርጉም እንዲሰጥ ሆኖ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆን አለበት::




ምስል 6.4: የውጤታማ ተግባቦት ባህሪያት

**•ግልጽ መልእክት:** የሚተላለፈው መረጃ በምንም መልኩ ግልጽነት የጎደለው ወይም ሐሰት መሆን የለበትም:: ከሰዋሰዋዊ ስህተቶች የጸዳመሆን አለበት::

**•የተሟላ መልእክት:** መግባባት ለውሳኔ መሰረት ነው:: መረጃው ያልተሟላ ከሆነ ወደ ተሳሳቱ ውሳኔዎች ሊወስደን ይችላል::

**•ቀጥተኛመልእክት:** የተላከው መልእክት አጭርና ቀጥተኛ ትርጓሜን በመስጠት የተፈለገውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መሆን አለበት::

**•ተዓማኒነት ያለው መልዕክት:-** ላኪው ስለሚያስተላልፈው ነገር ትክክለኛነት እስከ መጨረሻው እርግጠኛ መሆን አለበት::ይህ ሲሆን ተቀባዩ በላኪው ላይ እምነት ይኖረዋል፤እናም በተላከው መልእክት ላይ ሙሉ መተማመን ላይ ይደርሳል::

**•ተቀባዩን ከግምት ያስገባ መልዕክት:-** መልዕክቱን የምንልክበት የመገናኛ መንገዶቹና የተቀባዩ

የአመለካከት፣የቋንቋ፣የእውቀት፣የትምህርት ደረጃ እና አቋምን ከግምት ውስጥ በማስገባት ማቀድ አለብን።

•የመልዕክቱ ላኪ ጨዋነት፡ የተረቀቀው መልእክት ላኪው ያለውን ጨዋነት፣ትህትና እና ለተቀባዩ ያለውን አክብሮት የሚያንፀባርቅ መሆንአለበት።

## 6.4.2 በባህል ትስስር ውስጥ ባህላዊ ሽምግልና

- ባህላዊ ሽምግልና ምንድን ነው?
- በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች ግጭቶችን እንዴት ይፈታሉ?

በባህል ትስስር ውስጥ ባህላዊ ሽምግልና የባህል አስታራቂዎች ሆነው በተለይም በባህል አለመግባባት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመከላከል እንዲሁም መፍትሄ በመስጠት ይታወቃሉ። ሽምግልናው በተጣሉት በሁለቱ ወገኖች መካከል በመግባት ሁለቱም የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ እና የበለጠ አጥጋቢ በሆነ መልኩ እንዲገናኙ የሚደረግበትሂደት ነው።

በባህል መካከል የሚደረግ ሽምግልና በባህል አለመግባባት የተከሰቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ገለልተኛና ችሎታ ያለው አስተባባሪ እንዲኖር ማድረግን ያካትታል። ይህም የባህልንና የቋንቋ ክፍተቶችን በማጣጣም ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው።

ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ግጭቱን ለመፍታት ያላቸውን ፍላጎት መግለጽ እና ለሁሉም ፍትሃዊ መፍትሄ ለማምጣት ቁርጠኛ መሆናቸው አስፈላጊ ነው። የመፍትሄ ሃሳቦችን ማገናዘብም አስፈላጊ ነው።

አሁን ባለንበት በፍጥነት እያደገ ባለው ዓለም አቀፋዊ የባህል ትስስር ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ግንኙነቶችን ለማዳበር ያግዛሉ። ነገርግን ይህ ሁኔታ ግጭቶችን ያስከትላል፤ አንዳንድ ጊዜ በባህሎች መካከል አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በባህሎች እና ስልጣኔዎች መካከል ግጭቶች ይከሰታሉ።

በባህል ትስስር ውስጥ ያለ ባህላዊ ሽምግልና የሥነልቦና፣ የቋንቋና የባህል ጽንሰ-ሀሳቦችን አጠቃሎ የያዘ መስክ ነው።

- በባህል ትስስር ውስጥ የባህላዊ ሽምግልና ጥቅሞች ምንድናቸው?

በባህል ትስስር ውስጥ የባህላዊ ሽምግልና ጥቅሞች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የተለያዩ ለባህል መስተጋብር እንቅፋት የሚሆኑትን በመቀነስ የተሻለ ተግባቦትና የግንኙነት እንዲሁም በመካከላቸው መተሳሰብና መደማመጥ እንዲፈጠር ለማመቻቸት፣
- ለሁለቱም ወገኖች አመለካከታቸውን እንዲገልጹ እድል መስጠት፣





- ግጭትን በገለልተኛ፣ በባህል ምላሽ በሚሰጥ የሶስተኛ ወገን እርዳታ እና
- በህብረተሰቡ ውስጥ ባህላዊ አካታችነትና እና ግልጽነትን ማሳደግ።

## 6.4.3 የነቃ ተግባቦታዊ ባህሪ

• የነቃ ተግባቦት ማለት ምን ማለትነዉ?

የስሜታዊ ደህንነት ፍሰት በህይወት ዉስጥ የሚፈልጉትን ነገር በግልፅ ተግባቦት እንዲፈጥር ይረዳል። ሰዉ በመማር እንጅ በመወለድ ይዞት የሚመጣ ክህሎት የለም። ፍላጎታችሁን በመግለፅ ረገድ የተካናችሁ ካልሆናችሁ ብቃት ከሌላቸዉ ሰዎች ስለተማራችሁ ነዉ። የንቃተ ህሊና ቁልፍ መርህ ፍላጎታችሁን የሚያሟላዉን ልዩ ባህሪ በመጠየቅ ለሌላ ሰዉ በተቻለ መጠን ቀላል ማድረግ ነዉ። ሰዎች የተጋላጭነት ስሜት ሲሰማቸዉ ጉልበታቸዉ የሚፈልጉትን የማግኘት እድል እንደሚጨምር በማመን፣ በመጠየቅና በማስፈራራት ይካሳሉ።

ይህ አቀራረብ ብዙን ጊዜ ተቃራኒዉን ዉጤት ያስከትላል። ፍላጎቱም የሚያመለክተዉ ተቀባዩ ከሰጪው ያነሰ ዋጋ ያለዉ መሆኑና ስለዚህ ሰጪዉ ለሌሎች የመናገር መብት እንዳለዉ ነዉ። ይህ መርህ በሁሉም ግንኙነቶች ላይ ማለትም በንግድ አጋሮች፣ ስራ ባልደረባ፣ ጓደኞች፣ ልጆችና ወለጆች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

ከባህሎች ጋር ልምድ ከሌላችሁ የተለያዩ ባህል ያላቸዉን ሰዎች መረዳት በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ባህላዊ ተግባቦት ለብዙ ዓመታት ስለተለያዩ እምነቶች፣ ባህሪያት፣ የዓለም እይታዎችና ልማዶችን በመማር ማዳበር የሚያስችል ክህሎት ነው። በዚህም ከባህል ጋር በመግባባት ብዙ ልምድ ያለዉን በባህል መካከል አስታራቂን መምረጥ በጣም አስፈላጊ ነዉ።

ከዚህ በታች የተገለጹት ባለአራትደረጃነጥቦች የነቃ ተግባቦትን ለማዳበር የሚረዱቀላልሂደቶች ናቸው።

1) ስሜታዊ ያደረገንን ክስተትመለየት፡-ስሜታዊ መሆን ማለት በተጨባጭ ምን እንደሆነ በግልፅ ማስቀመጥ፤በተቻለመጠንራስን እንደ ውጪ ታዛቢ አድርጎ በመውሰድ ተጨባጭእውነታዎችንብቻመግለጽ። ለምሳሌ፡- “ጓደኛዬ በሰዓቱ አይደርስም” ከማለት ይልቅ “ጓደኛዬ በሰዓቱ እንደሚደርስ ተስማምቶ ነበር ነገር ግን እስከ አሁን አልደረሰም ።” የሚለው የተሻለ ነው።

2) ለስሜታችን ሃላፊነት መውሰድ፡- ስሜታችንን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸውን ቃላት መምረጥ።

   ለምሳሌ እያጋጠሙን ያሉ ስሜቶችን፣ ሀዘን፣ ብቸኝነት፣ ብስጭት ወይም ቅናት”ተሰማኝ” የመሳሰሉትን ቃላት እናስወግድ። ምክንያቱም የተጎጂነትን ስሜት የሚያጠናክሩ ስለሆነ፡ ፡ በተመሳሳይ “ችላተብሏል፣ተከዳ ወይም ውድቅ ተደርጓል” የሚሉት ቃላት በእኛ ውስጥ

ሌላ ሰው ሚና እንደ ተጫወተ ይጠቁማሉ። ለእኛ ስሜቶች ሀላፊነት ስንወስድ ለሌላ ሰው እናሳውቃለን እንጂ ሌላውን አንከስም ወይም ተጠያቂ አናደርግም።

3) የምንፈልገውንና ያላገኘነውን እንለይ፡- በአግባቡ ፍላጎቶቻችንን መለየትና እነሱንም ማሳወቅ ከቻልን ሰጭዎች ብዙ ነገር ሊያደርጉልንና እንደጨቅላ ሕፃናት ይንከባከቡን ነበር።ይሁን እንጂ እኛ የምንፈልገውን ሳናውቅና ሳናሳውቅ ሌሎች እንዲያደርጉልን እንጠብቃለን።

4) የምንፈልገውን እንጠይቅ፡-ፍላጎቶቻችንን የሚያሟሉልንምን የተለያዩ ባህሪያት ወይም ድርጊቶች አሉ? ለምሳሌ የጓደኛችንን የበለጠ ትኩረት ከፈለግን ከእኛ ጋር ብዙ እንዲቆይ ከመጠየቅ ይልቅ አብሮን የእረፍት ጊዜውን እንዲያሳልፍብን ጠይቀው የተሻለ ይሆናል።

ከላይ የተጠቀሱትን የተግባቦት ሂደቶች በመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ውስጣዊ ስሜቱን ይገልፃል፤ከሌሎች የሚፈልገውንም ይጠይቃል፤ የተሳካ ተግባቦትም በእጅጉ ይጨምራል።

### ተግባር 6.3

ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን የእናንተን ባህላዊ ማንነት ግምት ውስጥ በማስገባት በውስጡ ምንምን ጠቃሚ ነገሮችን እንደያዘ? ተወያዩበት። ከዚህ በታች የተሰጡትን የእናንተን ባህላዊ ማንነት በመግለፅ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

1) የባህል ማንነታችን፡-........................................................................

2) እኛ ያለን ልማድ፡-........................................................................

3) መለያ ምልክቶቻችን፡-........................................................................

4) በባህላችን የምንመገበው ምግብ፡-............................................................

5) የምንደሰትባቸው ክብረበዓላት፡-..............................................................

6) ለመጎብኘት የምንፈልጋቸው ቦታዎች፡-......................................................

7) የምንለብሰው ልብስ፡-.......................................................................

8) የምናደንቀው ጥበብ፡-.......................................................................

9) ሌላ ጠቃሚ መረጃ፡-.........................................................................





## 6.5 የምዕራፉ ማጠቃለያ

ይህንን ምዕራፍ ካነበባችሁ በኋላ ባህል እንዴት በባህል ትስስር ላይ ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚችል የበለጠ ተገንዝባችኋል። ከባህል ትስስር ትርጉም በመነሳት የባህላዊ ግንኙነቶች በመቀጠልም የባህላዊ ትስስርን አስፈላጊነትና የባህል ትስስር ዓይነቶችን ተምራችኋል።በመጨረሻም በውጤታማ ተግባቦትና በባህላዊ ሽምግልና እንዲሁም በነቃ ተግባቦታዊ ባህሪያት ላይ በማተኮር ሰፋ ያለ የእውቀት መሰረት እንዳገኛችሁ ተስፋ እናደርጋለን።

### ቁልፍቃላት

- የባህል ትስስር
- ግንኙነት
- ተግባቦት
- ዓለም አቀፍ መንደር
- ሉላዊነት
- ማህበራዊ ሚዲያ
- ጭፍን ጥላቻ
- ማካተት
- ፍቅር
- ተግዳሮት
- ንቃተ ህሊና

## የማጠቃለያመልመጃ 6.1

**ትዕዛዝ I:የሚከተሉትን ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆነ አውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።**

1) የባህል ልውውጥን ለመጨመር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

2) ባለፉት መቶ ዓመታት አንድ ሰው በተለምዶ የሚሄድበት ርቀት በማህበራዊ ግንኙነቱ ተወስኖ ነበር፡፡

3) የእኛብቻ ነው ትክክል የሚለው አስተሳሰብ ሌሎች ማስረጃዎችን እንዳናይ መሰናክል ሆኖብናል፡፡

4) ብሄር ተኮርነት የባህል ግንኙነቶችን ለመገንባት እንቅፋት ነው፡፡

**ትዕዛዝII:የሚከተሉትን ጥቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1) አሁን ባለንበት ዓለም ውስጥ ብሔራዊ ድንበሮች እየደበዘዙ ናቸው ምክንያቱም፡-

(ሀ) የካፒታሊዝም መምጣት

(ለ) የትምህርት መስፋፋት

(ሐ) የመገናኛ ብዙኃን ወቅታዊ ተጽእኖ

(መ) በሀብታሞች እና በድሆች መካከል ያለው ልዩነት መስፋፋት፡፡

2) ከሚከተሉት ውስጥ ስር-ነቀል የመረጃ ቴክኖሎጂ የትኛው ነው?

(ሀ) ስልክ

(ለ) ፋክስ

(ሐ) ኢንተርኔት

(መ) ሁሉም

3) ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ መሰረታዊ ማህበራዊ ፍላጎቶች በማሟላት የሰዎች ግንኙነት ለማጠናከር አይረዳም፡፡

(ሀ) ማካተት

(ለ) ፍቅር

(ሐ) ማግለል





(መ) ማሳመን

4) ከሚከተሉት ውስጥ ውጤታማ የተግባቦት ባህሪያት ያልሆኑት የትኞቹ ናቸው?

(ሀ) የተሟላ መልእክት

(ለ) ትክክለኛ መልዕክት

(ሐ) አስተማማኝነት

(መ) አለመተማመን

5) አሁንባለው ሁኔታ የዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያልሆነዉ፡-

(ሀ) ባህልእያደገ ነው፡፡

(ለ) ሉላዊነት

(ሐ) የተሳሳተተግባቦት

(መ) ዓለምአንድ መንደርነች፡፡

ትዕዛዝ III:ባዶ ቦታዉን በትክክለኛው መልስሙሉ፡፡

(ሀ)አንዳንድ ጊዜ የባህል ትስስር ............................................................ ይባላል፡፡

**ትዕዛዝIV:አጭር መልስ ስጡ፡፡**

(ሀ) የባህላዊ ሽምግልና ጥቅሞች ምንድን ናቸው?